
ፍኖተ ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ሚያዚያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም. ዋጋ ብር 6.00

2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.38

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!



# አንድ ዘለላ አለች እዚያ ስንደርስ ተመሳሳይ ዓላማ ካለን ጋር መዋሐዳችን አይቀርም

6

ኢ/ር ኃይሉ ሻወል

# የኦሮሞ ነገር - - - ከገዳ እስከ ገዳዳዉ ኦህዴድ







2

# በአፈወርቅ ተክሌ ሞት ማዘኑን አንድነት አስታወቀ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ እጅግ የተከበሩ ሜትር አርቲስት ሎሬየት አፈወርቅ ተክሌ ከዚህ አለም በሞት መለየታቸው እንዳሳዘነው ገለፀ፡፡ ፓርቲው ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በላከው ደብዳቤ “ታላቁ አርቲስት በጠለቀው የአርት ጥበባቸውና በታላላቅ የሥነጥበብ ሥራዎቻቸው አማካይነት በኢትዮጵያ ለሥነጥበብ መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጋቸው በላይ የሚወዷት ኢትዮጵያ አገራቸውንና ሕዝባቸውን ለዓለም ህብረተሰብ ያስተዋወቁ ታላቅ የጥበብ ሰው ናቸው፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመላው የስነጥበብ ዓለም ሲዘከሩና ሲከበሩ ይኖራሉ፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክም የክብር ሥፍራ ይኖራቸዋል፡፡” ሲል አሞካሽቷቸዋል፡፡

አንድነት በመጨረሻም “ለሟች ቤተሰብ መጽናናትን እየተመኘ ታላቁ የጥበብ ሰው በሕይወታቸው ዘመን ያፈሯቸው ብርቅ የጥበብ ሥራዎችና ቅርሶች በጥንቃቄ እንዲሁም በክብር ተይዘውና ተጠብቀው ለትውልድ የሚተላለፉበት ሁኔታ እንዲመቻች አደራ እንላለን፡፡” ሲል በላከው ደብዳቤ ደምድሟል፡፡

# ርዕዮት ዓለሙ በህመም ላይ ናት

በሽብርተኝነት ተከሳ 14 ዓመትና 33 ሺ ብር ቅጣት የተወሰነባት ጋዜጠኛና መምህርት ርዕዮት ዓለሙ ታማ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እየተመላለሰች መሆኗን ከቤተሰቦቿ መረዳት ተችሏል፡፡ ቤተሰቦቿ እንደሚሉት “ርዕዮት በጡቷ ላይ በተፈጠረ ዕጢና በጨጓራ ህመም እየተሰቃየች ስትሆን ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለህክምና ትመላለሳለች፡፡” ብለዋል፡፡

ምንጮቻችን እንደሚሉት “ሆስፒታሉ ከሰውነቷ ናሙና ወስዶ የመረመረ ሲሆን ጡቷ ቀዶ ጥገና ያስፈልገዋል በማለት ሐኪም ወስኗል፡፡ በተደጋጋሚ የህክምና ቀጠሮ ቢኖራትም ማረሚያ ቤቱ “አንዴ መኪና የለኝም፤ አንዴ አጃቢ የለኝም፤ በማለት ህክምናዋ እየተስተጓጎለባት ነው፡፡” በማለት ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡ ርዕዮ ዓለሙ በአዲስ ፕሬስ ጋዜጣ፣በቼንጅ መጽሔትና በኤፍ ኤም 96.3 ሬዲዮ ላይ በጋዜጠኝነት ያገለገለ ሳይሆን በፍትህ ጋዜጣ አምደኝነትና በኢትዮጵያ ሪቪው ድህረ ገድ በሪፖርተርነት እየሠራች ሳለ በሽብርተኝነት ተከሳ የተፈረደባት ናት፡፡

ወደ ገፅ 16 ዞሯል

# ወጣቱ በሱዳን ሠላም ህክምና ማዕከል ተፈፀሙብኝ በሚለው የግድያ ሙከራ እና የአካል መጉደል የእርዳታ ጥሪ አቀረበ

የባህርዳር ዩኒቨርስቲ 3ኛ ዓመት የሕግ ተማሪ የሆነው ወጣት ማርቆስ ከተማ በሱዳን ሠላም የህክምና ማዕከል ውስጥ በተፈፀሙብኝ ኢ-ሰብአዊ ድርጊትና የግድያ ሙከራ በህግ ለመጠየቅ እርዳታ እንዲደረግልኝ ጥሪዬን አቅርቡልኝ ሲል ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቀ፡፡ ወጣት ማርቆስ ከተማ ይህንን የገለፀው ዝግጅት ክፍላችን ድረስ ይዞ በቀረበው 15 ገጽ የህክምና ሰነድ ነው፡፡

ወጣቱ እንደሚለው “ሱዳን ከሚገኝ ሠላም

ወደ 11 ዞሯል

# ኢ.ህአዴግን በዘር ማጥፋት ወንጀል ለመክሰስ እየተዘጋጀ መሆኑን መኢአድ አስታወቀ

10

# የእነአንዱዓለም አራጌ የመከላከያ ቪ.ዲዮ ማስረጃ ቀረበ

- ፋይሉ ለግንቦት 3/2004 ዓ/ም ተቀጠረ
- የፍትህና ነጋድራስ ጋዜጣ “በሽብርተኝነት” ተጠርጥረው በእስር ላይ የሚገኙት የእነአንዱዓለም አራጌ 24 ተከሳሾች የመከላከያ የቪዲዮ ማስረጃ ባለፈው ረቡዕ ቀርቦ ታይታል፡፡ በእልቱ የታየው አንዱዓለም አራጌ ግንቦት 2003 ዓ/ም አሜሪካን አገር በተደረገው ስብሰባ ላይ ያደረጉት ንግግር እና እስከንድር ነጋ በአንድነት ፓርቲ ተጋብዞ ያደረገው ንግግር ቀረበ ለፍ/ቤቱ ታይቷል፡፡

አቶ አንዱዓለም አራጌ ባደረጉት ንግግር “የሰሜን አፍሪካ አገራት ለአውሮፓ ቅርብ በመሆናቸው የተሻለ የዲሞክራሲ ባህል

ወደ 11 ዞሯል

# “ሞረሽ” የተባለ የ “አማራ አብሮነት” ድርጅት ተቋቋመ

በአማራው ሕዝብ ላይ የሚደረገውን ግድያ፣ግፍ፣ህገ-ወጥ እስራትና፣ቅሚያና ዘረፋ እንዲሁም መብት እጦት ለመከላከል ሞረሽ-የአማራ አብሮነት (Amara Union) የተባለ አስተባባሪ ድርጅት መቋቋሙ ታወቀ፡፡ ድርጅቱ ለፖለቲካ የማይወዳደር እንዲሁም የማይወግን ሆኖ እንደሚሰራ አምባሳደር እምሩ ዘለቀ አስታወቁ፡፡ አምባሳደሩ የአማራው ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት የማያጠራጥር መሆኑን አውስተው “ኢትዮጵያውያን ነን ስንል የለም

ወደ 16 ዞሯል

## አቶ ይባስ አስፋው በአቶ ናትናኤል መኮንን ላይ የሞከሩት ድብደባ በአስረኞች ትብብር ከሸፈ

## ኢትዮጵያ ታላቁን ዓለማቀፍ ሊቅ አጣች

13

# የኦሮሞ ነገር - - - ከገዳ እስከ ገዳዳዉ ኦህዴድ



ሰለሞን ስዩም
era4st@yahoo.com

የኦሮሚያ ጉዳይ-- የኦሮሞ ነገር ቁርጥ ያለ ነገር ላይ የደረሰ አይመስልም፡፡ የታሪክ ተመራማሪዎች ከተረት መሰል ትንተናዎች “የኦሮሞ ኢትዮጵያዊነት” እስከ “ኦሮሚያ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛትነት” ጠርዝ ይዘዋል፡፡ አንዱ ሀቅ ግን በሀገሪቱ ውስጥ ካሉት ብሔር ብሔረሰቦች ሁሉ የቆዳ ስፋት ብልጫ ያለው ክልል ነው፡፡ ኦሮሚያ ከ40 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ያዋሰኗታል፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ እጅግ ወሳኝና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላቸው ካርታ ላይ ያረፈ ነው፡፡

ከዚህ ሁሉ ተፈጥሯዊ መልካም አጋጣሚዎች በኋላም ኦሮሞዎች “ትንንሽ” ከሚባሉ ብሔረሰቦች እኩል በደል ማስተናገዱ ይስማማሉ፡፡ ከዚህ ጭቆና ለመውጣት የኦሮሞ ብሔርተኝነት ሰባት ደረጃዎችን በስከዛሬው አካሄዱ መጓዙ ይነገራል፡፡

ዋና ዋና ደረጃዎች

ኦሮሞዎች ለመረዳጃ ማህበርነት በሚል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ለማዳበር የፈጠሩት “ዕድር” ሜጫና ቱለማ መሆኑ ይነገራል፡፡ ዶ/ር መረራ ጉዲና «መጫ ቱለማ ብሔርተኛ ቢሆንም ለፖለቲካ ስልጣን ግን ፍላጎት አልነበረውም» ይላሉ፡፡ የሜጫና ቱለማ ወርቃማ ዘመን ጀነራል ታደሰ ብሩ ወደ ሊቀ መንበርነት ሲመጡ እንደሆነ ይነገራል፡፡

ሁለተኛው እርከን ቋንቋችን፣ ባህላችን እንዲሁም መሬታችን እያጣን ነው ባሉ የባሌ ገበሬዎች አመፅ ሲጀምሩ የተንፀባረቀ ነበር፡፡ «በመሬታችን ባሪያ አንሆንም» በማለትም ከፍተኛ ሁኔታ ለሽያጭ የዋለውን መሬታቸውን ለማስመለስ የተንቀሳቀሱ ሲሆን የሶማሊያ ኢስላማዊ ሀይሎች በተለያየ መልኩ ድጋፍ አድርገውላቸዋል፡፡ ሶስተኛው ከሜጫና ቱለማ ጀምሮ የነበረው የኦሮሞ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መከፈል ሲሆን በመቀጠል ክፍፍሉ በመኢሶንና በኦነግ መካከል በመደብ ልዩነትና በብሔር ጭቆና መቀዳደም ላይ ከፍተኛ ክፍተት ተፈጠረ፡፡

ኦሮሚያ--ኢትዮሚያና ምንም

ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ አፄ ኃ/ሥላሴ ድረስ የኦሮሚያ ጉዳይ በኢትዮጵያ፣ ኦሮሚያና ኢትዮሚያ መካከል ሲዋልል ነበር፡፡ በሀያኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን የተጀመረዉ አንዱ የኦሮሞ ልሂቃን ጥያቄ «ኦሮሚያ» የምትባል ሀገር መፍጠር ነበር፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነዉ ኦነግ ነዉ፡፡ በዚህ ክፍለ ዘመን የበላይነቱን የያዘዉ አስተዳደር ደግሞ ኦሮሞ የተባለዉን ብሄር እዉቅና ሳይሰጠዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ የመጨፍለቅ ስራ ሲሰራ ነበር የሚሉ የክልሉ ሊሂቃን ቁጥር ቀላል አልነበረም፡፡ በሌላ መልኩ መኢሶን ዉስጥ ተሳታፊ የነበሩት ልሂቃን በታላቋ ኢትዮጵያ ግንባታ ዉስጥ የሰፈዉ ኦሮሞ ትልቅ አስተዋፅኦ መጉላት አለበት የሚሉ ነበሩ፡ ፡ ይህንን ኢትዮጵያና ኦሮሚያን በማዳቀል «ኢትዮሚያ» ማለት ይቻላል፡፡

ጉዲፈቻ-- ሞጋሳ እስከ ጠባብነት

የኦሮሞ የመስፋፋት ታሪክን ላነበበ ሰው የኦህዴድ ካድሬዎች የቀድሞቹ ኦሮሞ ቀጣይ ትውልድ መሆናቸው ያጠራጥራል፡፡ ከቀደምት ቦታቸዉ ወደ ሰሜን፣ ደቡብ ምስራቅና ምዕራብ ባደረጉት መስፋፋት ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ስኬት እንዳጎናፀፋቸው ይነገራል፡፡ የመጀመሪያ የክርስቲያን ደገኞችና የምስራቆቹ ሱልጣን መንግሥታት በርስ በርስ ጦርነት ከተዝለፈለፉ በኋላ መሆኑ ይታወቃል፡ ፡ ሁለተኛ ምክንያት የኦሮሞ ፖለቲካ ምሰሶ የሆነው “ገዳ” በየስምንት ዓመቱ በሚያመጣው የስራ ድርሻ ሽግሽግ የጦርነት ልምድ በተለይም ፈረስን በመጠቀም የሚሰጠው ስልጠና አለው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ምክንያቶች ለዕሁፉ ምሉዕነት ካልሆነ በቀር ዋነኞቹ አይሆኑም፡፡ ሦስተኛው ምክንያት ግን “ኦህዴድ ያአባት አያቱ ልጅ ነው እንዴ?” የሚያሰኝ ነው፡፡ ኦሮሞ በተስፋፋበት ዘመን አንድን ግለሰብ ሲማርክ “ጉድፈቻ” በሚል አሰራር ሙሉ በሙሉ ከህብረተሰቡ የሚቀላቅልበት አሰራር ነበረው፡፡ “ጉድፈቻ” ወደ አማርኛም የተወሰደ ቃል ሲሆን በዘመኑ አንድ የተማረከ ሰው በመምረጥ፣ በመመረጥ እንዲሁም በሌሎች መብቶች ከተወላጅ ኦሮሞዎች ጋር የሚስተካከልበት ዘዴ ነበር፡፡ የዘመኑ ኦሮሞዎች የያዙትን ህብረተሰብ /መንደር/ ደግሞ “ሞጋሳ” በተባለ አሰራር ሙሉ በሙሉ በኦሮሞነት ይወስዱታል፡፡ “ሞጋሳ” ማለት መሰየም /ስያሜ ማለት ሲሆን ልክ እንደ “ጉዲፈቻ” ሁሉ ባለ ሙሉ መብት ማድረግ ነው፡፡

ኤርትራዊው ፕ/ር አስምሮም ለገሰ “Oromo Democracy፡ An Indigenous African Political System” በማለት ባጠኑት ጥናታቸው “ሌሎችን በመቀበል፣ አብሮ በመኖርና በመስራት በአፍሪካ ደረጃ እንኳ አቻ የሌለው ብሔር ነው” ይላሉ፡፡ ኦህዴድ 22ኛ የልደት በዓሉን ለማክበር እጅግ የደከመበት በሚመስለው ፕሮፓጋንዳው ውስጥ በየትንሽ ርቀት የሚሰነቅራቸው አፍራሽና ከመስመር የወጡ የብሔርተኝነት መገለጫዎች ቡድኑ የኢህአዴግ አባል ድርጅት እንኳ አያስመስለውም፡፡ ፕ/ር አስመሮም ተወዳዳሪ በማይገኝላቸው የ“ገዳ” ጥናታቸው “ከማንም ጋር የሚያኖረው መሠረት ያለው ህዝብ” በማለት “Gada፡ Three Approaches to the Study of African Society” በተባለ መፅሐፋቸው ያወሳሉ፡፡ በሌላ መልኩ የኦነግ የቀድሞ የመገንጠል ጥያቄ ከተነሳ “ብሔርተኝነት ከህዝብ ይልቅ ከልሂቃን በኩል ለፖለቲካ ስልጣን የሚራገብ ነው” የሚለው የብሔርተኝነት አንደኛው ሀሊዮት ይገዛዋል፡፡

+Ve መብቶች አሉህ

በድረገጾች ላይ የኦሮሞ ነክ ጉዳዮችን በመተንተን የሚታወቁት ከማል አብዲሳ ኦህዴድ በኦሮሚያ ያለ የህወሓት ክንፍ እንደመሆኑ መጠን «የመሆን መብትን (+ve rights) እንጂ የማድረግ መብት (-ve rights) አይመቸዉም» ይላሉ፡፡ በባህል ልብሶችህ ማጌጥ ፣ በቋንቋ መናገር፣ መጨፈር ትችላለህ፤ ነገር ግን በባህል ልብስህ ላይ ከጠለፍከው ጌጥ እስከ የዘፈኖችህ ይዘት ድረስ ብርቱ ቁጥጥር አለብህ” ይላሉ፡፡ በከማል አብዲሳ አተናተን “መተቸትም ሆነ የተለየ ሀሳብ መያዝ ዋጋ የሚያስከፍልበት አሰራር የኦህዴድ ዋነኛ መገለጫ ነው” ይላሉ፡፡ በኦሮሚያ “መዝረፍ አንደኛው ‘የመሆን’ መብት ነው” የሚሉት ከማል አብዲሳ “ይህ ግን በኢህአዴግ ውስጥ እንደሚተገበረዉ ሁሉ የፖለቲካ መብትህን ይሸረሽራል” ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

የህወሓት “copy paste”

የኦሮሚያን ጉዳይ የሚከታተሉ ምሁራን ክልሉ ዛሬም በቂ አስተዳደራዊ ምላሽ አላገኘም ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ህወሓት የብሔር ጭቆናን ከመደብ ትግል አብልጣ ለማሳየት በነበረው ጉጉት በየብሔሩ ስም ድርጅቶችን “ጠፍጥፎ መስራት” ነበረበት፡፡ የኦሮሚያን ነገር ልዩ የሚያደርገው ደግሞ ይህንን ዘውግ ለረዥም አመታት ሲያቀነቅን የነበረው ኦነግ ሳይግባባ ሌላ ጥገኛ ድርጅት ህወሓት የፈጠረበት ሁኔታ ነው፡፡ ህወሓት የኦህዴድ ልሂቃንን ከጦር ሜዳ ምርኮ ያገኘ በመሆኑ በአካዳሚያዊ ዕውቀትም ሆነ በሞራል ነፃነት ለመጎናፀፍ የማይንቀሳቀሱ መሆኑን ያምናል፡፡ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በከፍተኛ አመራርነት የሰሩ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ ተናጋሪ “በህወሓት አመታዊ ክብረ በዓል ጊዜ እገኛለሁ፡፡ በእጅ የሚሰጠን የህወሓት የዕለቱ ፕሮግራም ‘የክብር እንግዶች . . . ፈንዲሻ ይበተናል፣ አምባሻ ይቆረሳል . . .’ የሚሉ ናቸው” ይላሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የኦህዴድ አመታዊ ክብረ በዓል ላይም “ፈንዲሻ ይበተናል፣ አምባሻ ይቆረሳል የሚል መርሃ ግብር ቅደም ተከተሉን እንኳ ሳይለቅ ይመጣል” የሚሉት እኚህ የድርጅቱ የቀድሞ አመራር “በኦሮሞ ባህል ሳር ይጎዘጎዛል፣ ወይ ዳቦ አሊያም “ሀንጮቴ” ይበላል እንጂ የምን ፈንዲሻ የምን አምባሻ ነው?” ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ አመራሩ “የኦህዴድን የበዛ




ጥገኝነት በዚህ እንኳ ላሳይ ብዬ ነው” ሲሉ ይደመድማሉ፡፡

የኦነግ አስፈላጊነት “አሙኙ መጣልህ”

“በገጠር ከብት ስትነዳ አንዳንዴ ይሰንፉብሃል፤ የእዚያኔ አንድ የሚያስበረግግ ነገር አምጥተህ ታስሮጣቸዋለህ፤ ህወሓት ይህንኑ በማድረግ ኦህዴድን ለማሯሯጥ ይተጋል” ይላሉ፡፡ እኚህ በድርጅቱ የአመራርነት ቦታ የነበሩ ሰዉ፡ ፡ ህወሓት የኦነግን መኖር በጣሙን ይፈልገዋል፡፡ ዋነኛ ጥቅሙም የኦህዴድን ታማኝነትና ታዛዥነት እንዲሁም በተባለው ፍጥነት እንዲጓዝ ማስበርገጊያ መሆኑ ይነገሯል፡፡ ከድርጅቱ የለቀቁ አንድ ሌላ የቀድሞ አመራር “ኦህዴድ ኦነግ የተባሉትን ሰዎች እንዲገርፍ፣ እንዲገድልና እንዲያሳድድ ተደርጓል” ይላሉ፡፡ በዚህም መሠረት “ኦህዴድ የኦነግ መምጣት ለፍርድ መቅረብ መሆኑን ስለሚያውቀዉ ለህወሓት ባሪያ መሆንን ይመርጣል” ሲሉ ይደመድማሉ፡፡

ከዊኪ ልክስ የተለቀቀ መረጃ እንደሚያሳየው አባዱላ በኦሮሚያ ታዋቂነትን ማትረፉ በጀመሩ ሰሞን በአምባሳደር ብርሃኑ ድንቃ የኢትዮጵያ መንግሥት ተወካይ፣ ፕ/ር ኤፍሬም ይስሃቅ ሽማግሌነትና እንዲሁም የኖርዌን ቤተክርስቲያን የልማት ተራድኦ በመሆን ኦነግን ለመሸምገል ተሞክሯል፡፡ በዚያው ሰሞን የኦነግ የረዥም ዘመን ስትራቴጂ ነዳፊ የነበሩት አባቢያ ነገዎ ኢትዮጵያ መጥተው ያለምንም ችግር መመለሳቸው ታውቋል፡፡ ጉዳዩን የሰሙት የወቅቱ የክልሉ ፕሬዝዳንት አባዱላ ገመዳ ክፉኛ በመደንገጣቸው የህወሓት የ “አሙኙ መጣልህ” ታክቲክ መሳካቱን ተንታኞች ይናገራሉ፡፡ በወቅቱ ጉዳዩ ከደረሳቸው የኦህዴድ አመራሮች ግርማ ብሩ ብቻ ሀሳቡን መቀበላቸው ይነገራል፡፡

«ጥቁር ኦሮሞዎች» እንደ ጥቁር አማራዎች

ተስፋዬ ገብረአብ በብአዴን ውስጥ አመራር ሆነው በዘር ግንዳቸው አማራ ያልሆኑትን “ጥቁር አማሮች” መሆናቸውን ያብራራል፡፡ ተስፋዬ “ጥቁር” የሚለው ቃል አመጣጣቸው እንደ “ጥቁር ገበያ የተጭበረበረ መሆኑን ለማሳየት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አስቀምጧል፡፡ የተስፋዬ ዋነኞቹ ምሳሌዎች ከቤንቺ ማጂ የተገኘው ተፈራ ዋልዋና ኤርትራውያን ቤተሰቦች የወለዱት አቶ በረከት ስምኦን ናቸው፡፡ አቶ ተፈራ ዋልዋን ግን ዉስጠ አዋቂዎች «በናቱ ሲዳማ ባባቱ አማራ የሀገረ ማሪያም ተወላጅ ነዉ» ይላሉ፡፡እንደዚህ ሁሉ የኦህዴድን ፖለቲካ ክፍትና ነፃ ውይይት የሞላበት እንዳይሆን ያደረገው “በጥቁር ኦሮሞነት” የሚፈረጁ አመራሮቹ ባላቸው የበታችነት ቀውስ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ለክልሉ መንግሥት ቅርብ ነኝ ያሉ አስተያየት ሰጪ አብዛኛዎቹ አመራሮች በቁርጠኝነት ለመስራት እንኳ ቢሞክሩ ባላቸው የኋላ የዘር ግንድ አሸማቃቂ ነገር እንደሚገጥማቸው ይነገራሉ፡፡

አስተያየት ሰጪው በዚህ ረገድ “ከኢብራሂም መልካ በኋላ ሙሉ የኦሮሞ ውክልና ያለው አመራር አላውቅም” ይላሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት እንኳ በዚህ ሽምቀቆ የተያዙትን ሲዘረዝሩ “እሸቱ ደሴ የፍቼ ቆለኛ ነው፤ ዘላለም ጀማነህና አበራ ሀይሉ ጎደሜ ናቸው ይባላሉ፤ አስቴር ማሞ የጎንደሬው ተወላጅ እና የደምቢው ሀገር ገዥ የበላንባራስ በላይነህ የልጅ ልጅ፤ ኩማ በቀድሞ ስሙ ታዬ ተ/ማሪያም ነው፡፡ የጎንደር ተወላጅ አባቱ ቄስ ናቸው” ሲል የዘር ሽኩቻዉን ለፍኖተ ነፃነት አጋርተዋል፡፡ ኩማን በተመለከተ ፍኖተ ነፃነት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ጠይቃ “ኩማ የጎንደር ተወላጅ አባት የለውም፤ አባቱ ግን ከጎንደር በመጡ ቄስ ተክለ ሀይማኖት ተምረው ከቀሰሱ በኋላ ተ/ማሪያም ተብለዋል፡፡ ለዚህም ነው ኩማ አንዳንዴ የተክለ ሃይማኖት ልጅ ነው የሚባለው” ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ታዛቢዎች ከዚህ ውጪም ህወሓት በክልሉ ሴራ አለው ይላሉ፡፡ በተለይ እንዲሾሙ ድጋፉ የሚሰጣቸው ሰዎች የኋላ ታሪካቸው የተበላሸ መሆናቸው እንደሚተኮርበት ያወሳሉ፡ ፡ ይህም አሳሪ የሆነ መንገድ ነው፡፡ የማስፈፀም ብቃት እንኳ ቢኖራቸዉ ታሪካቸዉ የሚያነሳዉን መጥፎ አቧራ በመፍራት ይቆጠባሉ፡፡

የመጋረጃ ጀርባ ፕሬዝዴንቶች

«ኦህዴድ አንድም ጊዜ ከህወሓት ውጭ የሆነበት አጋጣሚ የለም» የሚሉት የክልሉ ፖለቲካ ተከታታዮች ህወሓት የመጋረጃ ጀርባ ፕሬዘዳንቶችን እስከ ማስቀመጥ ሀይል እንዳለዉ ይናገራሉ፡፡ ይህ በደቡብም የሚንፀባረቅ ነበር፡፡ በክልሉ የአንድ ወቅት የመጋረጃ ጀርባ የነበሩት አቶ ቢተው በላይ በአብዛኛው የፖለቲካ ሰዎች ዘንድ ይታወሳሉ፡ ፡

ኦሮሚያን በተመለከተ እስካሁን ሁለት ግልፅ የወጡ የመጋረጃ ጀርባ ፕሬዚዳንቶች የነበሩ እንደ ሆነ የሚናገር ነው፡፡ ቀደም ብሎ ክልሉን ከኋላ ሆነው በማሽከርከር የሚታወቁት ሰለሞን ተስፋዬ (ሰለሞን ጢሞ) እንደ ነበሩ የክልሉን ፖለቲካ የሚከታተሉ ያስታውሳሉ፡፡ ነገር ግን ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በ “ዳንዲ የነጋሶ መንገድ” የግል ታሪክ መፅሐፍ ውስጥ ለእገዛ የተቀመጡና ለኦህዴድ መጠናከር የሚተጉ ሰው እንደነበሩ ይከራከራሉ፡፡ ከሰለሞን ጢሞ በኋላ አሁን ደግሞ የጠ/ሚ/ሩ ፅፈት ቤት ሰው ገ/ተንሳይ ወ/ተንሳይ በኦሮሚያ የመጋረጃ ጀርባ ፕሬዚዴንት እንደሆኑ ይነገራል፡ ፡ ይህ እንግዲህ በጉያ ስር ያለውን ለማየት እንጂ አጠቃላይ የህወሓትን ቁጥጥር ለማሳየት አይመጥንም፡፡ ህወሓት ፖለቲካዉን ለመቆጣጠር ቆንጆ ሴት በማስቀመጥ ሁሉ ይጠቀማል፡፡

የኦህዴድ “ነፃነት”

የኦህዴድ ከፍተኛ አመራር የነበሩ አስተያየት ሰጪ የኦሮሞ ህዝብ ትግል ለድንበሩ ነፃነት፣ ለባህሉ መከበርና በቋንቋ የመናገር መብቱን ለማስከበር መታገሉን ጠቁመው፤ አህዴድ ነፃ ቢሆን፣ ፌዴራሊዝሙ እውነተኛ ቢሆን፣ በህገ መንግሥቱ የተቀመጠው የፊንፊኔና የድሬደዋ ጉዳይ በተፈታ ነበር፡፡ ኦህዴድ ከ21 ዓመታት በኋላም የኦሮሚያ ጥቅምን በሚመለከት ህገ መንግሥቱ ያስቀመጠውን የ«ወደፊት በህግ ይወሰናል» እንጥልጥል አልተቋጨም፡፡ አስተያየት ሰጪዋ እንደሚሉት አዲስ አበባ በኦሮሚያ መሬት ላይ ከማረፏም በላይ 5ቱም ኬላዎች በኦሮሚያ ውስጥ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ “ይባስ ግን” ይላሉ አስተያየት ሰጪዋ “የፌዴራል መንግሥት ፖሊስ ኬላዎቹን እንዲቆጣጠር በሚል የኦሮሚያ ፖሊስ ተባሯል፡፡ በተጨማሪም አዲስ አበባ ዉሃ፣ የቁም ከብትና ቀረጥ ከኦሮሚያ ማግኘቷን ያወሳሉ፡፡

እንደ አብዛኛዎቹ አስተያየት ሰጪዎች የኦህዴድ ነፃነት ሙስና ነው፡፡ ሙስና የክልሉ ህጋዊ ስርዓት እስኪመስል ድረስ እየተሰራበት ነው፡፡ በአንድ ወቅት የኦህዴድ ጽ/ቤት ኃላፊ የነበረው ጫላ ወርዶፋ በሙስና ተከሶ ታስሮ ነበር፡ ፡ ከስራም ታግዶ ነበር፡፡ ከየት መጣ ሳይባላ ብዙ ገንዘብ በማንቀሳቀስ የሙስና ተራራ በሚሰራበት የኦሮሚያ መንገድ ኮንስትራክሽንና ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊነት መመደቡን ታዛቢዎች ይናገራሉ፡፡

አባዱላ የፓርቲው ተፈጥሮ በፈቀደላቸው መጠን ሞስነዋል የሚሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ የተለያዩ ንብረቶችንም “አፍርተዋል”፡፡ ነገር ግን ከቁጥጥር ውጭ እየወጣ በሄደው አካሄዳቸው ተገምግመው ቦሌ አከባቢ የገነቡትን ቤት ለድርጅታቸው እንዲሰጡ ተደርጎ ተደምድሟል፡፡ የመጨረሻ እርምጃ የነበረው አፈ ጉባኤ እንዲሆኑ ማድረግ ነበር፡፡

ወደ 12 ፡ገጽ

# ልማታዊ ጋዜጠኝነት እንዴት ነው?



ግርማ ሠይፉ ማሩ
girmaseifu32@yahoo.com

ኢቴቪ መረጃ የመስጠት ግዴታውን ለህዝብ ጥቅም ሲባል መገደድ ይኖርበታል!!

«በሱማሊ ክልል ተፈጥሮ የነበረውን ግጭት ለማስወገድ መንግስት ባደረገው ጥረት ስምምነት ላይ መደረሱ ተገለፀ» የሚል ዜና በምስል ተደግፎ ከፍተኛ ሹማምንት በተገኙበት የእርቅና የሰላም ኮንፈረንስ መደረጉን ሰማን፤ ዜናው በዕውነት ጥሩ የሚባል ነው፡፡ ለነገሩ መቼ ነበር ይህ ግጭት የተፈጠረው፣ በግጭቱ ምን ያህል ሰው እና ሃብት ላይ ጉዳት ደረሰባቸው? የሚሉት ግን ያልተገለጹ ነገር ግን አስፈላጊ መረጃዎች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ከእርቅ መውረዱ ብቻ ሳይሆን ካስከተለው አላስፈላጊ ጉዳትም ትምህርት ሊወሰድ ይችል እንደ ነበር ለማወቅ ነብይ መሆን አያስፈልግም፡፡ በሌሎች አካባቢዎች ተመሳሳይ ግጭት አለ ወይስ የለም? ይህ በእንዲ እንዳለ ኮንፍረንሱ ለምን በክልሉ ውስጥ አልተካሄደም? አሁንም ያለለቀ ጉዳይ አለ ወይ? ብሎ ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን በእንጥልጥል መተው ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ያልበረደ ግጭት አለ ብለን ግምት ካስቀመጥን፤ የኢቲቪ የእናትና አባት ልጅ የሆነው ጋዜጣ በገፅ ሶስት ላይ በአሸባሪነት የማይጠይቀን ይመስላችኋል? ቢሆንም ግድ የለም ነው መልሳችን፡፡ ፍርሃትን ለፈሩ ማስፈራሪያ የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ የአዲስ ዘመኑ የነፃ መድረክ ብዕረኛ ደፋር ከሆንህ ህዝብ እንዲፈርደን ትክክለኛ ስምና ፎቶ በያዘ መጣጥፍ እንገናኝ፡፡ ያለበለዚያ ፈሪ ለማስፈራራት ልብ ከየት ያመጣል፡፡

የጉራ ፈርዳ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ግልፅ የሆነ የህገ መንግሰት ድንጋጌ በመጣስ ከሚኖሩበት ተባረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህገመንግሰት ለዜጎች ብቻ ሳይሆን በህጋዊ መንገድ ሀገር ውስጥ ለገባ የውጭ ዜጋም መብት ይሰጣል፡፡ ምን ዋጋ አለው በወረቀት ላይ ሆኖ አረፈው እንጂ፡፡ ኢቴቪ ይህንን አልሰማም ይሆናል፤ ይህ ጉዳይ ግን በኤርትራ መንግስት ተፈፅሞ ቢሆን ኖሮ በልዩ ዘጋባ ሁሉ ሊቀርብ ይችል ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ መንግስት ዘላቂ እልባት ካለገኘለት የሚያመረቅዝ መሆኑን ለማወቅ የተለየ ጥናት አያስፈልግም፡፡ በደቡብ ክልል አማርኛ ተናጋሪ ዜጎች የተባረሩት በአማርኛ በተፃፈ ደብዳቤ ነው፡፡ ይህንን ተከትሎ ሌሎች ክልሎች የመልስ ምት ብለው እርምጃ ቢወስዱ የደቡብ ክልል ምን ይሆናል ምላሹ? ለምሳሌ ከደቡብ ሄደው በቤኒሻንጉል የሰፈሩ አሉ፤ የአዲስ አበባ ክልል አዲስ መጤ ናችሁ ብሎ ደቡቦችን ቢያስወጣ ምን ምላሽ ይኖረናል ጎበዝ? እየተስተዋለ ቢሆን ጥሩ ነው፡፡

የጉራ ፈርዳ ነዋሪዎችን አስመልክቶ የደቡብ ክልል ርዕስ መስተዳድር ዘግይተዉም ቢሆን በኢቲቪ ቀርበው በጥሬ ሃቅ ላይ ውሸት አለው ብለዋል፤ ልክ ናቸው፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለቱም ልክ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ወይ መኢአድ ፅ/ቤት ተሰብሰበው ወደ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የሄዱት ሰዎች ከማርስ ነው የመጡት (ውሸታቸውን ነው ከደቡብ ክልል ከጉራ ፈርዳ መጣን ማለታቸው) ያለበለዚያ ግን ውሸት ነው ያሉን ባለስልጣን እየዋሹን ነው፡፡ ግን ለምን? ይህ ዜና በዕውነት የአማራጭ ቴሌቪዥን ፍላጎቴን የመጨረሻ ነው ያደረሰው፡፡ አፈርኩ እንዲህ ባሉ ዜናዎች፡፡ ‹‹ኢቲቪን ማመን ዘግቶ ነው›› ብሎዋል አንድ የማህበረሰብ ድዕረ ገፅ አፍቃሪ፡፡

በነገራችን ላይ ብሮድካስት ባለሥልጣን በፈቃድ አሰጣጥ ከእቅድ በታች መሆኑን በዕድገትና ትራንሰፎርሜሽን የአንድ ዓመት አፈፃፀም ግምገማ ላይ ተገዎዋል፡፡ ምክንያቱ ግን የሚያመለክት ባለመኖሩ ነው የሚል ነው፡፡ ፋና ብሮድካስት እንዳመለከተው ሰምቼ ነበር፡፡ ለፋናም ቢሆን ይሰጥልን፡፡ የሚገርም ምክንያት በመሆኑ ለማስገረም ነው እዚህ ላይ ማንሳቴ፡፡

የፕሬዚዳንታችንን ጉዳይ ምን ደረሰ እንበል? ከኢቲቪ የተሻለ መረጃ ያለ አይመስለኝም፡፡ ለነገሩ አዋጆች በምክር ቤት እየፀደቁ ቢሆንም ማን እንደሚፈርመው አይታወቅም፡፡ ለነገሩ በቅርብ ለሚያውቁዋቸው አልጋ ከመያዛቸውም በፊት በቅጡ ይፈርሙ ነበር የሚል ዕምነት ስለሌለ በቅርቡ ስራ ይጀምራል ተብሎ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በተነገረው ኤሌክትሮኒክ ፊርማ ስርዓት መጠቅም ጀምረው ካልሆነ እንዴት ይሆናል፡፡ የፕሬዝዳንቱ ጤና ያሳስበናል!!

ፕሬዝዳንቱ ከሚጠበቅባቸው ስራ አንዱ የሆነው የስራ ጊዜያቸውን አጠናቀው የሚሸኙ እና አዲስ የተሾሙ አምባሳደሮችን መቀበልና መሸኘት እንዴት እየሆኑ እንደሆነ የሚታወቅ ባይሆንም የሹመት ደብዳቤያቸውን ለማቅረብ ይጠብቁ ከነበሩት የእንግሊዝ አምባሳደር ጨምሮ ሌሎቹ አምባሳደሮች እንዴት እንደሆኑ አይታወቅም፡፡ ለመሆኑ ፕሬዝዳንቱ በህመም ምክንያት ተግባሩን መወጣት ካልቻ ምንድነው ያለው አማራጭ? ኢህአዴግ ለዚህ መላ ያጣል ብዬ አላሰብም፡፡ ግን ለስራ ቅልጥፍናም ቢሆን አንድ ብትሉን ጥሩ ነው፡፡ ለነገሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደርበው ቢይዙትና ለወደፊቱም በዚያው እንዲቀጥል ቢሆን ምን አለበት? የህገመንግስት ድንጋጌ ከሆነ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በሌላ ሁኔታ ከተወሰነ ችግር እንደሌለው ከልምድ ተረድተናል፡፡

ለመምህራን የተደረገው ጭማሪ የመምህራንን ጥቅም ያስጠበቀ እንደሆነ ይህንንም የመምህራን ማህበር ገልጿዋል ተብለን በማግስቱ መምህራን ስድብ ነው ብለው እስከ ትምህርት ማቆም ደረሱ፡፡ ውሸቱን የነገረን ልማታዊው ኢቲቪ እውነቱን ግን ሊነግረን አልቻለም፡፡ እውነቱን ነው በአንድ ትምህርት ቤት የተደረገን የስራ ማቆም አድማ መዘገብ በመላው ሀገሪቱ አድማው እንዲስፋ መረጃ መስጠት ነው፡፡ የኢራን መምህራን ይህንን ዓይነት ድርጊት አድርገው አንድ የዜና አውታር ቢዘግበው ኢቲቪ ተቀብሎ እንደሚያስተጋባ አትጠራጠሩ፡፡ ኢትዮጵያውያን የሚያስፈልጋቸው የኢራን መምህራን ማህበር እንጂ የኢትዮጵያውያን መምህራን ጉዳይ አይደለም እያለን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

ኢትዮጵያውያን የሚደርስብን በደል አንድ ብቻ አይደለም - በሀገራችን ሚዲያ በቂ መረጃ እንዳናገኝ መገለል ብቻ አይደለም፡፡ በውጭ ሚዲያዎችም እዚህ ግባ የሚባል የሚዲያ ሽፋን የላትም - የበለጠ የሚያስገርመው ኢትዮጵያ በአለም ከፍተኛ ዲፕሎማቶች የሚኖሩባት ሀገር ብትሆንም ለዜናም ሆነ ሌሎች ዓለም አቀፍ ዘገባዎች የተከፈተች አይደለችም፡፡ ይህም ጭምር ነው አማራጭ የቴሌቪዥን አምሮቴን የሚያንረው፡፡

ኢቲቪ ሌሎችም ያልሰማናቸው (እንዳልሰማ በመሆን) ያላሰማን ብዙ ነገሮች እንዳሉ መጠርጠር ይኖርብናል፡፡ ልማታዊነታቸው እስኪረጋገጥ የሚጠበቁ ናቸው ብለን ልንወስዳቸው እንችላለን፡፡ ይዋል ይደር እንጂ ማድረግ ሲገባው ባለደረገው፤ እያወቀ መረጃ በማሳሳት ለፈፀማቸው ስህተቶች ተጠያቂ እንደሚሆን ልብ ማለት ተገቢ ነው፡፡ ለጊዜው ውጤቱ ምንም ይሁን ምን አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ይህንን ግዴታውን እንዲወጣ በፍትህ አደባባይ አቅርቦታል፡፡ ሌሎችም ይህንን ፈለግ ተከትለው ግዴታውን እንዲወጣ ማስገደድ ይኖርብናል፡፡

# አማራውን የማጥፋት ዘመቻ መቼ ይሆን የሚያቆመው?

መ/ር ዘካርያስ የማነብርሃን
(የአንድነት ፓርቲ ብ/ም/ቤት ሰብሳቢ)
Moresh2004@yahoo.com

በአማራው ላይ ጥቃት የተጀመረው ዛሬ ሳይሆን ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ጀምሮ እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል፡፡ እንዲጠፋ የተወሰነበት የአማራው ተወላጅ እንደ ኢትዮጵያ ጣላቶች አባባል በራሱና በታሪኩ የሚተማመን፣አትንኩኝ ባይ፣ለነፃነቱ ለህልውናው፣ ለሃይማኖቱና ለሐገሩ ዳርድንበር ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር ሟች በመሆኑ ነው ለማያባራ ጥቃት የተዳረገው፡፡ የሕወሓት መሪዎች ከበረሃ ጀምረው በአማራ ሕዝብ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲያንፀባርቁ መቆየታቸውን እናውቃለን፡፡

በትግሉ ወቅትም ሆነ መንግሥትም ከሆኑ በኋላ በግልፅና በስውር ከትግል አጋሮቻቸው ሻዕቢያ እና ኦነግ ጋር በመሆን ጥቃት ሲያካሂዱበት እንደነበር የትላንት ትዝታችን ነው፡፡

ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ አማራውን “ነፍጠኛ” በማለት ከሌላው ጎሣ ጋር ተፋቅሮ፣ተጋብቶ፣ተዋልዶና ተዋህዶ ከኖረበት ቀዬው በግፍ ሲያባርሩት እንደነበር ከሞት የተረፉት ተፈናቃዮች ምስክር ናቸው፡፡ በተለይ በሽግግሩ ዘመን በአማራው ላይ የተፈፀመው ጭፍጨፋ ታሪክ ምንጊዜም ሲያስታውሰው ይኖራል፡፡ ጨፍጫፊዎቹ በወቅቱ ለፍርድ ባለመቅረባቸው ዛሬም ከ20 ዓመት በኋላ በዴሞክራሲ ስም እያፈናቀሉት ይገኛሉ፡፡ አማራውን ለማፈናቀል የሚሰጡት የሃሰት ሽፋን “መሬት በመያዝና መሬት በመሸጥ፣ በመደለል የተሰማሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ‹‹መሬት ለማስመለስ ነው›› የሚል የሀሰት ካባ ደርበው እንደልማዳቸው አማራውን ከቀዬው በአዲስ መልክ ማፈናቀሉን ተያይዘውታል፡፡ ነገሮች የተለወጡ ይምሰሉ እንጂ ያው ናቸው፡፡

ባንድ ወቅት ጠ/ሚኒስትር መለስ “የአማራውን ሕዝብ እንዳያንሰራራ አድርገን አዳክመነዋል፡፡ እስክስታውንና ተረቱን ይዞ ይኑር” ማለታቸው አይዘነጋም፡፡ ይህንኑ የአለቃቸውን ቃል የሚያውቁት የኢትዮጵያ ጦር መሪ የሆኑት ጀኔራል ሳሞራ የኑስ ነሐሴ 15 ቀን 2002 ዓ.ም በአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አክስዮን ባለድርሻ በመሆናቸው በስብሰባው ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር “ይህንን ባንክ ያቋቋምነው'ኮ በታጋዮች የሕይወት መስዋዕትነት በተከፈለ አካላቸውን ባጡ በትግራይ ልጆች ደም እኮ ነው፡፡ ቀደም ሲል የተደረገው ምርጫ ውድቅ የሆነበትን ቃለ-ጉባዔ እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ፡፡ ደርግን ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለን ከሥልጣኑ አውርደነዋል፡፡ አማራንም ዳግም እንዳያንሰራራ አድርገን አጥፍተነዋል፡፡” ማለታቸውን በፅናት ጋዜጣ መስከረም 29 ቀን 2003 ዓ.ም አንብበናል፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያ በአማራው ላይ የደረሰው ጥቃት የጀኔራሉ ምት አካል ይሆን? የአማራውን ተወላጅ በአርሲ በበደኖ፣በአርባጉጉ በአረካ በግፍ የጨፈጨፉትና ያስጨፈጨፉት ለፍርድ ባለመቅረባቸው ታሪክ እራሱን ይደግማል እንዲሉ ሰሞኑን በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ፕሬዘዳንት በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ትዕዛዝ ተፈርሞ በወጣው ደብዳቤ በሺዎች የሚቆጠሩ የዓማራው ተወላጆች አካባቢውን ለቀው እየተሰደዱ ይገኛሉ፡፡

መሰደድ ብቻ ሳይሆን በግዳጅ ከቀያቸው እንዲፈናቀሉ የተደረጉት ዜጐቻችን ሰቆቃና ግፍ እየተፈፀመባቸው መሆኑን ከራሳቸው አንደበት በልዩ ልዩ መገናኛ ብዙሃን ሰሞኑን እያዳመጥን እንገኛለን፡፡ ቤት ንብረታቸው እንዳለ በእሳት ይቃጠልባቸዋል፤ለዓመታት ያፈሩትን ሀብትና የእርሻ ማሳ እንዲሁ ጥለው ይሰደዳሉ፡፡ ይህም አልበቃ ብሎ ድብደባ እየተፈፀመባቸው፣ በጦር እስከመወጋትና መቁሰል ድረስ መድረሳቸውንም ብሎም በድብደባው የተነሳ ህሊናውን ስቶ ከተጫነበት መኪና ላይ ወድቆ ህይወቱ ያለፈ በጉራ ፈርዳ ወረዳ አዲስ ዓለም ማርያም መኖሩን ጋዜጦች ዘግበውታል፡፡ ግፍ የተፈፀመባቸው የአማራው ተወላጆች በVOA ሰሞኑን ሲናገሩ እንደ ተደመጠው 20 ሺ በላይ አባወራዎች፣ሴቶች፣አቅመደካሞች፣ህፃናቶች የተሰደዱ መሆኑን ገልፀው በአጠቃላይ ከ80 ሺ ያላነሱ የአማራ ተወላጆች “የመሬት ማስመለስ መተማመኛ ቅፅ” ሞልተው አንድ ላይ ተሰብስበው ግር ብለው እንዳይወጡ ትዕዛዝ በመተላለፉ በየተራ ምንም ዓይነት ንብረት ሳይዙ ለመውጣት ተራቸውን በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን ገልፀውልናል፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ‹‹የህገ-መንግሥቱ ብቸኛ የበላይ ጠባቂ ነኝ›› የሚለው የኢህአዴግ መንግሥት ዝም ማለቱ “እንደተመኘኋት አገኘኋት” አስመስሎበታል፡፡ “የእኔ ጥፋት አማራ ሆኜ መፈጠሬ ነው” ያሉት እኛ በሽብር ወንጀል ተወንጅለው የተፈረደባቸው የቀድሞው የጦር መኮንን ብ/ዴኤራል ተፈራ ማሞ እንዲሁም በወህኒ የተወረወሩት የፖለቲካና የህሊና እስረኞች አማራ ወይም ኦሮሞ በመሆናቸው ብቻ የታሰሩ ዜጐች መሆናቸውን የሰሞኑ የማዕከላዊው መንግሥት ዝምታ ያሳብቅበታል፡፡ በመሆኑም ከ56 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩባት ደቡብ የሀገራችን ክልል አማራውን ብቻ ለይቶ ማስወጣቱ የአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ወይም የካድሬው የተሳሳተ ውሳኔ ሳይሆን የፌደራል መንግሥቱ እጅ እንዳለበት ዝምታው እራሱ በግልፅ ይናገራል፡፡

አዎ! አማራውን ከፌደራል መንግሥት ስልጣን የማራቁ ረቂቅ ሴራ ተሳክቷል፡፡ ሆኖም ግን አማራውንና ኦሮሞውን በማጋጨት ዕድሜያቸውን ለማራዘም ያሴሩት ሴራ ሲከሽፍባቸው ዛሬ ደግሞ ተጋብቶ፣ ተዋልዶ፣ ተከባብሮና ተስማምቶ በሠላም የሚኖረውን የደቡብ ኢትዮጵያ ነዋሪዎችን ሠላም ማደፍረስ ወቅታዊውን የመምህራን ጥያቄ የሕዝብ የኑሮ ውድነት የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብት መከበር ጥያቄ አቅጣጫ ለማስቀየስ የተጠቀሙበት ዕኩይ ተግባር መሆኑ ምንም አያጠራጥርም፡፡

የህዳሴውን ግድብ በጭንብልነት በመጠቀም የሕዝብን እሮሮ ለማዳፈን የተሞከረው አደንቋሪ ጩኸት አልሰራ ሲል ሕዝብን ከሕዝብ ጋር በማጋጨት ፋታ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት ታሪክና ትውልድ ይቅር የማይሉት አስነዋሪ ወንጀል ነው ስለሆነም በአስቸኳይ መቆም አለበት፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ መሬት ኢትዮጵያዊው ተነፍጎት በአንድ ኪሎ ሙዝ ዋጋ መሬታችን ለረጅም ዓመት በኪራይ ስም ለውጪ ዜጐች እየተቸበቸበ መሆኑን ተገንዝበን ይህን ለማስቆም በጋራ መነሳት እንጂ መከፋፈል የለብንም፡፡


ዛሬም እንደ ትላንቱ የከፋፋይ ገዥዎቻችንን ሴራ አክሽፈን ልናሳፈራቸው ይገባል፡፡

በሕዝብ ታማኝነት ያላቸው እውነተኛ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰሞኑን በደቡብ ኢትዮጵያ እየተፈፀመ ያለውን አስነዋሪ ድርጊት በማውገዝ የመሪነት ሚናችሁንበጋራልትወጡ ይገባል፡፡ በተለይም አንድነት/መድረክ ባላችሁ የአባል ድርጅቶች ሰፊ መዋቅር ተጠቅማችሁ በአንድ ብሔር ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ ያለማጋለጣችሁ እና በግልፅ እስከ አሁን ድረስ ያለማውገዛችሁ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ አሁንም አልረፈደም፡፡ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ህብረ-ብሔር ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን እቦታው ድረስ ቡድን በአስቸኳይ በመላክ እንዲሁም የዘረጋውን ድርጅታዊ መዋቅር በመጠቀም ይህንን አሳፋሪ የሰብዓዊ መብት ረገጣ በአስቸኳይ እንዲቆም የመሪነት ሚናውን ነገ ሳይሆን ዛሬ መፈፀም ይጠበቅበታል፡፡ የመድረክ አባል ድርጅቶች በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ በዋነኛነት የምትንቀሳቀሱ ፓርቲዎች የተደገሰው ሴራ እንዲከሽፍ ኃላፊነቱን ወስዳችሁ ድርሻችሁን ልትጫወቱ ይገባል፡፡

እንዲጠፋ ከተወሰነበት የአማራው ሕዝብ ጎን በመቆም የተመዘዘበትን የጥፋት ሰይፍ ወደ አፎቱ እንዲገባ ሁላችንም የዜግነት ድርሻችንን በመወጣት የእንቁጣጣሹ በግ ሲታረድ የመስቀሉ በግ ይስቃል ከተባለው ዓይነት ጥቃት እንድንድን በጋራ እንነሳ በማለት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአክብሮት ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

ኢትዮጵያን አምላክ ይጠብቃት!!

# ርዕሰ አንቀፅ




# ሀሳባቸውን በመገናኛ ብዙኃን በነፃነት የሚገልፁ ዜጎች ላይ የተከፈተው ዘመቻ ሊገታ ይገባል

ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ ኢህአዴግ ማርሽ እንደቀየረ ይታወቃል፡፡ ይሄም ማርሽ ቅየራ በግልፅ እንደታየው ከጭላንጭል ዴሞክራሲ ወደ ለየለት የአምባገነንነት ስርዓት፤ ከመድብለ ፓርቲ ወደ አንድ ፓርቲ የአፈና ነፃ ሚዲያን ወደ ማይፈለግ ስርዓትነት ተሸጋግሯል፡፡ እንደዚህ አይነቱን የማይጠቅም አክሮባት (U-Tern) መስራት እነ አቶ በረከት "ከናዳ የማምለጥ ሩጫ" እያሉ ይመፃደቁበት እንጂ ነገሩ ወዲህ ነው፡፡ እውነትም ሩጫው ፓርቲያቸው የገቡትን ቃል ባለመፈፀማቸው ከተነሳባቸው የህዝብ ቁጣ ለማምለጥ ነበር፡፡ ሩጫቸው ጠንካራ ስራ ሰርተው ከካናዳ ለማምለጥ ብቻ ሳይሆን ጭላንጭሉን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት፣ ብልጭ ያለውን መድብለ ፓርቲ፣ እየተንገዳገደ ያለውን ነፃ ፕሬስና በጥንካሬ ለሀገራቸው እየሰሩ ያሉ ተቃዋሚዎችን የማጥፋት ዘመቻ ነው፡፡ ሩጫቸው የአንድ ፓርቲን የበላይነት በግድ የማሸከም ነው፡፡ ውድድር የሚባለውን የማጥፋት ነው፡፡ ከ1997 ዓ.ም በኋላ ገዥው ፓርቲ እየተከተለ ያለው አቅጣጫ ጠቅለል ተደርጐ ሲታይ ከላይ ከገለፅናቸው ክብ መስመሮች የሚወጣ አይደለም፡፡ ዋና ግቡም በውድም ሆነ በግድ ጠቅልሎ የመግዛት ነው፡፡

የኢህአዴግን ባህሪ ጠንቅቀን እናውቃለን የሚሉ ልሂቃን በተደጋጋሚ እንደገለፁት ሲጀመርም ፓርቲው ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አልታገለም፤ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት እንዲረጋገጥ አልታገለም፡፡ የታገለው ለስልጣንና ለስልጣን ብቻ ነው ይላሉ፡፡ ኢህአዴግና አመራሩ ገና ወደ ስልጣን ሳይመጡ የአልባኒያ ኮሚኒዝም ተከታይና አቀንቃኝ ነበሩ፡፡ በቀላሉ የማይፋቅ የኮሚኒስት አስተሳሰብ ባለቤት የሆኑት የገዥው ፓርቲ ባለስልጣናት የዓለም ሕዝብ ድጋፉን የቸረው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከጉሮሮአቸው የሚወርድላቸው አልሆነም፡፡ አሁን እያየን ያለነው አፈናም የዚህ ውጤት ነው፡፡

የትግራይን ነፃ ሪፐብሊክ ለመመስረት ተብሎ የተጀመረው ትግል የመሐል አገሩን ማዕከላዊ መንግስት በመቆጣጠር ሲጠናቀቅ "ነፃ አውጭ ነኝ" የሚለው ኢህአዴግ ሁለት መንታ መንገድ ላይ ቆመ፡፡ አንደኛው ሲጠመቁበት የኖሩትን የፈራረሰው የሶቪየት ህብረቱ ሶሻሊዝም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በኋላ የበላይነቱን እየተቆናጠጠ ያለው ካፒታሊዝም ነው፡፡

ይሄው በልዕለ ሃያሏ አሜሪካ የሚመራው ካፒታሊዝም ወደ በትረ ስልጣኑ ለመጣው ነፃ አውጭው ንጉስ ዶላርና አልዋጥላቸው ብሎ እየተናነቃቸው ያለውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና ሰብዓዊ መብት መጠበቅ የሚሉትን ቀላቅሎ ሰጣቸው፡፡ ስለዚህ የአልባኒያ ኮሚኒዝም ተከታይ የነበሩት ኮሚኒስት ታጋዮች በአንዴ ማልያ ቀየሩና "ዴሞክራት" የሚል አዲስ ማልያ ለበሱ፡፡ ሶሻሊስትነቱ መሳቢያ ውስጥ ተከተተ፡፡ ለይስሙላ የዴሞክራሲ ተቋማት የሚባሉት ለኮፍ፣ ለኮፍ ተደረጉ፡፡

"ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ" እንደሚባለው መሆኑ አልተገለጠለትም እንጅ! "ዴሞክራት" የሚለው ማልያ ለይስሙላ እንደተለበሰ ልብ ያላለው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ሀገሩን የምር ዴሞክራሲያዊት ሊያደርግ ተነቃነቀ፡፡ በ1997 ዓ.ም የታየውም ይሄው እውነተኛ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ፍላጐት ነው፡፡ ከላይ እንደገለፅነው "ብትደርሷት አፍንጫችሁን ላሷት!" የተባለውና ወደ ስውር ዘመቻ የተገባው ሀቀኛ ተቃዋሚዎችና በፅናት እየሰሩ ያሉ አንዳንድ ነፃ ጋዜጦች የገዥው ፓርቲ መደበኛ ጠላት ተደርገው የተወሰዱት፤ ኢህአዴግም አውራ ፓርቲ እንደሆነ የተሰማው ከ1997 በኋላ ነው፡፡ ወደ ድሮው ዘመን የተመለሰውም ከዚሁ ምርጫ በኋላ ነው፡፡

በተለይ ከ97 በኋላ ገዥው ፓርቲ እንደስትራቴጂ እየተከተለ ያለውን ህግ እያጣቀሱ መፈረጅ፤ ነፃ ጋዜጦችን ማጥፋትና ሀቀኛ ተቃዋሚዎች ላይ ስም በመለጠፍ ከህዝብ ለመነጠል የሚያደርገውን ደባ በሀገር ላይ እንደተቃጣ ደባ በመቁጠር ጋዜጣችን ፍኖተ ነፃነት በጥብቅ ይቃወማል፡፡

ከምር ራሱ ኢህአዴግ ለታይታም ቢሆን የሚያነበንበው ህዳሴና መካከለኛ ገቢ ያላትን ኢትዮጵያ እንድናይ ከተፈለገ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ጋዜጦች ላይ የሚያካሂደውን ዘመቻ በማቆም በአስቸኳይ ወደ ውይይት መምጣት ይገባዋል፡፡ ስውርና ግልፅ ዘመቻውንም ማቆም አለበት፡፡ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች እንዲሰደዱ ማድረግ ወይም እስር ቤት ማጐር ከጥቅሙ ጉዳቱ የበዛ ነው፡፡ የህዝብን የነፃነት ስሜትም ማፈን አይቻልም፡፡ ትውልድ ካልቆመ በስተቀር ሊዳፈን አይችልም፡፡ ሊቆም ደግሞ አይችልም፡፡ "ሚስማር አናቱን በመቱት ቁጥር ይጠብቃል" እንደሚባለው ስርዓቱ ላይ ጥላቻ ከማትረፉና በደል የሚፈፀምባቸው የበለጠ እንዲበረቱ ከማድረግ ውጭ ጥቅም የለውም፡፡ ለሀገርም አይጠቅምም፡፡

በተለይ መንግስት በርካታ ሃላፊነቶች ተጭነውበት እያለ በማይጠቅም ግልፅ ዘመቻ ተጠምዶ ሲገኝ ያሳስባል፡፡ ለዚህም አብነት የሚሆነንን ምሳሌ እናንሳ፡፡ በመጀመሪያ የኢህአዴግ የንድፈ ሀሳብ መጽሄት በሆነቸው "አዲስ ራዕይ" ላይ ሊያጠፋቸው የፈለጋቸውን ዜጎች ያሰፍራል፡፡ ከዚያ በመቀጠል ደግሞ በእነ አይጋፎረምና አዲስ ዘመን ላይ በግለሰብ ስም አጥፊና ፈራጅ ፅሁፍ ይቀርባል፡፡ ብዙም ሳይቆይ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ውይይት ሆኖ ይቀርባል፡፡ ማሳረጊያውም "በሽብር ተግባር ሲንቀሳቀሱ የተገኙ ግለሰቦች በህዝብ ትብብር በቁጥጥር ስር ዋሉ" በሚል የኢቴቪ ዜና ይሆናል፡፡ ድራማው እንደዚህ ነው፡፡ ይሄ በጣም አደገኛና አሳሳቢ አካሄድ በአስቸኳይ እንዲቆም እናሳስባለን፡፡ ይሄ አይነቱ ግልፅ ዘመቻ በሳምንታዊው ፍትሕ ጋዜጣ እንደተጀመረ ተመልክተናል፡፡ ይሄን የማሳደድና የማጥፋት ዘመቻ አጥብቀን እንቃወማለን፡፡ ከዚህ በፊትም ከላይ በገለፅነው መንገድ የታሰሩ የፖለቲካ ሰዎች በርካታ ናቸው፡፡ ትናንት የበርካታ አንባቢያንን ቀልብ ገዝታ የነበረችው "አዲስ ነገር" ጋዜጣ የተዘጋችውና አዘጋጆችም ለሀገራቸው ብዙ መስራት እየቻሉ የተሰደዱት ከላይ በገለፅነው አይነት ቅንብር ነው፡፡ የአውራምባ ታይምስ አዘጋጅ ከመሰደዱ በፊት በአዲስ ዘመን ገፅ ሦስት ላይ "ይታሰር" የሚል ፅሁፍ ቀርቦበት ነበር፡፡ በኬንያና በሱዳን የተሰደዱ ጋዜጠኞችም በርካታ ናቸው፡፡ ይሄ ለአንድ ገዥ ፓርቲ ምን አይነት እርካታ እንደሚሰጠው ባይገባንም ዘመቻው አሁንም ቀጥሏል፡፡

ከላይ በገለፅነው አካሄድ ሳምንታዊው ፍትሕ ጋዜጣ ላይ ዘመቻው ተጧጡፏል፡፡ "ፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ" በሚል ርዕስ ፍረጃው፣ ማስፈራሪያውና ዛቻው ሌላ ነው፡፡ እነዚህ ፅሁፎች በግለሰብ ስም ይውጡ እንጅ ከጀርባ ተቋም እንዳለ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህ በፊትም ያየነው ይሄንን ነው፡፡ ዝም ብሎ ካለቦታው ለማይመለከተው ሁሉ "ሽብርተኛ" የሚል ስም መለጠፉና ማን አለብኝነት የስርዓቱ መገለጫ እየሆነ ነው፡፡ አሁንም ፍትሕ ጋዜጣና ሌሎች ላይ የተከፈተው ዘመቻና ፍረጃ እጅግ ያሳስበናል፡፡ የተነቃበትና የማይጠቅመው የኢህአዴግ ግልፅ ዘመቻ ሊገታ ይገባዋል፡፡

ከመሬት እየተነሱ "ሽብርተኛ! ሽብርተኛ" እያሉ ለስልጣን ያሰጉኛል የሚሉት ላይ ሁሉ ጣትን መጠቆም መዘዙ ለራስም ሊተርፍ ይችላል፡፡ የህዝብ ብሶት መፈንጃ ምክንያቱ አይታወቅም፡፡ ለሌሎች በቆፈሩት ጉድጓድ ማን እንደሚገባ አይታወቅምና ለማንኛውም ለዚች ምስኪን ሀገር ቅድሚያ መሥራቱ ነው የሚበጀው፡፡

ጋዜጣችን "ፍኖተ-ነፃነት" ብለናታል፡፡ "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር "የነፃነት መንገድ" ማለት ነው!!

ፍኖተ -ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሠረተ፡፡ ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሥር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር የፓርቲው ጋዜጣ ነው፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል ይፈልጋል፡፡ የማንኛዉም ሰዉ ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበት‌ና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙ‌ንና ፖሊሲዉን ለማቅረብ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነዉ

ዋና አዘጋጅ፡-
ሰለሞን ስዩም
አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 1
የቤ.ቁ 028

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መሥፍን

አምደኞች፡- ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ወንድሙ ኢብሳ
አንዱዓለም አራጌ
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ቀለሙ ሁነኛው
በለጠ ጎሹ

ኮምፒውተር ጽሑፍ፡-
የሺ ሃብቴ
ብርቱካን መንገሻ

ህትመት ክትትል፡-
አያክሉህም ጀንበሩ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ

አሣታሚው፡-
አንድነት ለዴሞክሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት)

አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ.ቁ አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07 የቤ.ቁ 984

የዝግጅት ክፍሉ
ስልክ +251 118-44 08 40
+251 922 11 17 62
+251 926 81 46 81
+251 913 05 69 42
+251 923 11 93 74

ፖ.ሳ.ቁ፡ 4222

ኢሜይል፡- fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org

ፋክስ ቁጥር፡- +251-111226288

# ይህ ሰሚ ያጣ ጩኸት እንጂ ጫጫታ አይደለም!



ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
mesayewa2011@gmail.com

ለዛሬ ጽሁፌ እንደመነሻ ያደረግኩት በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚንትራችን የሊዝ አዋጁን በሚመለከት "ይህ አዋጅ ጫጫታ የሚያስነሳ አልመሰለንም" ያሉትን አባባል መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡ በርግጥ ያን ጊዜ ህዝቡ ጮኽ እንጂ አልተንጫጫም፡፡ ህዝቡ ዛሬም እየጮኽ ነው፡፡ ይህንንም ጠቅላይ ሚንስትሩ ምን እንደሚሉት ባላዉቅም ጫጫታ አለመሆኑን ለማብራራት እሞክራለሁ፡- 1) የመምህሩ የደመወዝ ጭማሪ፣ 2) የአማራ ህዝብ ከጉራፈርዳ ወረዳ መፈናቀል፡፡ 3) መቆሚያ የሌለዉ የኑሮ ዉድነት፣ ወደ ፊትም በባሰ ሁኔታ የሚያስጮህ ይመስለኛል፡፡

ኢህአዴግ ሀገሪቱን ከተቆጣጠረ ጀምሮ ህዝብ በተለያዩ ጊዜ ስለሚደርስበት መከራና ችግር አስመልክቶ ይጮኻል፡፡ ያለመታደል ሁኖ በየትኛዉም መንግስት ቢሆን ይህ ህዝብ ሰሚ አላገኘም፡፡ በደርግ ጊዜ "ወርቅ ሲያነጥፉለት ፋንድያ ነዉ" የሚል የመዘባበቻ መልስ ተሰጥቶት ነበር፡፡ በወቅቱ የእርስ በርስ ጦርነት፣ ልጆቹ ለብሄራዊ ውትድርና ትምህርታቸዉን እያቋረጡ መወሰዳቸዉ፣ ልጆቹ በቀይ ሽብር መጨፍጨፋቸው፣ በቀበሌ ካድሬዎች ግፍና በደል ስለተፈጸመባቸዉ፣ በመጮሁ ተሰደበ፡፡ በኢህአዴግ የ20 ዓመት አስተዳደሩም ችግሮችን ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም፡፡ ሆኖም ከመጀመሪዉ እስካሁን ህዝብ ላቀረበዉ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፍላጎት አሳይቶ አያዉቅም፡፡ ይህ ኢህአዴግ እየሄደበት ያለዉ የግትርነት አካሔድ ለማንም አልጠቀመም፡፡ ግትርነት ወደሞት እና ወደመጥፊያ የሚወስድ ሰፊ መንገድ ነዉ፡፡ ኢህአዴግ ደግሞ ይህንን እየተከተለ ነዉ፡፡

ይህንን ስል ምንም ነገር ተደብቆ እንደማይቀር አንድ ነገር አስታወሰኝ፡፡ የትግሬና የወሎ ህዝብ በተራበና የሰዉ ልጆች እንደቅጠል በረገፉ ጊዜ አፄዉ ረሀብን እንደዉርደት ቆጥረዉ ከህዝቡ ስቃይ ይልቅ የእርሳቸዉን ክብር በማስቀደም «የራበኝ» ጩኸቱን እንደአጎዛ ተቀመጡበት፡፡ ሆኖም የተሸፈነ ሳይገለጥ፣ የተደበቀ ሳይወጣ አይቀርምና ጆናታን ድምብልቢ የተባለዉ ጋዜጠኛ «የተደበቀዉ ረሀብ» (the hidden hunger) በሚል ርዕስ ያዘጋጀዉን

| ተ.ቁ | ሙሉ ዴሞክራሲ | ዴሞክራሲ እያበበባቸው ያለው | ዲቃላ ዴሞክራሲ | አምባገነናዊ ደሞክራሲ | የጨነገፈ መንግሥት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሞሪሺየስ | ጋና<br>ሴኔጋሌ<br>ቤኒን<br>ናሚቢያ<br>ቦትስዋና<br>ደቡብ አፍሪካ<br>ሶማሊላንድ | ሞሮኮግብጥ<br>ደቡብ ሱዳን<br>ኡጋንዳ<br>ኬኒያ<br>ቡሩንዲ<br>ታንዛዘኒያ<br>ማላዊ<br>ሞዛምቢክ<br><br>ሞሩታኒያ<br>ጊኒ<br>ኮት ዲቮር<br>ኒጄር<br>ናይጄሪያ<br>ሊቢያ | ማሊ<br>አልጄሪያ<br>ቡርኪናፋሶ<br>ቻደ<br>ካሜሩን<br>ማዕከላዊ አፍሪካ ሪፓብልክ<br>ኮነጎ ብራዛቪል<br>ጋቦን<br>ኮነጎአንጎላ<br>ዚምባቡዌ<br>ማዳጋስካር<br>ኢትዮጵያ<br>ኤርትራ<br>ሱዳን<br>ሱዋዚላንድ | ሶማሊ |

ፊልም በቴምስ ቴሌቭዥን ላይ በማቅረብ ይፋ አደረገዉ፡፡ በዚህም አሰቃቂዉን የወሎን ረሃብ የሰዉ ልጆች እልቂት ከማሳዬቱም በላይ በምዕራብ አፍሪካ ከብቶች ሲያልቁ በኢትዮጵያ ግን የሰዉ ልጆች እያለቁ መሆናቸዉን በመግለጽ የዓለምን ህዝብ ልብ ሰበረ፡፡ አፄዉ ለራሳቸዉ ክብር ብለዉ የህዝቡን ልቅሶ እንደተራ ጫጫታ በመቁጠር ለመደበቅ ቢሞክሩም አልተሳካላቸዉም፡፡ በዚህም የዓለም ህዝብ በአንድ ድምጽ ኢትዮጵያዊ ወገኑን ከረሃብ ለመታደግ ሲረባረብ ለአፄዉ ሰጥቶት የነበረዉ ክብር ግን ቀነሰ፡፡ ኢህአዴግም አሜሪካንና መሰሎቿን ቢታበቅም እስከ ህዝብ የመጨረሻ ቁጣ ድረስ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነዉ፡፡ ለዚህም ሙባረክን ማስታወሱ ብልህነት ነዉ፡፡ አብዳላ ሳላህንም ቢሆን ማስታወሱ አይከፋም፡፡ ህዝቡ የመጨረሻ ግንፍልታዉ ላይ ከደረሰ በኋላ አሜሪካ እስካሁን ባለን ልምድ ወደ ህዝብ ሽብልል በማለት ስለምትሰጠዉ መግለጫ እና ከህዝቡ ጎን መሆኗን ለመግለጽ የሰኮንዶች ሽርፍራፊ ሰዓት አይወስድባትም፡፡

አሁን ህዝቡ መበደሉን ትንሽ ብቻ በመጮህ በብዙ ዝምታ እያሳለፈ ይገኛል፡

ወደ 8 ዞሯል

# ማጣፊያው ላልተበጀለት የአፍሪካ ቀንድ ግጭትና መዘዙ መፍትሔው ምን ይሆን?

ከመ/ር ደረጀ መላኩ

ለአፍሪካው ቀንድ አለመረጋጋት ሁነኛውን ሥፍራ የሚይዘው እስላማዊው ታጣቂ ቡድን አልሻባብ በሦስት ሀይሎች ማለትም በአሚሦም፣ በኬንያ እና በኢትዮጵያ እየተደቆሰ ጠንካራ ይዞታዎችን ለቋል ተብሎ ቢደሰኩርም አካባቢው ከግጭት አዙሪት መውጣት እንዳልቻለ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ሲናገሩ ከአለም መገናኛ ብዙሃን እያነበብን ወይም እያደመጥን እንገኛለን፡፡

አንድ የፖለቲካ ሣይንስ ተንታኝ ስለ አፍሪካው ቀንድ ፖለቲካ ሁኔታ ፕሮፌሰር መምህራቸው ያስተማሯቸውን በማስታወስ በሚከተለው መልኩ አስቀምጠውታል፡፡

"የአፍሪካው ቀንድ ፖለቲካ ማለት በግጭት የተሞላ ሥርዓት" ነው ይሉታል፡፡ ትክክለኛ አባባል ይመስለኛል፡፡ ባለፉት አስር እና ሃያ አመታት ብቻ አካባቢው ከተፈጥሮ ቁጣ ባሻገር ከግጭት አዙሪት መውጣት ያልቻለ የምዝብሮች መኖሪያ ሆኗል፡፡ በደካሞች፣ በስግብግቦች እና አምባገነኖች ምክንያት የተነሳ፡፡ ለምንድነው ነው ይሄ አካባቢ በማያቋርጥ የግጭት አዙሪት ውስጥ የተዶለው? የአካባቢው አገዛዞች አሊያም አለም አቀፉ ህብረተሰብ በተለይ በአለም ፖለቲካ መፃኢ እድል ላይ መወሠን የሚችሉት ምዕራባውያንና ታላቋ አሜሪካ የአፍሪካን ቀንድ ግጭቶች ለመፍታት የሚጠቀሙበት ዘዴ ምን ጎደለው?

እነዚህንና የመሣሰሉትን ጥያቄዎች ለመዳሰስ እና የራሴን መላ ምት ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡ ባለፉት 50 እና 60 አመታት አካባቢው ከማያባራ እልቂት ውስጥ ሊገባ የቻለው በዋነኛነት በጂኦ ፖለቲካዊ አቀማመጡ የተነሳ ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ባሻግር አገዛዞቹ (አምባገኖች) ግጭቶችን ለሥልጣን ማራዘሚያ ፍቱህን መድሃኒት ናቸው ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቀንዱ አካባቢ አገዛዞች አንዱ የሌላውን ተቃዋሚ ቡድን አቅፈው ይይዙ እንደነበር (እንደሚይዙ) ታሪክ ያስተምረናል፤ በተለይ ነፍጥ ያነገቱ ተቃዋሚዎቻቸውን፡፡

በ1960 እና ከዛ በፊት (እ.ኤ.አ) ሱዳን የኢትዮጵያን መንግስት የሚቃወሙትን ትደግፍ ነበር (ለምሳሌ ELF; EPOF እና OLF) ይጠቀሳሉ፡፡ ኢትዮጵያ በበኩሏ አኛኛ የተሠኘውን የተቃዋሞ እንቅስቃሴ (Anya anya rebels) ታስተባብር እንደነበር የቀንዱ አካባቢ የፖለቲካ ተጠባቢዎች ይናገራሉ፡፡

በተለይ ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያምና አገዛዛቸው በዶክተር ጆን ጋራንግ ይመራ ለነበረው የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ግንባር SPLMA መጠነ ሰፊ ድጋፉን አድርጓል፡፡ መሪዎቹ በጊዮን ሆቴል እና በሌሎች አካባቢዎች ረፍት እንዲያደርጉ ተፈቅዷል፡፡ ከዚህም እልፍ በማለት በአሦሳ የበርታ ሚሊሻዎችን በጋምቤላ ደግሞ ያኙዋክ ሚሊሻዎችን መሣሪያ ለማስታጠቅ ተሞክሯል፡፡

ሱዳን ደግሞ ሌላ የግጭት ካርድ መዘዘች፤ ዛሬ የአዲስ አበባ እና አስመራ አገዛዝ ለመሆን የበቁት ስንቅና ትጥቅ ማከማቻ ወይንም ሁለንተናዊ ድጋፍ ትሳጣቸው የነበረችው ሱዳን ነበረች፡፡ ምንም እንኳን የስልጣን አክሊል ለመድፋት በለስ ባይቀናቸውም ኢህአፓና ኢዲዩ የሱዳን ድጋፍ አልተለያቸውም ነበር፡፡ እንደ ዛሬው ከካርቱም ኡምዱርማን እስር ቤት አንገታቸው እየታነቀ ተላልፈው አይሰጡም ነበር፡፡ ሱማሊያ በአፄ ኃ/ሥላሴ ላይ አኩርፈው የሸፈቱትን ዋቆ ጉቱን አቅፋ ደግፋ በመያዝ እሣት ላይ ቤኒዚን አርከፍክፋለች፡፡

"ፍየል ከመድረሷ . . ." እንዲሉ ከእናት ኢትዮጵያ በሸፍጥ የተለየችው ኤርትራ ሳትቀር ለSPLMA እና NDA (ለብሔራዊ ዲሞክራሲ ህብረት) ድጋፍ ስትል ወታደሮቿን ሱዳን ሉአላዊ ግዛት ድረስ ልካ እንደነበር በወቅቱ ተዘግቧል፡፡

ሱዳን በበኩሏ እስላማዊ ፍልስፍና በማራመድ የሚታወቁ የአስመራን ተቃዋሚዎች አይዟችሁ በርቱ ትላለች፡፡ በአሁኑ ዘመን የሚካሄደው የአፍሪካው ቀንድ አገዛዞች ጨሀትና ስሞታ ወይም የክስ ውርጅብኝ ካለፉት ሁኔታዎች የተለየ እንዳልሆነ ማስተዋል ለሚችል ሰው ግልፅ ይመስለኛል፡፡

የአዲስ አበባው መንግስት በአሸባሪነት ፈርጆ በጥቁር መዝገብ ውስጥ ያሰፈረቻቸውን የኦጋዴን ነፃ አውጪ ድርጅት (ONLF)፣ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ድርጅት (OLF) እና ግንቦት ሠባት የተሠኙትን ተቃዋሚዎቹን የኤርትራ መንግስት እንደሚረዳቸው በይፋ የተናገረው ጉዳይ ነው፡፡ በሚያስገርም ሁኔታ የአዲስ አበባው አገዛዝ አዲስ ባወጣው የውጪ ፖሊሲ መሠረት የቀድሞ ሁነኛ ሸሪኩ የነበሩትን አቶ ኢሣያስ አፈወርቂን ከሥልጣን እናስወግዳለን ለሚሉ ኤርትራውያን የፖለቲካ ድርጅቶች ድጋፍ እያደረገ ስለመሆኑ የአካባቢው ተንታኞች በየጊዜው የተናገሩት ጉዳይ ነው፡፡

በተጨማሪም ኢጋድ የፀጥጣው ምክር ቤት ኤርትራን የአልሻባብ ሸሪክ በሚል የፈረጀት መሠለኝ፡፡ የውጭ ፖሊሲ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ከሆነ የአንድ ሀገር የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የሀገሪቷ የውስጥ (domestic policy) ነፀብራቅ ነው፡፡

በዚህ ምክንያት በሀገራቸው ሠላም ማምጣት ያልቻሉ ለሌሎች የተፈለገውን መረጋጋት ሊያስገኙ አይቻላቸውም፡፡ ጸሐፊው ማተኮር የሚሻው የሠብአዊና የዴሞክራሲ መብቶችን የሚደፈጥጡ አምባገነኖች ለሌሎች ሠላምን ማምጣት አይቻላቸውም በሚለው ላይ እንደሆነ አንባቢያን ያስታውሳል፡፡

ግራም ነፈሰ ቀኝ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ወድቋል፣ ሱዳን ከብጥብጥ የዳነች አይመስለኝም፤ ኤርትራ በተዘጋ ቤት ውስጥ ያለች መሠለኝ፤ የኬንያ ህዝብም የደላው አይመስለኝም፤ ሡማሊያ በለየለት ጦርነት ውስጥ እንደምትደማ ሁሉም ያውቀዋል፡፡ በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የአፍሪካው ቀንድ በአለም አቀፍ አሸባሪዎች ኢላማ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል የፖለቲካ መገመት ይቻላል፡፡

እንዴት ነው ታዲያ የአፍሪካው ቀንድ ከግጭት አዙሪት ሊወጣ የሚችለው? በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የግጭቶች መንስኤዎች የዴሞክራሲ አለመኖር፣ ነፃና ገለልተኛ የምርጫ ሁኔታዎች አለመመቻቸት፣ ሠላማዊ የስልጣን ሽግግር እውን አለመሆን እና በሌሎች ምክንያቶች ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ቀንዱ የአምባገኖች መፈንጫ ሆኗል፡፡ እነዚህን ለመጣል ደግሞ ብረት አምላኪዎች ተፈጥረዋል፡፡ በእኔ በኩል ሠላማዊ ትግል አማራጭ የማይገኝለት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ከዚህ ባሻገር ሀገራት በአንድነት ላይ ያላቸው አቋም ፅኑ አይደለም ይባላል፡፡ ሁለት አስርተ ዓመታት ባለሞላ ጊዜ ውስጥ በቀንዱ ሁለት ሀገራት ተፈጥረዋል፡፡ ሆኖም የእነዚህ አዲስ ሀገርነት ሠላምን አላመጣም፡፡ በአንፃሩ ግጭትን እያባባሰ ይገኛል፡፡ በዚህ የመሰነጣጠቅ ውጤት በአለም በጨካኝ አገዛዝ ፍዳዋን የምታይ ኤርትራ መወለዷን አንርሣ፡፡

ስለሆነም ከከፋ እልቂት ለመዳንና ከግጭት አዙሪት ለመውጣት ከተፈለገ በአፍሪካው ቀንድ በተለይ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ባህል ሥር መስደድ አለበት፡፡

የዴሞክራሲ ባህል እውን እንዲሆን ከተፈለገ ደግሞ የኢጋድ አባል ሀገራት በተለይ ኢትዮጵያ የአሜሪካን መንግስትና የምእራቡ አለም እጅና ጓንት ሆነው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የአዲስ አበባው አገዛዝ ለእውነተኛ የፌዴራሊዝም ሥርዓት እውን መሆን ፈቃደኛ መሆን ይገባዋል፡፡ በኢትዮጵያ በእውነት መሠረት ላይ ሆኖ ለሠብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት የቆመ መንግስት ከተመሠረተ ሌሎችም የእኛን አርአያ ሊከተሉ ይችላሉ፡፡


አለም አቀፉ ማህበረሰብ በተለይ አሜሪካ አሸባሪዎችን መዋጋት ያለባት ለራሷ ጥቅም ብቻ በማሰብ መሆን የለበትም፡፡ በመጀመሪያ በአካባቢው መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የበኩሏን ሠላምና ዲሞክራሲ ከሠፈኑ በኋላ የአሸባሪዎች አደጋ እዳው ገብስ ይመስለኛል፡፡

አሜሪካ የራሷን ጥቅም በማስላቷ ብቻ በሱዳን ዳርፉር የተነሳውን ብጥብጥና ደም መፋሰስ ለማቆም ብዙ ጊዜ ጥረት ስታደርግ

ወደ 16 ዞሯል

ኢ/ር ኃይሉ ሻወል የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ፕሬዝደንት ናቸው፡፡ ስለ ፓርቲያቸው ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ፣ ስለ ወቅቱ ፖለቲካ፣ ስለግላቸው ከባልደረባችን ብዙአየሁ ወንድሙ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡

# አንድ ዘለላ አለች እዚያ ስንደርስ ተመሳሳይ ዓለማ ካለን ጋር መዋሐዳችን አይቀርም



➢ መኢአድ አሁን ያለበት ተጨባጭ ሁኔታ ምን ይመስላል?

መኢአድ ላለፉት ሁለት አመታት በከፍተኛ ችገር ውስጥ ነው የቆየው፡፡ በውስጥ ችግሮች ላይ እንድናተኩር ተገደናል፡፤ ቤታችንን በማጽዳት ላይ ቆየን፡፡ የፖርቲውን ገንዘብ ያሸሹ፤ ራሳቸውን ትልቅ አድርገው ያዩ የነበሩ ሁሉ፤ ቁጥራቸው በርካታ ባይሆኑም ፓርቲውን ሲያምሱ ከርመዋል፡፡ ምርጫ ቦርዱም አብሯቸው ሆኖ ሠርቷል፡፡ ሆኖም ግን ታስቦ የነበረው፣ ተዶልቶ የነበረው ሁሉ ከሽፏል፡፡ የከሸፈው በኃይሉ ሻወል ሳይሆን በጠንከራ የፖርቲው ወጣቶች ነው፡፡ አዲስ አበባንና አንዳንድ ዞኖችን ለማወናበድ ሞክረው ነበር፡፡ አልተሳካላቸውም፡፡ እንዲሁም ዞን ድረስ ሊሄድላቸው አልቻለም፡፡

አሁን አዲስ አበባንም ዞኖችንም በአዲስ መልክ እያደራጀን ነው፡፡ ብዥታ ውስጥ የነበረው ዲያስፖራውም አሁን ግልጽ እየሆነላቸው ነው፡፡ ቻብተሮቻችንንም እንዲሁ እያደራጀን እንገኛለን፡፡ ችግሩ ከቅንጅት ጊዜ ጀምሮ ተያይዞ የመጣም ስለነበረ ለማስተካከል ጊዜ ወስዶብናል፡፡ አሁን ሁሉም ነገር እየተስካከለ ነው፡፡

➢ በጀታችሁም ተስተካክሏል ማለት ነው?

በጀቱ ገና ነው፤ አልተስተካከለም፤ እየተስተካከለ ያለው የፓርቲውን አደረጃጀት መዋቅር ነው፡፡ የፓርቲው ገቢና በጀት መሠረቱ የአባላቱ ወራዊ ክፍያ ነው፡፡ አደረጃጀቱና መዋቅሩ ከተስተካከለ በጀቱና ገቢው ቀጥሎ የሚመጣ ነው፡፡

➢ "መኢአድ ድርጅታዊ አሰራር የውስጥ ዲሞክራሲ የለውም፡፡ በጋራ አጀንዳ መቅረጽ፣ በነፃነት መወያየት፣ በጋራ የመወሰን ባህል የለውም" ይባላል፡፡ ምን አስተያየት አልዎት?

ይኸ የቆየ አሉቧልታ ነው፡፡ በፖርቲው ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ህይወት ከሌለ፣ አምባገነናዊ አሠራር ካለ፣ ጠቅላላ ጉባኤው እንዴት አስገድዶ ሊመልሰኝ ይችላል? የማይፈልገውን፣ መብቱን የሚገፈውን፣ ነፃነቱን የሚከለክለውን በምን ምክንያት በግድ ምራኝ ብሎ ያስገድደዋል? ይህ የተለመደ ተራ ወሬ ነው፡፡ እንደማንኛውም ስብሰባ ሥርዓቱን ጠብቆ አጀንዳ ይያዛል፡፡ ሥራ አስፈፃሚውም፣ ማእከላዊ ም/ቤቱም በነፃነት ሐሳቡን ያንሰራሽራል፤ በሐሳብ የበላይነት ያሸነፈ ሐሰብ ይፀድቃል፡፡ በድምጽ ብልጫ የፀደቀውን ሐሳብ ሁሉም አክብሮ በሥራ ላይ ያውላል፤ ምኑነው የወስጥ ዲሞክራሲ የለውም የሚያሰኘው?

➢ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ፣ ማዕከላዊ ም/ ቤት በሥራ አስፈጻሚው በደንቡ መሠረት ጊዜውን ጠብቆ አይስበስብም፤ በዚህ ምክንያት ችግር ይከሰታል፤ የሚሉ አሉ፤ ምን አሳተያየት አልዎት?

ከጠቅላላ ጉባኤው እንነሳ፤ የፓርቲያችን ጠቅላላ ጉባኤ የሚያደረገው በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ነው፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ቢገጥም፤ የሰብሰባውን ጊዜ እስከ ስድስት ወር ድረስ ማራዘም እንደሚችል ደንቡ ይደነግጋል፡፡ የፓርቲውን ቁልፍ ቁልፍ ቦታ ይዘው የነበሩ ቡድኖች ጠቅላላ ጉባኤው እንዲደረግ ባለመፈለጋቸው ጠቅላላ ጉባኤው በወቅቱ ሊደረግ አልቻለም፡፡ የጊዜ ገደቡ ሊያልቅ ሲል ግን በግድ ስብሰባው እንዲደረግ አድርገናል፡፡ በሰኔ ወር 2002 ዓ/ም መድረግ የነበረበትን ስብሰባ በህዳር ወር ውስጥ አድርገናል፡፡ የፓርቲውን ደንብ አልጣስንም፡፡ በደንቡ መሰረት ማዕከላዊ ም/ቤቱ አባላት የዞን ስብሰቢዎች ናቸው፡፡ የዞን ስብሰባዎችን ከየዞኑ ለመጥራት አበልና ትራንስፖርት የግድ ነው፡፡ ለዚሁ ሲባል በየስድስት ወሩ ም/ቤቱ እየተሰበሰበ ይወያያል፡፡ ይመከራል፤ ይወስናል፡፡

ከዚህ በፊት በጽ/ቤቱ መሽገው ፓርቲውን ሲያምሱ የነበሩ ግለሰቦች የዞን ተጠሪዎች ቀርተው አዲስ አበባ ያለው አመራር ብቻ እየተሰበሰበ ይወስን ይሉ ነበር፡፡ አምባገነናዊ ከተባለም መባል ያለበት እንዲህ ያለ አስተሳሰብ ነው፡፡ ሥራ አስፈጻሚውም ጊዜውን ጠብቆ ይሰበሰባል፡፡ በየደረጃው ያለው የፓርቲው መዋቅር ባለው ደንብ መሠረት እየሠራ ነው ብለን እናምናለን፡፡

➢ ከእርስዎ በስተቀር ከጠቅላላ ጉባኤ እስከ ጠቅላላ ጉባኤ ድረስ የሚዘልቅ ተመራጭ የለም ይባላል፡፡ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ አመራር በእርስዎ ይታገዳል፤ ይባረራል ይባላል፡፡ ምን መልስ አልዎት?

እስከ 2002 ዓ/ም ድረስ አመራር አልተቀየረም፡፡ አመራር የተቀየረው ከአሁኑ ጠቅላላ ጉባኤ በኋላ ባለው ወቅት ነው፡፡ ከላይ እንደገለጽኩልህ በአሁኑ ጠቅላላ ጉባኤ እኔ ፕሬዝዳንት ሆኜ እቀጥላለሁ ብዬ ራሴን ያዘጋጀሁበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ጠቅላላ ጉባኤው አስገድዶ እንድቀጥል አድርጎኛል፡፡ ኃላፊነቱን ከተቀበልኩ በኋላ የሥራ አስፈጻሙውን ዝርዝር ማቅረብ ግድ ሆነብኝ፡፡ እኔ በወቅቱ ማቅረብ አልፈለኩም ነበር፡፡ ፓርቲውን የሚያምሱትንና ፓርቲውን ለመምራት የተዘጋጁትን መለየት ስለሚያስፈልግ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በግድ ፓርቲውን ምራ ካላችሁኝ በማለት ለጠቅላላ ጉባኤው አሳውኩኝ፡፡ አሁን የማቀርበው ጊዜዊ ኮሚቴ ነው፤ ወደ ሥራው ስንገባ የሚሰራውንና የማይሰራውን በማለት አመራሩን እንዳስተካክል ውክልና እንዲሰጠኝ ብዬ ጠየኩኝ፡፡ ጠቅላላ ጉባኤው ውክልናውን ሰጠኝ ይህንን ምርጫ ቦርዱ በሥፍራው ተገኝቶ ተከታትሎታል፤ ውክልናውንም ተቀብሎታል፡፡ በዚሁ መሠረት ፓርቲውን የሚበጠብጡትን ለድርጅቱ ደንብና ዓላማ በቆሙ ሰዎች አስተካክዬ ቀጠልኩ፡፡ አመራሩ የተለወጠው በዚህ ምክንያትና አሰራር ነው፡፡ አሉቧልታ ማውራት ቀላል ነው፡፡ በሚሰራ ሰው ላይ ማስወራት የማይመለከተውን ስም በመስጠት ባህል እየሆነ ነው፡፡

➢ ይህንን ለአባላቱና ለደጋፊዎቻችሁ በግልጽ ለምን አላሳወቃችሁም?

ነጻ ፕሬስ፣ ነጻ ሬድዮ በሌለበት አገር አሉቧልታ የበላይነት ይይዛል፡፡ ጋዜጦች እና ጋዜጠኞች በነፃነት

እየሰሩ አይደሉም፡፡ በቅርቡ ከደቡብ ክልል ግዳጅ በተሞለበት ውሳኔና አመራር እየተፈናቀሉ ስለሚገኙት ዜጎቻችን ሕዝብ እንዲያውቀው ለማድረግ ሞክረን ነበር፡፡ በራሳችን ወጪ አንድ ጋዜጣኛ ስፍራው ድረስ ሄዶ እንዲመለከት አደረግን፡፡ የሚወራውንና የሚሰራውን በአይኑ አይቶ አረጋግጦ ለህዝብ እንዲያረጋግጥ አስበን ነው፡፡ አይቶ ከመጣ በኋላ "ምን አየህ?" ብለን ጠየቅነው፡፡ የያውን ሁሉ ነገረን፡ ፡ ይህንኑ በጋዜጣው ላይ ይዘግበዋል ብለን ስንጠብቅ፤ የዘገበው ሌላ ሆኖ ተገኘ፤ የነገርከንና በጋዜጣው ላይ የፃፍከው ለምን ተለያየ? ብለን ስንጠይቀው "አለቆቼ ይህ አይወጣም ብለው ከለከሉኝ" አለን፡፡ ጋዜጦች አትራፊዎች አይደሉም፤ ማስታወቂያ ካላገኙ ይከስራሉ፤ ማስታወቂያ ካላገኙ ይዘጋሉ፡፡ ማስታወቂያ ለማግኘት ደግሞ ኢህአዲግ የማይፈልገውን አለመዘገብ የግድ ነው፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ህዝብ እውነቱን መረጃ ማግኘት ከባድ እየሆነ ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሥርዓት ውስጥ ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል፡ ፡ አሉቧልታም ሥርዓት ባሕል እየሆነ ይሄዳል፡፡ በዚህ ምክንያት እርምጃችን ግልጽ ያልሆነላቸው ሊኖር ይችል ይሆናል፡፡ አብዛኛው አባላችን ተረድቶታል ብለን እናምናለን፡፡

➢ በእርስዎ በኩል ከሚነሱ ችግሮች አንዱ የጠቅላላ ጉባኤውን የማዕከላዊ ም/ቤቱን ሥልጣን ውክልና ስጡኝ ብለው ከወሰዱ ብኋላ የግል ውሳኔ ይወስናሉ ይባላል፡፡ ይህንን እንዴት ያዩታል?

ይኸም ቅድም ከገለጽኩልህ ጋር የተያያዘ ነው፡ ፡ ሳልዘጋጅ ፓርቲውን አሁን ባለበት ሁኔታ ጥለህ አትሄድም፤ ፓርቲውን በግራ በቀኝ ለመከፋፈል የሚንቀሳቀሱ ነበሩ፡፡ ጥለህ ልትሄድ አትችልም አሉኝ፡፡ በግድ ምራ፤ አስፈላጊ ነህ፤ ካላችሁኝ አመራሩን አስቤበት እንዳስተካክል ውክልና ስጡኝ አልኩኝ፤ በአንድ ድምጽ ስጡኝ፡፡ በተሰጠኝ ውክልና ፓርቲውን ማጽዳት፣ ማስተካከል ችያለሁ፡፡ እቅዳቸው የከሸፈባቸው ማድረግ የፈለጉትን ማድረግ ያልቻሉ የተለያየ ወሬ ሊያስወሩ ይችላሉ፡፡ እውነቱን ማወቅ ለሚፈልግ ግን ውክልናውን የወሰድኩት ፓርቲውን ለማትረፍ ነው፡፡ አትርፌበታለሁ፡፡

➢ ብስራተ ገብርኤል አካባቢ ያሠሩትን ጂምናዚየም ሲያስመርቁ የጠ/ሚኒስትሩን የሕግ አማካሪ ዶ/ር ፋሲል ናሆምን በክብር እንግድነት ጠርተው ነበር ይባላል፡፡ እርስዎ ከጠ/ሚኒስተሩ ጋር በዶ/ር ፋሲል በኩል እንደሚገናኙ ይነገራል፡፡ ምን አስተያየት አልዎት?

ሳቅ.......ይህ ደግሞ እስከአሁን ድረስ ያልሰማሁት አሉቧልታ ነው፡፡ ለመሆኑ ጂምናዚየሙ በሥነሥርዓት ተመርቋል እንዴ? ጂምናዚየሙ ሥራውን የጀመረው የክቡር እንግዳ ተጠርቶ ሥነ ሥርዓት ተደርጎለት አይደለም፡፡ ሌለው ከምትለው ሰው ጋር ምንም አይነት ግብብነትና ግንኙነትም የለኝም፡፡ ተራ አሉቧልተኞች የፈጠሩት ወሬ ነው፡፡

➢ ፓርቲያችሁ የምርጫ ሥነ ምግባሩን ከፈርመ በኋላ እርስዎ ጀሞ ሳይት በሚባለው አካባቢ 40 ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ለግንባታ ወስደዋል ይባላል እውነት ነው?

ይኸም ሌላው የፈጠራ ወሬ ነው፡፡ ጀሞ የሚባለውስ ቦታ የት ነው? እኔ ስሙንም ሰምቼ አላውቅም፡፡ ጀሞ ኬኒያታ እዚያ ቦታ መጥቶ ነው አካቢው ስሙን ያገኘው? 40 ሺ ካሬ ሜትር እኮ በጣም ብዙ ነው፡፡ ምን ያደርግልኛል፡፡ ይኼ የምታየው ዥምናዚየም 10ሺ ካሬ ሜትር ነው፡፡ ምን ልሰራበት ነው? ይሄንን ያህል መሬት የምጠይቀው፡፡ እኔ ገንዘብ ያፈራሁትም ውጪ ነው፡፡ የምንቀሳቀሰውም ከውጪ ይዤ በመጣሁት ገንዘብ ነው፡፡ እዚህ አገር ያፈራሁት አምስት ሳንቲም የለም፡፡ ለመሆኑ ውጪ አገር ያፈራውን ገንዘብ አገር ቤት አምጥቶ ግንባታ ላይ ያዋለ ሰው ስንት ይሆን? ይኸው እዚህ አገር ቤት የሠራሁት ግንባታ አሁን ባለው ሁኔታ ትልቅ ዕዳ ነው፡፡ ሥርዓቱ ከፍተኛ ችግር ያለበት ነው፡፡ ይህንን እያየሁ ሌላ ቦታ እንዴት እጠይቃለሁ? የሰማህው ውሸት ነው?

➢ ፓርቲያችሁ የምርጫ ሥነ ምግባሩን መፈረሙ እንደ ትልቅ የፖለቲካ ስህተት የሚቆጥሩት ተቃዋሚዎች አሉ፡፡ ለምርጫ 2002 ውጤት፤ አሁን ለተፈጠረው የፓርቲዎች ም/ቤት ላለው የፖለቲካ ምህዳር መፈጠር አስተዋጽኦ አድርጓል ይባላል፡፡ በእርስዎ እይታ ያን ጊዜ የነበርዎትን አመለካከትና ዛሬ ላይ ሆነው ሲያዩት እንዴት ይመለከቱታል?

በዚህ ጉዳይ ትላንትም ዛሬም ያለኝ አመለካከትም፤ አቋምም አንድ ነው፡፡ ድርድሩን የጀመርነው ሁላችንም በጋራ ነው፡፡ የተወሰኑት የምንደራደረው ለብቻችን ነው ብለው አቋረጡ፡፡ የወጡበት ምክንያት ለእኛ ግልጽ አልነበርም፡፡ በዚህ ቁጭት ነበረን፡፡ ስለዚህ እኛ ድርድሩን ቀጠልንበት፡፡ ከቅንጅት ጊዜ ጀምሮ እኛ ስንፈታ ያልተፈቱ ነበሩ፡፡ እነሱን ማስፈታት ነበረብን፡፡ በየቀኑ አባላት እየተመላለሱ "ተቀምጣችሁ የመደራደር ባህል የላችሁም፤ ኢህአዴግ የመደራደር ፍላጎት ሲኖረው እናንተ እንቢተኛ ትሆናላችሁ" እያሉ ይጨቀጭቁን ነበር፡፡ ኢህአዴግ እስከዛሬ ከማንም ጋር ተደራድሮ ቃሉን እንደማያከበር ግን ጠንቅቀን እናውቅ ነበር፡፡ ይህንን እያወቅን ተደራድረን 500 ሰው እስረኞችን ማስለቀቅ ቻልን፡፡ ይህ ለእኛ ትልቅ ድል ነው፡፡ ቀጥሎ የኢህኢዴግን ማነት ይወቅሱን ለነበሩ ሁሉ ይኸውላችሁ ብለን ለማሳየት በቅተናል፡ ፡ ኢህአዴግ ሁለተኛ እንዲያልፍ ማድረግ ችለናል፡ ፤ አሁንስ በዚያ መንገድ ትሄዳላችሁ ወይ? ብለህ ካልከኝ ግን መልሳችን አንሄድም ነው፡፡ ስምምነቱን ፈርመን በማግስቱ በአባላቶቻችን ላይ የተለመደውን ዘመቻ ጀመረ፤ እስከ ዛሬ ድረስ የፈጠራ ስምና ወንጀል እየፈጠረላቸው ያሻውን ያደርገል

➢ ከምርጫ ሥነ ምግባር ተያይዞ በተፈጠረ ስምምነት የፖርቲዎች ም/ቤት ተቋቁሟል፡ ፡ እናንተ ከም/ቤቱ ራሳችሁን አግላችኋል፡ ፤ እነሱ ደግሞ የአየር ስዓት አግኝተው እስከመከራከር ሄደዋል፡፡ "የአገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር ጠቧል" የሚለውን አስተሳሰብ የሚያፈርስ አይሆንም?

ኢህአዴግ እሱን የሚደግፍ ፓርቲዎችን መርጦ የፓርቲዎች ም/ቤት ብሎ አቋቋመ፤ እሱ እጅሲወጣ እጅ ያወጣሉ፡፡ እሱ ሲያወርድ ያወርዳሉ ደመወዝ እየከፈላቸው አስቀምጧቸዋል፡፡ እኛ አጀንዳ ስናቀርብ እሱን ወደ ጎን አድርጎ እሱ በሚያቀርበው አጀንዳ ብቻ እንድንወያይ ይፈልጋል፡፤ ለእኛ 3ሺ ብር ሲመደብ ለእነሱ 300ሺ ብር ይመደብላቸዋል፡፡ ከእነዚህ ጋር መቀጠሉን ስለአልፈለግን ወጥተናል፡፡ የተሰጣቸው የአየር ሠዓት የእነሱ የም/ቤቱ ስብሰብሰባ የፖለቲካ ምህዳሩን መስፋት የሚያሳይ አይደለም፡፤ ጉዳዩን ሁሉም ጠንቅቆ ያወቀዋል፡፡

➢ የምርጫ ሥነ ምግባሩን በመፈረማችሁ ህዝብ በፖለቲካ አቋማችሁ በዥርታ ፈጥሮበታል ብለው ያስባሉ? በምርጫ 2002 ያገኛችሁት ውጤት ይህንን የሚገለጽ አይመስልዎትም?

ሕዝብ በትግል ጉዞአችን ወይም በፖለቲካ አቋማችን ላይ ብዥታ ተፈጥሮብታል ብለን አናምንም፡፡ ስለምርጫ 2002 ውጤት ላልከኝ ምርጫውን ህዝብ አልተሳተፈበትም፡፡ ኢህኢዴግ የሚያገኘው ድምጽ ከ10% አይበልጥም፡፡ ኢህኢዴግ በህዝብ የሚደገፍ፤ በህዝብ የሚፈለግ ድርጅት አይደለም፡፡ ለዚህ ነው ህዝብ አማራጭ እንዳይስማ የሚከለከለው፡ ፡ አማራጭ ያላቸውን ፓርቲዎች ከህዝብ እንዳይገኙ የሚከለከለው፡፡ ነፃ ሚዲያ እንዳይኖር የሚያደርገው፤ ከምርጫው በፊት የምርጫ ኮሮጆዎች በድምጽ መስጫ ካርድ ተሞልተው ነው የተሰቀሉት፡፡ ይህንን በተጨባጭ ይዘናል ለአውሮፓ ታዛቢ ቡድን አሳይተናል፡፡ እነሱም በሪፖርታቸው አላካቱትም፡ ፤ ምርጫው ውጤት የሕዝብን ድምጽ የያዘ ሳይሆን በጣቢያው ላይ የነበሩ ምርጫ አስፈጻሚ፤ የህዝብ ታዛቢ እየተባሉ በየጠቢያው የተቀመጡ የኢህአዴግ አባላት የሞሉት ካርድ ውጤት ነው፡፡

➢ በቅርቡ ከአራትና ከአምስት ወር በኋላ የአዲስ አበባ ከተማ ምርጫ ይደረጋል፡ ፡ ፓርቲያችሁ ለምርጫው ምን ያህል ዝግጅት እያደረገ ነው?

ምርጫ የሚለው ትልቅ ክብር ያለው ቃል ነው፡፡ ብለን መጠየቁ የተሻለ ነው፡፡ በ1997 ዓ.ም ምርጫ የሚመስል ነገር ፈንጥቆ ነበር፡፡ ህዝቡም ምረጡ ካለችሁኝ ብሎ ቅንጅትን መረጠ፡፡ ኢህአዴግ ለምን እኔን አልመረጣችሁም ብሎ የፈፀመውን ሁሉ እናውቃለን፤ ይህ በእንዲህ እያለ ምርጫ 2002 በዘፈቀደ ገባን፡፡ ኢህአዴግ መሳቂያ የሆንበትን ምርጫ አደረገ፡፡ ትላንት የነበረው ችግር ዛሬም አለ፡፡ የተስተካከለ ነገር የለም፡፡ መለወጥ ያለባቸው ነገሮች አልተለወጡም፡፡ ገለልተኛና ነፃ የምርጫ ቦርድ የለም፡፡ በዞን፣ በወረዳ፣ በጣቢያው ያለው የምርጫ አስፈጻሚ የኢህዲዴግ ካድሬና ደህንነት ነው፡፡ የየአካባቢው አስተዳደር ኃላፊዎች ናቸው፡፡ ዛሬም ያለምንም ሐፍረት መዋቅር ትክክል ነው ብለው ቀጥለውበታል፡፡ የግል ሚዲያውን ሙሉ በሙሉ ማለት በሚያስችልበት ሁኔታ አጥፍተውታል፡፡ የከተማውን ህዝብ ቤት እያፈረሱ መኖሪያ አሳጥተውታል፡፡ ልጆቹን ከየት/ቤቱ አስቀርተውበታል፡፡ ኢህአዴግ ከዚህ በፊት የሠራው አልበቃ ብሎ ዛሬ ሌላ ድራማ እንዲሠራብን አንፈቅድለትም፡፡ የምርጫ ምህዳሩ እስከልተስካከለ ድረስ፣ የመወዳደሪያው ሜዳ ለሁላችንም እኩል እስካልሆነ ድረስ፣ ምርጫውን አንካፈልም፡፡ በአንጻሩ ግን ትግላችንን አጠናክረን እንገፋበታለን፡፡

➢ ከደቡብ ክልል ስለሚፈናቀሉት ሰዎች የሚሉት ይኖራል?

ጉዳዩን በቅርብ እየተከታተልነው ነው፡፡ ዜጎችን ከመኖሪያቸው አካባቢ ማፈናቀል፣ ንብረታቸውን መቀማት ቤታቸውን ማቃጠል መደብደብ ማስር መግደል ማስዳድ እየተፈጸመ ነው ታስቦበትና ታቅዶበት የሚከናወን ነው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ተናገሪዎች ላይ እየተፈጸመ ያለ ድርጊት ነው፡፡ ጉዳዩ የዘር ማጥፋት ዓለማ ያለው ነው፤ ከዓለም አቀፍ የህግ ባለምያዎች እየመከርንበት ነው፡፡ ኢህኢዴግ ከዚህ አስከፊና አሰቃቂ ድርጊቱ በአስቸኳይ ካልተቆጠበ በዓለም አቀፍ ፍ/ቤት በዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ልንመሰረት እንችላለን፡፡

➢ የመኢአድ ጠቅላላ ጉባኤ ከአንድነት ፓርቲ ጋር ውህደት እንዲደረግ ወስኖ ኢ/ር ኃይሉ ሽረውታል ይባላል፡፡ እርስዎን የውህደትና የህብረት ችግር ፈጣሪ አድርገው የሚመለከቱ ወገኖች አሉ ምን አስተያየት አልዎት?

በመጀመሪያ ደረጃ የመኢአድ ጠቅላላ ጉባኤ ውህደቱ እንዲፈጸም ወስኖአል የሚባለው ስህተት ነው፡፡ አልወሰነም፡፡ ከጠቅላላ ጉባኤው በፊት በአመራሩ ውሳኔ ከሁለት ፓርቲዎች ጋር ድርድር ጀምረን ነበር፡ ፡ ይህንኑ ለጠቅላላ ጉባኤው ማሳወቅ ስለነበረብኝ አቀረብኩ፤ ጉባኤውም ድርድሩ እንዲቀጥል ፈቀደ፡ ፡ መኢአድ በህብረት ስም፣ በቅንጀት ስም፣ በውህደት ስም፣ በርካታ ችግሮችና ፈተናዎች ገጥመውት ነበርና ያለፈው ችግር እንደይደገም ጥንቃቄ እንዲደረግ ማሳሰቢያ ሰጥቷል፡፡ በተሰጠኝ ማስጠንቀቂያ መሰረት የማያስኬደን ሁኔታ በመፈጠሩ ድርድሩን አቋርጠናል፡ ፡ ድርድሩ በምንስማማበት ሁኔታ ቢጠናቀቅ ኖሮ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርበን እናፀድቅ ነበር፡፡ ፓርቲያችንን ደብቀን የምንፈጽመው ውህደት የለም፡፡ አሁንም ለውህደት የሚያደርሱ ስምምነትና መግባባት የለም፡ ፡ ለመደጋገፍ፣ አብሮ ለመስራት ችግር የለብንም፡፡ ከዚያ ባለፈ ውህደት ብለን ዘለን ገብተን ችግር ውስጥ መግባት አንፈልግም፡፡ የእምነት ጉዳይ አለ፡፡ "ብሔር ብሔረሰቦችና ኢትዮጵያዊነትን ማንፀባረቅ" የሚሉ ጥያቄዎች አሉ፡፡ በቀላሉ የሚመለስ አይደለም፡፡ ዘርና ቋንቋን መሠረት ያደረገ የፌዴራል አደረጃጀት ወይስ በኢትዮጵያዊነትና በጂኦግራፊካል አቀማመጥ የሚለው እምነት በጥልቅት ሊፈተሽ የሚገባው ነው ብለን እናምናለን፡፡

ኢህአዴግ በቀደደው ቦይ እየተጓዝን እሱ እየፈበረከ በሚያሳየን ጉዳይ እየሄድን አማራጭ አለኝ ማለት አይቻልም፡፡ ትግሉን ማስተባበር ተደጋግፈን ተመካክረን ትግሉን ማራመድ ተገቢ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በዚህ ችግር የለብንም፡፡ አንድ ዘለላ አለች፡፡ እዚያ ስንደርስ ተመሳሳይ ዓላማ ካለን ጋር መዋሐዳችን አይቀርም፡፡ ለመረዳዳትም፣ ለመዋሀድ ግን ልንጠብቀው የሚገባንን ጥንቃቄ ማስታወል ይገባናል፡ ፡ ከአንዳችን ወደ አንዳችን ለመግባት የሚመጡትን መፈተሽ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ የማይፈልጉትን ፓርቲ ለቀው ወደሚፈልጉት ፓርቲ መግባት መብታችን ነው፡፡ ሆኖም ግን ቀድሞ የነበሩን ፓርቲ መልቀቂያ ያቀረቡበትንና የተሰናበቱበትን ማስረጃ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ግጭትን ያስቀራል፡፡ ከደቡብ ኢህአዴግን ለቀው ወደ እኛ ፓርቲ የተቀላቀሉ አሉ፡፡ መልቀቂያቸውን አረጋግጠን ተቀብለናቸዋል፡፡

➢ በእርስዎ እምነት ፓርቲዎች ምን ማድረግ አለባቸው ብለው ያስባሉ?

አምባገነን ሆነ ይህንን መመሪያ ሰጠ ላለመባል ይህንን አድርጉ ይህንን አታደርጉ የሚለውን የግል ሐሳቤን ዛሬ ባልስጥ ደስ ይለኛል፡፡ ቦታዬን ስለቅ ምክሬን ብለግስ የተሻለ ነው፡፡ በፓርቲያችን በአሁኑ ወቅት ቤታችንን አጽድተናል ብለን እናምናለን፡፡ እያንዳንዱ ፓርቲ ራሱን በጥንቃቄ ቢፈትሽ ብዙ ነገር ያገኛል፡፡ ራሱን ሳይፈትሽ፣ ራሱን ሳያውቅ፣ በየዋህነት ቢቀመጥ የእኛ ዕድል ይገጥመዋል፡፡ ፓርቲያችንን ሊዘጉብን ነበር፡፡ አትርፈነዋል፡፡ ወደ ውስጥ ማየት መፈተሽ እንደቀላል ጉዳይ የሚታይ አይደለም፡፡ ጉያችንን እንየው፡፡

አብረን ብንሄድ ምን ዓይነት ኃይል አለን ብሎ ማወቁ ይጠቅማል፡፡ ያለፍንበትን የትግል ጉዞ እንመርምረው እስከ ምርጫ 97 ድርስ የተጓዝንበትን ጉዞና ውጤቱን እናስታውሳለን፤ ከዚያ ውጤት በኋላ ያለውን የህዝቡን ስነ ልቦና እንወቀው፤ ምሁራኑ፣ አዋቂው፣ ወጣቱ ህዝቡ የት ቦታ እንዳለ እንገንዘብ ኢህአዴግ በእያንዳንዱ ቤት ገብቶ ምን እየሰራ እንደሆነ እንፈትሽ ህዝቡ ዛሬም በነጻነቱ በመብቱ ጉዳይ ብዥታ የለበትም፡፡ ሕዝብ የፍርሃት ድባብ ውስጥ ነው፡፡ ከዚህ የፍርሃት ድባብ ውስጥ ለማውጣት እንስራ የሚለውን ሀሳብ ብሰጥ ደስ ይለኛል፡፡ በመጨረሻ ዛሬ ለሕዝብ የወገነ ሚዲያ ያስፈልገል፡፡ የሞያውን ሥነ ምግባር ጠንቅቆ የተረዳ የሚዲያ ባለሞያ ሕዝብ ይፈልጋል፡፡

ወደ 14 የዞ



የአደባባይ ምስጢሮች

# “የነፃነት ዕሳቤ” “ዕውቀት በፍለጋ ሲገኝ ነፃነት ደግሞ ከዕውቀት ይገኛል”

በመንገሻ ክሉ

በኔ ዕድሜ ልክ ያለውን የኢትዮጵያን የፖለቲካ ገፅታ ለማየት አይኔን ለአንድ ሰከንድ ስጨፍን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ነፃነትን በብርቱ ፈልገው ሲጮሁ ጥቂት አምባገነኖች ደግሞ በዚህ ጩኸት ላይ ሲሸምቁበት ነው የሚታየኝ፡፡ በተለይ ያለፉትን አስር ዓመታትን ፖለቲካዊ ትዝታዎቼን ስቃኛቸው ለምንድነው እጅ የምንፈልገው? ትልቅ ነገር በሌሎች እጅ እንዳለ የምናስበው እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ፡፡

እኔ የምፈልገው ነገር ሊሰጠኝ በማይፈልግ ሰው እጅ እንዳለ ካሰብኩና ለማስመለስ ደፋር ከሆንኩ ወደ ፍልሚያ እገባለሁ፡፡ ከፈራሁም አጐንብሼ ሎሌ ሆኜ እኖራለሁ፡፡ ይሄ ነው የሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ፡፡

ግን ማነው “ለነፃነትህ ታገል” ብሎ ያስተማረኝ? ለምንስ ነው ነፃነትህ ያለው በራስህ እጅ ነውና ነፃነትህን ለመቀዳጀት ወደ ፍልሚያ መግባትም ሆነ ፈርተህ እንደ ሎሌ መኖር አይገባህም የሚል አስተማሪ ያልገጠመኝ? ቆይቶ ግን እየኖርኩበት ያለሁበት የነፃነት ፍልስፍና ይሄ መሆኑ ገባኝ፡፡ የናንተስ የነፃነት እሳቤ እንዴት ነው?

ዴሞክራሲና ነፃነት የሚሰፍነው ሁሉም ነፃነትን ፍለጋ ስለጮኸ ሣይሆን ሁሉም ራሱን በነፃነት መግለጥ ሲችል ብቻ ነው፡፡ ነፃነት የሚመጣው ደምን በማፍሰስ ሣይሆን በነፃነት ከማሰብ ነው፡፡ በነፃነት ለማሰብና ለመኖር ደግሞ ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ የለም፡፡ ነፃነት ነገ ወይም ዛሬ አይደለም፡፡ ነፃነት አሁን ነው፡፡ እኛ ነፃ ነን፡፡

ነፃነትን በሰላማዊም ሆነ ሠላማዊ ባልሆነ የፖለቲካ ትግል አትፈልጉት፤ይልቅ አሁን ኑሩት፤አሁን የትኛውንም ጤናማና ገንቢ የሆነውን አስተሣሰባችሁን ኑሩት፡፡ የምትፈልጉት አይነት የፖለቲካ ስርዓት በሀገራችሁ ለመዘርጋትም ሰይፍን አታንሱ፡፡

ከብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተ ማርያም የጦር ሜዳ ከተሰኘው መፅሐፋቸው ሽፋን ላይ ባየሁት ጊዜ ሁሉ የሚያስገርመኝ የጄነራሉ ሃሣብ አለ፡፡ “ላብ ደምን ያድናል” የሚል፡፡ እኔም ይህንን አባባል በአንድ ደረጃ ከፍ በማድረግ “ዕውቀት ደምን ያድናል” ብዬ እስባለሁ፡፡ እውቀት ብርሃን የበራለት ወይም ራሱን ያወቀ ህብረተሰብ ለነፃነት ጦር አይሰብቅም፡፡ እውነተኛ ነፃነት በዕውቀት እንጂ በደም አይገኝምና፡፡

በየትኛውም ዘመንና ሀገር ነፃነት ዕውቀትን ቀድማ አታውቅም፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን ከደካማ የቢሮ ትግል ወጥተው በትምህርትና ቤተ መፅሐፍት መስፋፋት ላይና ስልጡን የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ላይ በትጋት ያለማቋርጥ ቢሠሩ ኢህአዴግ ሥልጣን ሣይለቅ ሕዝቡ በነፃነት መኖርን እንዲያውቅ ሊያደርጉት እንደሚችሉ አስበው ያውቁ ይሆን? ነፃነት ያለፖለቲካ ምርጫ እንደሚገኝስ? የትኛው የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ነው ከሥልጣን ሽኩቻ ወጥቶ አንድ ቤተመፅሐፍት እንኳ የከፈተ? ከፅንሰ ሃሣብ ውጭ ባላቸው የነፃነት ዕሳቤና ውስጣዊ ማንነት ረገድስ ከገዢዎቻችን ምን የህል ይለያሉ?

መለስ ዜናዊ ኢህአዴግ ሥልጣን ከመያዙ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ ከሲ አይ ኤው ባለስልጣን ጋር ሲነጋገሩ “ኢትዮጵያውያን ነፃነትና ዴሞክራሲ እንዲጐናፀፉ እንፈልጋለን” ብሎ ነበር፡፡ ነገር ግን ያለፉት ሃያ አመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ረጅም ሰፊና ጥልቅ የነፃነትና ዴሞክራሲ ፍለጋ ጩኸት የተሰማበት ጊዜ ነው፡፡ ይልቅ መለስ ዜናዊ ዛሬ ኢትዮጵያን በዓለም ላይ ለፕሬስ ነፃነት ፍፁም ከማይመቹ ሀገራት የመጀመሪያውን ቦታ እንድትይዝ አድርገዋታል፡፡ ሆኖም ነፃነትና ዴሞክራሲ እንሰጣችኋለን ያሉን ሰዎች ሊሰጡን ባለመቻላቸው አትዘኑባቸው ራሳቸው የሕይወት ነፃነት የላቸውምና፡፡ የደካማ ተፈጥሮዋቸውና የበስተጀርባ ታሪካቸው ውጤቶች ናቸውና፡፡

ሚሼል አባማ “ነፃነት ሕግ በመለወጥ የሚመጣ ሣይሆን በሰዎች የዕለት ተዕለት ዕድገት የሚመጣ ነገር ነው፡፡” ማለቷ “ነፃነት የሚገኘው በሂደት ከሚዳብር ዕውቀት ነው” ማለቷ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ነፃነት ለሰው ልጆች ያለ-ህግ የተሰጠ መብት ነው ማለትም ይቻላል፡፡

ስለዚህ ነፃነት የሁለንተናዊ ዕድገት መሠረት ነውና የሕሊና ነፃነታችሁን ያለማንም ጣልቃ ገብነት አሁኑኑ አረጋግጡ፡፡ በቃ አንድ ቀን ነፃ እንደምትወጡ ተስፋ አታድርጉ፡፡ አሁን ነፃ እንደሆናችሁ ግን ቁጠሩ፡፡

## ይህ ሰሚ ያጣ ጩኸት . . .

ከገፅ 5 የዞረ

፡ የኢህአዴግ ወዳጅ የሆነው የአሜሪካን መንግስት CSIS የተባለ “ቲንክ ታንክ ግሩፕ” በምስራቅ አፍሪካ ጥናት አሰርቶ የኢትዮጵያ ህዝብ ቻይና ታጋሽ እንዲሁም ችግሮችን የመቋቋም ተሰጥኦ እንዳለዉ እና እስካሁን ከፍተኛ የሆነ በደል ቢደርስበትም ችግሮቹን ከመሸከም ዉጭ ለችግሮቹ ምላሽ ለመስጠት ምንም ሙከራ አለማድረጉን አረጋግጧል፡፡ ይህ የሚያሳዬዉ የኢትጵያ ህዝብ ሁሉን ቻይ መሆኑን ነዉ፡፡ ነገር ግን ይላል ጽሁፉ የኢትዮጵያ ህዝብ ትእግስቱ ሄዶ ሄዶ ካለቀ መመለሻ እንደሌለዉ ያትታል፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ኢህአዴግ ብዙ ይማርበታል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ምክንያቱም ጥናታዊ ጽሁፉ ከወጣ አራት ወራት ያህል ቢያስቆጥርም ኢህአዴግ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከመዉጣቱ በፊት እያደረገ የነበረዉን እያደረገ ነውና፡፡ ይህን ሳስተውል በበኩሌ ሁለት የተለያዩ ግምቶች ይኖሩኛል፡፡

የአምባ ገነንነቱ ደረጃ ሊለያይ ይችል ይሆናል እንጂ እንደየ ደረጃዉ በሁሉም ሀገር አምባገነንነት አለ፡፡ የእኛዎቹ ግን ትንሽ ሳይሆን በጣም የበዛ ይመስላል፡፡ምክንያቱም የለየላቸዉ አምባገነኖች አታድርግ ይላሉ፡፡ ያንን እነርሱ የከለከሉትን ያደረገ ህገ መንግስት ስለጣሰ ይቀጣል፡፡ ይህ ሰዉ ቀድሞዉንም አታድርግ የተባለዉን ሲያደርግ ለመቀጣት ወስኖ ነዉ፡፡ ለምሳሌ በደርግ ጊዜ ደርግን የተመለከተ ማንኛዉንም ትችት በጽሁም ይሁን በንግግር መቅረብ አይቻልም፡፡ ከተቻ ያዉ ቀይ ሽብር ይፋፋምበታል፡፡ አሁን በአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ግን በህገ መንግስት ሰዉ ያሻዉን እንዲናገር፣ የተሰማዉን እንዲጽፍ ተፈቅዶለታል፡፡ መቃወምም መደገፍም በሰላማዊ ሰልፍም ህዝባዊ ስብሰባም እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ ግን ይህንን የተፈቀደዉን ያደረገ ግን በሰበብ አስባብ ይወቀሳል፤ ይከሰሳል፤ ይታሰራል፡፡

በቅርቡ “ዘ ኢኮኖሚስት” የአፍሪካ ሀገራትን የዲሞክራሲ ደረጃ ከፋፍሎ አዉጥቷል፡፡በዚህም ሙሉ በሙሉ ዲሞክራሲ የሰፈነባቸዉ፣ ዲሞክራሲ እያበበባቸዉ ያሉ ሀገራት፣ ዲቃላ ዲሞክራሲ ያለባቸዉ ሀገራት፣ አምባገነናዊ ስርአት የሰፈነባቸዉ ሀገራት እና የፈረሱ ሀገራት በሚል ዘርዝሮ አዉትቷል፡፡ እኔ የ ዘ ኢኮኖሚስት ያወጣዉን ዝርዝር በሰንጠረዥ ለማሳዬት እንሞክራለሁ፡፡

ሙሉ በሙሉ ዲሞክራሲ ሰፍኖባታል ብሎ ያወጣት ሞሪሽየስ ብቻ ስትሆን እርሷንም በደማቅ አረንጓዴ ቀለም አቅልሚታል፡፡ሌሎችን እንደነ ጋና ያሉትን ዲሞክራሲ እያበበባቸዉ ብሎ ሲጠራቸዉ እንደነ ሊቢያና ግብጽ የመሳሰሉትን ዲቃላ ዲሞክራሲ ብሎአቸዋል፡፡ የእኛን ሀገር ኢትዮጵያንና ጎረቤታችን ኤርትራን አምባገነን ስርዓት የሰፈነባቸዉ ሲል ገልጾ ሱማሌን ግን «የጨነገፈች ሀገር» ብሎ ሰይሟታል፡፡ እኔ በበኩሌ የአገሬ ሁኔታ አሳስቦኛል፡፡ በእድገት፣ በገቢ ማነስ በዴሞክራሲ እጦት፣ በአፈና አገዛዝ እስከመቼ ታንቀን እንኖራለን? ትናንት ከተፈጠረችዉ ደቡብ ሱዳን ማነስና ከተቀናቃኞችን ኤርትራ አለመብለጣችን በእጅጉ የሚያስቆጭ ነው፡፡ መንግስታችንም ቢሆን ይህ ነገር ሊያበሳጨዉና ሊያንገበግበዉ ይገባ ነበር፡፡ አፄ ኃይለ ሥላሴም እኮ የተራበዉን ህዝብ መራቡን የደበቁት የዉጭ ሰዉ እንዳይሳለቅባቸዉ ነበር፡፡ ስለዚህ አቶ መለስም ቢሆኑ ይህንን ነገር በመደበቅ ሳይሆን በመለወጥ ስማቸዉን ቢያድሱትና የመጀመሪያዉ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መሪ ቢባሉ እኔ ምኞቴ ነዉ፡፡ አለበለዚያ «ምከረዉ ምከረዉእምቢ ካለ...» በማለት የሚተርት ህዝብ ነዉ ዝም ያለዉ፡፡

ጠቅላይ ሚንስትር መለስ “በቀን ሶስት ጊዜ ትበላላችሁ” ካሉት የተስፋ ዳቦ በስተቀር ኢህአዴግ እንደገባ የነበረዉ ሁኔታ እንዳለ ነዉ፡፡ መቼም አንድ ከኢህአዴግ የተማርኩት ቁም ነገር ቢኖር በቃል አለመገኘት ነዉ፡፡ ለምሳሌ በቀን ሶስት ጊዜ ትበላላችሁ በተባለ በ20 ዓመታችን አንድ ጊዜ እንኳን መብላት አቅቶን እየተቸገርን ነዉ፡፡ “እንከን የለሽ ምርጫ እናደርጋለን” በተባለ ማግስት ሀገሪቱ እንከን በእንከን ሆነች፡፡ በደም ተጨማለቀች፡፡ በምርጫ ማግስት የገባነው ወደ ልማት ሣይሆን የአገዳደሉን ሁኔታ ወደ ማጣራቱ ነው፡፡ የመናገር የመጻፍ መብታችሁ ይጠበቃል በተባለ ማግስት ይሄዉ በአሁኑ ሰዓት ህገመንግስቱ የሰጣቸዉን መብት ጠብቀዉ እየተናገርን ነዉ በተባሉ ሰዎች “የሽብር ሴራ ሲያሴሩ ተያዙ” በሚለዉ ሰበብ በየስር ቤቱ እንደሚገኙ ምስክር አያሻም፡፡ ይህ ሁሉ አፈና የተደረገበት ህዝቡ እየጮኸ እንጂ እየተንጫጫ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ለበርካታ ጊዜና ወቅት ወልዶ ባስተማራቸዉ ልጆቹ (የወቅቱ ካድሬዎች) በመሆናቸዉ ብቻ ሲበደል ኖሯል፡፡ ነገር ግን እየተበደለ ሲጮህ ሰሚ አጥቶ በዳዮቹ ሲሾሙ ሲሸለሙ ሲወደሱ ኖረዋል፡፡ እነዚህ ካድሬዎች የህዝቡን ምሬት ከራሱ ከህዝቡ እየዘረፉ አንዱ ደላላ አንዱ ነጋዴ በመሆን የራሱን መልሶ ለራሱ በመሸጥ ህዝቡን አደህይተዉ እነርሱ ከበሩ፡፡ ህዝቡ ከእለት ወደ እለት የተጎሳቆለ ኑሮ ሲኖር እነርሱ ያለችግር ደልቷቸው የተንደላቀቀ ኑሮ ይኖራሉ፡፡ ህዝቡ በኑሮ ዉድነት ልጆቹን ዳቦ አብልቶ የህዝብ ትምህርት ቤት ልኮ ማስተማር አቅቶት ካድሬዎቹ ግን ከደመወዛቸዉ እጠፍ በላይ እየከፈሉ በሀገሪቱ ዉሥጥ እጅግ ዉድ ከሆኑ ትምህርት ቤቶች ልጆቻቸዉን ያስተምራሉ፡፡ በርካታ ካድሬዎችና የወቅቱ ባለስልጣናትና የባለስልጣናት ወዳጆች በሀገሪቱ ዋና ከተማ ትላልቅ ፎቆችን አሰርተዉ ተንደላቀዉ ሲኖሩ ህዝቡ ተበድሎ ሲጮህ “አትንጫጫ ይባላል፡፡ህዝቡ ጮኸ እንጂ አልተጫንጫም፡፡ ዛሬም ቢሆን እየጮኸ እንጂ እየተንጫጫ አይደለም፡፡

## የእኛን ቀሺ ገብሩዎችንና አሞራዎችን ፊልም ሰጡን

ሐሳቡ የተከበሩ የአቶ ግራማ ሴይፉ ነው፡፡ ባለፈው ዕሮብ ምሽት በአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት ለህሊና እስረኞች በተደረገ የሻማ ምሽት ላይ ከተናገሩት የተወሰደ ነው፡፡ ሐሳቡ ቃል በቃል ባይሆንም እንዲህ የሚል ነው፡፡ “ኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ስለ ቀሺ ገብሩና ስለአሞራው ዶክመንተሪ ፊልም ሠርቶ አሳይተውናል፡፡ የዓላማ ጽናታቸውን ነግረውናል፡፡ ዓላማቸው ምንም ይሁን ምን የከፈሉትን መስዋዕትነት አደንቃለሁ፡፡ ኢቴቪ የተጠቀመበትን መንገድ ግን አልደግፍም፡፡ ዛሬ ሻማ የምናበራላቸው የእኛ ቀሺ ገብሩና አሞራዎች አሉን፡፡ በኢህአዴግ እስር ቤት ታስረው ቀንና ሌሊት እየገረፉ የቀረጧቸው፡፡ በሐሰት መስክሩ፤ ያልሠሩትን ሠራን ብላችሁ እመኑ፤ ንጹሕንን ወንጀሉ እየተባሉ የተቀጠቀጡ፡፡ ተደብቀው የተቀረጹትን ፊልሙን ይስጡን”

“ጫካም እያሉ የኢትዮጵያ ሠራዊትን ሲማርኩ እየቀጠቀጧቸው የቀረፃ◯ቸውስ የለም? የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለብሶ ለአገሬ ዳር ድንበር፣ ለአገሬ ሉዓላዊነት እሞታለሁ፤ እያለ እየፎከረ፤ የሞተ፤ አካለ ጐዶሎ የሆነ፤ ወታደር የለም? እጄን ለወንበዴ አልሰጥም! አገሬ አትቆረስም! የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ቀይ ባህር ነው፤ እያለ የሞተ የለም? ፊልሙን ቢሰጡን” የሚል ሐሳብ ያለው ነው፡፡

አቶ ግራማ እውነት ብለዋል፡፡ እኔም ከሰማሁትና ካነበብኩት ትዝ አለኝ፡፡ “ዳግማዊ ቴዎድሮስ” የተባለላቸው ኰሎኔል ማሞ ተምትሜ፣ እጄን ለወንበዴ አልሰጥም ብለው ራሳቸውን በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጠቅልለው ቀይ ባህር ላይ የሞቱት፣ ጄኔራል ሰለሞን ተሰማ፤ ጀግናው ኰሎኔል በላይ አስጨናቂ፣ ኰሎኔል ግርማ አስፈሩ - - - - - በህሊናዬ ታወሱኝ፡፡ የዛሬውም የነገውም ትውልድ እንዲያውቃቸው ለምን ፊልሙን አይሰጡንም? እነዚህ ጀግኖች የኢትዮጵያ ህዝብ አሞራዎች ቀሺገብሩዎች ናቸው፡፡ የዛሬው ትውልድ ሳይሆን የነገው ትውልድ የሚዘክራቸው ጀግና ናቸውና!!

## ኢቴቪን ተመልከት!

አንድ አዛውንት ፒያሣ አካባቢ ካንዲት ጥግ ቦታ ላስቲክ ቢጤ ወጥረው የተበላሹ መነፅሮችን ይጠግናሉ፤ ፍሬሞችን ይሸጣሉ፤ እንዲሁም አዳዲስ የፀሐይ መነፅሮችንም በመሸጥ የታወቁ ናቸው፡፡ በዚህ የሥራቸው ፀባይ በርካታ ገጠመኞች እንዳሏቸው ይናገራሉ፡፡ ከገጠመኞቻቸው መሀከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ግራ የገባው ወጣት ከሚሰሩበት ይሄድና “አባባ የወደ ፊት እጣ ፈንታዬን የሚያሣይ መነፅር አለዎት?” ሲል ይጠይቃቸዋል፡፡ አዛውንቱ ሣቅ አሉና “ሰማህ ልጄ ያንተን የወደፊት እጣ ፈንታ የሚያሳህ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ነው፡፡ እሱን ተመልከት!!” አሉት፡፡

# የኢህአዴግ ጥንካሬ ወይስ የተቃዋሚዎች ድክመት

ብስራት ወ/ሚካኤል
afrosonb@gmail.com

አንድ የመንግስት ሥርዓት ዘለዓለማዊ ሊሆን አይችልም፤ ሆኖም አያውቅም፡፡ ነገር ግን ጊዜ የሰጣቸው ገዥዎች ካድሬዎቻቸውን ዘለዓለማዊ እንደሆኑ አድርገው ይነግሯቸዋል፡፡ ጀሌ ካድሬዎችም እውነት ነው ብለው በመቀበል አለቆቻቸው ከሌሉ ሀገር፣ ህዝብም ሆነ ራሳቸው እንደሌሉ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ ይሄ ደግሞ ከሰውአዊ (ፍጡራዊ) አስተሳሰብ ፍጹም የራቀ ነው፡፡ አምነው የሚቀበሉትንም አእምሮ እንዳለው ፍጡር ሳይሆን እንደ ህይወት አልባ ዕቃ የመቁጠር ያህል ነው፡፡ ምክንያቱም አይደለም የመንግስት ሥርዓት፤ ዘለዓለማዊ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ሁሉም ፍጡር ይወለዳል፤ ያድጋል፤ ይሞታል የሚባለው፡፡

በኢትዮጵያም በተጨባጭ እየታየ ያለውም ይሄው ነው፡፡ ያለፉ ሥርዓቶች ሁሉ ሊወድቁ ሲሉ በመጨረሻ ራሳቸውን ለመከላከል ሲሉ ለህዝቡ የቤት ሥራ ይሰጡና ውስጣቸውን ለመገንባት ላይ ታች ይላሉ፡፡ ከዚያም የሥርዓቱ መውደቅና መፍረክረክ ሲረጋገጥ ቅድሚያ እረፍት ይሰጠን ይሆናል" በሚል ዋና ተቀናቃኞቻቸውን፣ በህዝቡ ተቀባይነት ያገኙትንም ስም በማጥፋት ማሰር፣ ማንገላታትና ማስፈራራት አሊያም ከቻሉ በስውርም ቢሆን የሞትን መስዋዕት ለማቅረብ ይሞክራሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የማይሳኩ ከሆነ የውጭ ሀገር መንግስታት ላይ ጣት መቀሰር ይጀምራሉ፡፡ የተጠቀሱት ሁሉ የማያስኬዱ ከሆነ የመጨረሻው እርምጃ የሚሆነው በራሱ በገዥው መደብ ውስጥ ተመሳሳይ የሥልጣን ደረጃ ያላቸውን በመካከላቸው የበላይና የበታች በማድረግ ዕድላቸውን ይሞክራሉ፡፡

ይሄ ደግሞ ጦሱ ምንም ለማያውቀው ሰፊው ህዝብ ይተርፋል፡፡ በዚህ ጊዜ ጠንካራና የተደራጀ የፖለቲካ ፓርቲ ካለ ህዝቡን ለመታደግ ይዘጋጃል፡፡ የአካሄድ ስልቱን ከላይ ያሉት የገዥዎችን ድክመት ተጠቅሞ ራሱን ለመሪነት ያዘጋጃል፤ የሀገርንም ደህንነት ያስጠብቃል፡፡ ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሱት ከታዩ የገዥው መደብ ፍጻሜ ብስራት ስለሆነ የህዝቡንም ንቃት ህሊና ከፍ ያደርግና ከተቀባይነት ወደ ጠያቂነት (ለምን?) ወደሚለው ተሸጋግሯልና፡፡ ይሄኔ የግድ ቁርጠኛ የሆነና በሚከተለው ህጋዊና ሰላማዊ ትግል የሚተማመን አካል አካሄዶቹን በማጤን የራሱን የሚያዋጣውን እርምጃ ይወስዳል፡፡ አለበለዚያ በህዝቡ ተዓማኒነት ያለው ፓርቲ ይህን የማያደርግ ከሆነ ተቀባይነቱ እየወረደ ይመጣና ገዥው እንደገና እንዲያንሰራራ ዕድል ይሰጠዋል፡፡

የኢህአዴግ መፍረክረክ

የአንድ አካባቢን ህዝብ ወክያለሁ ብሎ የትጥቅ ትግል ያነገበና በመጨረሻም በለስ ቀንቶት ስልጣን ከያዘ በኋላ (ከ1983 ዓ.ም ማለቂያ ጀምሮ) ብዙ ፈተናዎች መጥተውበት የተለያየ የኃይል አስተላለፍ ተጠቅሞ እዚህ ደርሷል፡፡ ያም ቢሆን ግን ከሥጋት ሊያመልጥ አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት በተለያየ ጊዜ ከሚናገራቸው አቋሞች ውጭ መንገድ እየሳተ በመሄዱ በቀደምት አባሎቹ እምነት በማጣቱ መሠረቱ (ህወሓት) ለሁለት እንዲከፈል አስገድዶታል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የህወሓት /ኢህአዴግ ከፍተኛ አመራሮች ከትግራይ ተወላጆች የህወሓት ታጋይ ይልቅ እስከ 1990 ዓ.ም እምነት ያላቸው ሻዕቢያ (ኤርትራውያን) ላይ ነበር፡፡ የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እስኪካሄድ ድረስ በአብዛኛው ከፍተኛ የመንግስት አመራር እስከ ቀበሌ መስተዳደር (በተለይ አዲስ አበባ) የነበሩት ኤርትራውያን ነበሩ፡፡ ይህ ሲባል ግን አሁንም ኢትዮጵያን ከሚያስተዳድሩት ከፍተኛ የመንግስት አመራሮች የሉም ማለት አይደለም፡፡ የሚገርመው ያሉት አመራሮችም ቢሆኑ የሚሰሩት ለኤርትራውያንም ሆነ ለኢትዮጵያውያን ጥቅም ሳይሆን ለራሳቸው ጥቅም ነው፡፡

ከ1992 ዓ.ም ውጤት አልባ ጦርነት በኋላ የተረሱት የህወሓት ታጋዮች ተሳቡ፤ ከዚያም ኢህአዴግን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንም ያለምንም ተቀናቃኝ የመሪነቱን ሥፍራ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ተቆጣጠሩት፡፡ እነሱም ቢሆኑ ለትግራይም ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም መቆም አልቻሉም፡፡ በመሀል በተፈጠረው ጦርነትና ውጤቱ እንዲሁም የአቶ መለስ የበላይነት ማሳያ "ቦናፓርቲዝም" ቅንቀና በ1993 ዓ.ም ህወሓት ለሁለት ተከፈለ፡፡ "የስየ እና የመለስ" ቡድን በሚል፡፡ የነ አቶ ስየ ቡድን የሀገር ጥቅም ላይ ያቀነቀነ እንደሆነና የአቶ መለስ ቡድን ደግሞ የግለሰብ (የአቶ መለስ) የሐሳብ የበላይነት ላይ ያነጣጠረ ክፍፍል እንደነበረ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ "ነፃነትና ዳኝነት በኢትዮጵያ" በአቶ ስየ አብርሃ "ከሀገር በስተጀርባ" በአስራት አብረሃም እና "የሁለት ምርጫዎች ወግ" በአቶ በረከት ስምዖን የተፃፉት መፅሐፎች ገልፀውታል፡፡ በዚህ ጊዜ ለነ አቶ መለስ "ህወሓት" ታማኝ የነበሩት ብአዴኖች ናቸው፡፡ በተለይ ተሰናባቾቹ የሰመ ብአዴን አመራሮች አቶ አዲሱ ለገሰ እና አቶ ተፈራ ዋልዋ የአቶ መለስና ቡድናቸው የቀኝ እጅ በመሆን ታድገዋቸዋል፡፡ ይሄም እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ ቀጥሎ ነበር፡፡

በህወሓት እና በአቶ መለስ ታማኝነት ወደር ያልተገኘለት ብአዴን በግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ምርጫ የተጠበቀውን ሚና መጫወት አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ኢህአዴግ በከፍተኛ ደረጃ በመፍረክረኩና ሀገርም ሆነ ድርጅቱን መምራት ባለመቻሉ በወቅቱ ገና ከተመሠረተ 6 ወር የሆነው ቅንጅት (የቀድሞው) ትልቅ ፈተና በመሆን ያልተጠበቀ ውጤት ሊያመጣ ችሏል፡፡

ብአዴን

ብአዴን የተጠበቀበትን ተዓማኒነት ለአቶ መለስ ባለመወጣቱ ሌላ የቤት ሥራ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ይህም የምርጫ 1997 ዓ.ም ውጤትን ተከትሎ እነ አቶ ተፈራ ዋልዋ ተጨማሪ የቤት ሥራ ተሰጣቸው፡፡ ከዚያም በተመሰቃቀለና በተዋከበ ሥራ አመራሮቹ በየክልሉ በመዘዋወርና በፕላዝማ ቴሌቪዥን የአባላት ምልመላና የውጤት ማስቀልበሻና ማስቀየሻ ሥራ ተካሄደ፡፡ ክንውኑም በ1998 ዓ.ም ሲሆን መጀመሪያ ለራሱ አባላት፣ መቀጠልም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመራቂ ተማሪዎች ከዚያም ለሀገሪቱ የመንግስት ሰራተኞች በመጨረሻም ለገበሬው ማኅበረሰብ በልማት ስም የፕሮፓጋንዳ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ይህን እውነታ አቶ በረከት ስምዖን "የሁለት ምርጫዎች ወግ" በሚል መፅሐፋቸው ቅንጭብጫቢውን ገልፀውታል፡፡

እነ አቶ መለስ በዚህ ጊዜ በብአዴን ላይ ሙሉ እምነት ስላልነበራቸው እሳቸውም በተመሳሳይ ሥራ ተጠምደው ነበር፡፡ ስጋት ናቸው ያሏቸውን የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ታጋይ አባላት የጦር መኮንኖች ላይም "ህጋዊ ማዕቀፍ" በማበጀት እርምጃ ወሰዱ፡፡ ያሰጉኛል ያሉትንም አሰሩ፡፡ እስከዚህ ድረስ ብአዴን ከሌሎች የኢህአዴግ ድርጅቶች ህወሓት፣ ኦህዴድ እና ደኢህዴን ይልቅ ለአቶ መለስ ታማኝ ነበር፡፡

በ1997 ዓ.ም የተሰጠውን የቤት ሥራ በብቃት ያልሰራው ብአዴን እና አመራሮቹንም በሂደት ከ2002 ዓ.ም ምርጫ በፊት የማርገፍገፍና የማሰናበት እርምጃ በአቶ መለስ ተወሰደ፡፡ እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት የብአዴን አመራሮች ከስልጣን ሲሻሩ እንዳያንገራግሩ በቅድሚያ የብአዴን ታጋይ አመራሮች (የሚፈሩት) ሰራዊቱ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ያላቸው እድል የሚሰጣቸውን ውሳኔ ከመቀበል ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ የብአዴን ለአቶ መለስ ታማኝነትም ከ2002 ዓ.ም ምርጫ በፊት አበቃ፡፡ ብአዴን ቀድሞም ቢሆን በአማራ ህዝብ ስም የተቋቋመ በህወሓት አማካኝነት ለኤርትራ ጥቅም አቀንቃኞች የሚሰራ እንጂ

ወደ 11 የዞሯል

# በርሜሉ ቀዳዳ ከሆነ ውሃው አይሞላም

ሰለሞን ስዩም

ማስታወሻ

ይህንን ፅሁፍ በፍኖተ ነፃነት የኤዲቶሪያል ስብሰባ ላይ ለዚህ ዕትም ያስያዝኩት ማክሰኞ ሚያዚያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ነዉ፡፡ ዓርብ ሚያዚያ 5 ቀን 2004 ዓ.ም በወጣችዉ ፍትህ ጋዜጣ የወጣዉን የተመስገን ደሳለኝ ፅሁፍ ሳነብ ፈረንጆቹ «ሳይክክ ፓወር» ወይም በሀሳብ መገጣጠም የሚሉት ነገር ታውሶኛል፡፡ ለማንኛዉም ይንን ፅሁፍ የተመስገንን ካነነብኩ በኋላ ማሻሻል ጣዕሙን ማበላሸት በመሆኑ እነሆ እንደወረደ፡፡

በኢመደበኛ ወግ ሁለት ቡድኖችን ልፍጠር፡፡ አንደኛውን ወገን በዚህ ስርዓት ቢደሰትም ባይደሰትም ቁሳዊ ጥቅም በማግኘቱ መኖሩን የሚመኝ እና የሚሰራ ነው እንበል፡፡ ሌላውን ቡድን ደግሞ በደምሳሳው ያለውን ስርዓት በሆነ ምክንያት የማይፈልግ ነው ብዬ ልዉሰድ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ለመብዛት እና ሁለታኞቹን ቡድኖች ለማፈን አንድ ተጨማሪ ዕድል አላቸው፤ ይህውም እነዚህ ቡድኖች ባላቸው የዘቀጠ ስብዕና ከዋናዎቹ የአስተዳደር ሰዎች ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ በመሆኑም የጥቅም ተጋሪነታቸው ከፍላጎታቸው መመሳሰል የመነጨ ይሆናል፡፡ ሌላው የነዚህ ቡድኖች ተጨማሪ ዕድል የስብዕና ዝቅጠት ያለባቸውን ምልምል አባላት የማፍራት ሰፊ ዕድላቸው ነው፡፡ አንድ ማህበረሰብ "አምኖ" የወከላቸውን ሰዎች ብዙ ነገር ይጠብቅባቸዋል፡፡ "ታምነው" የተወከሉ ሰዎችም በተጠበቁት መጠን እና ላሉበት ደረጃ የመመጠን (role behavior) ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ነገር ግን ይህን ሳያደርጉ የሚቀሩበት አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ይህ በወካዮች ዘንድ የመከዳት ኃሊዮች (Betrayal theory) ውስጥ እንደሚከታቸው ይታወቃል፡፡ የመከዳት ስሜት የመጀመሪያው እርምጃ የከጂውን ስብዕና በመውረስ ለመበቀል መሞከር ነው፡፡ ባሏ ሌላ ሴት ያማገጠባት ሚስት ምግባሩን በመድገም ልትበቀለው ትፈልጋለች፡፡ ሙሰኛ መሪዎች ያፈሩት ሙሰኛ ስርዓት ያንዥበባቸው ማህበረሰቦችም ያንኑ ፀባይ በመድገም የመካደድ ስሜታቸው ለመበቀል ይሞክራሉ፡፡ በዚህ የተነሳ መሆን አለበት የዘመኑ ምሩቆች ገና ከመቀጠራቸዉ በፊት ነዉ የሚቀጠሩበት መስሪያ ቤት ለምስበራ ያመች እንደሆነ የሚያጠኑት፡፡

በመሆኑም የስርዓቱን መኖር የማይፈልገው ሰዎች ቁጥር በዚህ መልኩ ይመነምናል፡፡ ስርዓቱን ያከትም ዘንድ የምንሰራው ቡድኖች አንደኞቹ ጎራ የሆነዉ በመገናኛ ብዙሃን የምንሰራዉ ሰዎች ነን፡፡ ይህ ዘርፍ እጅግ ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆኑን ደግሞ ከኛ ይልቅ ስርዓቱ ያውቀዋል፡፡ በመሆኑም ህልውናውን ለማረጋገጥ ሴራ መሸረብ ባህሪው ነው፡፡ የመለስ ዜናዊ መንግሥት ከደርግ የሚለየው የኃሳብ ልዩነቶችን በሆደ ሰፊነት በማስተናገድ ያለመሆኑን አንድ ሁለቴ ፅፌያለሁ፡፡ ደርግ በመግደል የመለስ ዜናዊ መንግሥት ደግሞ በማሳደድ ብቻ ይለያያሉ፡፡ ለነፃና ልዩ ሀሳብ ግን ሁለቱም አላርጂክ ናቸው፡፡ ከጦር መሣሪያ ባልተናነሰ መልኩም በሳል ቃለ ነቢቦች (Rhetorics) ያስደነግጣቸዋል፡፡ እንግዲያውንስ አንድ ነገር ስተናል፡፡ በዚህ ዘርፍ ያለነው ሰዎች የኢህአዴግን ሽበባ፣ እስርና እንግልት በመፍራት የመሰደድ እድል 'የምንጠቀም' ከሆነ ሰፊ ቀዳዳ ባለው በርሜል ላይ የከፈትናት ውሃ እንዲትሞላ እንደመጠበቅ ነው፡፡

ወደ በርሜሉ የሚወርደውና ከበርሜሉ የሚወጣው ዉሃ ተመጣጣኝ እንኳ ቢሆን በውሃዉ መጠን ላይ ለዉጥ አይኖርም፡፡ ወደ በርሜሉ የሚወርደው ዉሃ የሚወጣውን በትንሹ ቢበልጥ የመሙያውን ጊዜ ያራዝማል፡፡ ውሃው ቶሎ እንዲሞላ በርሜሉ የተንቦረቀቀ ቀዳዳ ይቅርና ሽንቁር እንኳ ሊኖረው አይገባም፡፡ በትግላችን ላይም እንዲሁ፡፡

የዳዊት ከበደ መሰደድ ኢህአዴግ ላይ ምን ጫና አመጣ? «ዳዊት ከበደ ተሰደደ» ብለን ዜና ሰራን፣ ዳዊት አንድ ሁለቴ ፅሁፍ ላከ፤ በቃ አከተመ፡፡ የአዲስ ነገር መዘጋት እኛን ከመረጃና ትንተና ከማፋታት የዘለለ ኢህአዴግ ላይ ያደረሰዉ 'ጉዳት' ምንድነዉ? አዲስ ነገር ብትኖር መንግስ በስንቱ ይጨነቅ እኮ ነበር! እርግጠኛ ነኝ ቃሊቲም ቢሆኑ ከሚፅፉት ፅሁፍ ያልተናነሰ ያስጨንቀዉ ነበር፡፡ አርጋዉ አሸኔ በመሰደዱ የኢህአዴግ ስልጣን ጫና ዉስጥ ይገባል? «ስደት በጋዜጠኛዉ አይን» የኢህአድግን እድሜ ስንዝር ያህል ይቀንሳል?

የኔ ምርጫ

የኔ ምርጫ ቃሊቲን መሙላት ነዉ፡፡ የኛ ቃሊቲን መሙላት ኢህአዴግን ከብርሃኑ ነጋ ግንቦት ሰባት የባሰ እንቅልፍ ይነሳዋል፡፡ ኢህአዴግን የከበደው አንዳርጋቸው ፅጌ ሳይሆን ልቡናዬ ንፅህናውን የሚያምንለት እስክንድር ነጋ ነው፡፡ እስክንድር ፖለቲካ ተነተነ ሊያነቃን ተነሳ፤ አንዷለም «ሁሉንም በፍቅር መማረክ ነዉ» ብሎ ከፖለቲካዉ የተሸሸግነዉን ወጣቶች ወደዚያዉ ሊያተመን ገባ፡፡ ከሙልነህ ኢዮኤልም፣ ከመስፍን ነጋሽም፣ ከዐብይ ተ/ማሪያምም በላይ የአንዷለምና የናትናኤል ቃሊቲ መሆን የኢህአዴግን ዕድሜ ያሳጥራል፡፡ ከሰሞኑ የተጀመረችው ዘመቻ የነዳዊት ከበደን፣ የነነፃነት ደምሴን፣ የነዐብይ ተ/ማርያምን፣ የነግርማዉ ተስፋሁንን፣ የነታምራት ነገራን መንገድ ለማመቻቸት የተቀነባበረች ናት፡፡ አሁን ደግሞ የመንግስት የእግር እሳት የሆነችዉ ፍትህ ናት፡፡ ከንግዲህ መንግስት ፀረ ነጻ አስተሳሰብና አብዮታዊ ዴሞክራሲን ይዞ ፍትህን አይታገስም፡፡ ተመስገንን ግን አንድ ነገር ልምከረው! አትሰደድ፣ እንዲህ ብለህ እግርህን አታንሳ! "ጀግና አድርገው እንድፈጥሩህ፤ እድሜያቸውን አሳጥረህ የሰቆቃ ጊዜያችንን እንድታቀርብልን ፋሲካችን ሁንልን! እንዲህ ብለህ አትሰደድ! ያንተ መሰደድ

ወደ 15 የዞሯል

# አዲሶቹ "ቀሺ ገብሩዎች" በሻማ ምሽት ታወሱ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ወር በገባ በሦስተኛው ቀን የሚያረገውን የእስረኞች ማስታወሻ የሻማ ምሽት አከበረ፡፡ ፓርቲው የታሰሩት የፓርቲው አመራር አባላትና ጋዜጠኞች በሀገሪቱ ካለው የህሊና እስረኞች ምድብ መሆናቸውን አስታውቋል፡፡ ፕሮግራሙን በንግግር የከፈቱት የፓርቲው የፓለቲካ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሙላት ጣሰው "ታሳሪዎች በነፃነታችንና በማብታችን አንደራደርም" ያሉ የነፃነት አርበኞች መሆናቸውን አስታውሰው "እነዚህን የትግል ፈላጊዎች አይቶ ዝም ማለት ትግሉ ሲጀመር የተገባውን ቃል መርሳት ነው" ብለዋል፡፡ አቶ ሙላት በንግግራቸው መዝጊያ "አምባገነኖች ንፁሐንን ወንጀለኞች አድርገው ሲያቀርቧቸው ህዝብ ሲያሸነፍ በአለም እና በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት ለፍርድ ይቀርባሉ"ሲሉ ደምድመዋል፡፡

የፓርቲው የብሔራዊ ም/ቤት ሰብሳቢ መ/ር ዘካርያስ የማነብርሃን በበኩላቸው "ኢህአዴግ በነበረው የምርጫ 97 ክርክር አቶ በረከት "በብልቃጥ ውስጥ የዘጋንበትን ጅኒ እናንተ ልታወጡት ትፈልጋላችሁ" ማለታቸውን አስተውሰው አሁንም ያንኑ ለማድረግ የነፃነታችንን ጅኒዎች እስር ቤት ከቷቸዋል" ሲሉ ግልፀዋል፡፡ መ/ር ዘካርያስ "ኢህአዴግ አውራ ፓርቲ ነኝ" ቢልም ህዝቡ "አውሬ ፓርቲ ነህ" ማለት መጀመሩን አውስተው ከዚህ አይነቱ አሳተዳደር ከዚህ የሚሻል ነገር ከመጠበቅ በታሰሩት ጀግኖች በመቅናት ትግሉን እስከ ቀራኒዮ መውሰድ ነው" በማለት ተናግረዋል፡፡

በመቀጠል የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ ባደረጉት ንግግር "ETV ላቀረበልን አሞራውና ቀሺ ገብሩ አድናቆታቸውን ከገለፁ በኋላ የኛዎቹ ቀሺ ገብሩና አሞራዎችም ተመጣጣኝ ክብር እንደሚገባቸው ተናግረዋል፡፡ የተከበሩ አቶ ግርማ "በርግጥ ኢቴቪ ሀቀኛ ቢሆን ኢህአዴግ ማርኮ ያናገራቸው እና እምቢ ለሀገሬ በማለት ባንዲራ ለብሰው የተረሸኑትን የኢትዮጵያ ወታደሮች ፊልም ሊሰጠን በተገባ ነበር" ብለዋል፡፡ በመቀጠል ወ/ሪት ብርቱካን በታሰረች ጊዜ ኢህአዴግ "ንግስቲቱን ፈትቶ ነፃ ይወጣ" ተብሎ መመከሩን አስታውሰው አሁንም እነ አንዱአለምን በመፍታት ከጭንቀት መገላገል እንዳለበትና ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ እንዳለበት አስታውሰዋል፡፡ በፕሮግራሙ ላይ የተገኙትንም ሰዎች ያደነቁ ሲሆን "እኛ ነፃ አውጪዎች ሳንሆን የነፃ ሰዎች ስብስብ ነን" ካሉ በኋላ በዚህ ሁኔታ እየበዛን ስንሄድ በኛና በደህንነት ሰዎች መካከል ያለው የቁጥር ምጣኔ "ወደኛ ማድላቱ አይቀርም" ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በመጨረሻም "ቻይናውያንን መውረር አይቻልም" ያሉት አቶ ግርማ "እጅ ስለሚሰጡ ትርፉ እነሱን መቀለብ ነው" ካሉ በኋላ "እኛም ለማሸነፍ ቻይኖች መሆን አለብን" ሲሉ ደምድዋል፡፡

ሌላው ተናጋሪ የድርጅቱ የሕግና ሰብአዊ መብቶች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ደምሴ መንግስቱ በበኩላቸው የታሳሪዎቹ ለዚህ መብቃት የኢህአዴግ ባለስልጣናት በህግ ላይ ያላቸው ግንዛቤ መሆኑን ገለፀው ባላቸው የሕግ ግንዛቤ በሦስት እንደሚመደቡ አብራርተዋል፡፡ አቶ ደምሴ የኢሕአዴግ ባለስልጣናት አንድም ያወጡትን ህግ እያውቁም ሁለትም የሚያውቁ ግን ለራሳቸው የሚጠቀሙ ሶስተኞቹ የተምታታባቸው መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

በዕለቱ የመጨረሻው ንግግር ያደረጉት የድርጅቱ ዋና ፀሐፊ አቶ አስራት ጣሴ በበኩላቸው "እነ አንዱአለም በሽብር ሲከሰሱ ሳይ ማን አሸባሪ አይሆንም? እላለሁ" ያሉ ሲሆን በነ አልቃይዳ፤ በነ አልሸባብ ህግ ሲከሰሱ ማየት የሚያም መሆኑን አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡ አቶ አስራት በማከል ሽብርተኝነትን ለመረዳት ሶማሊያ፤ አፍጋኒስታንና ነይጄሪያን ማሰብ እንደሚገባ አስታውሰው "እነ አንዱአለምን በዚህ ህግ መክሰስ በሽብርተኝነት በተጠቁ ሰዎች ላይ መቀለድ ነው" በማለት ንግግራቸው አጠናክረዋል፡፡ አቶ አስራት በመጨረሻም "ነፃነት በነፃ አይገኝም፤ በነጻ የሚገኘው ባርነት ብቻ ነው" በማለት በቁርጠኝነት መታገል እንደሚገባ በማስገንዘብ ንግግራችን ፈጽመዋል፡፡

በእለቱ ግጥሞች፣ መነባንቦችና ዲስኩሮች የተደመጡ ሲሆን የታሳሪ ቤተሰቦች፣ወዳጆችና ጓደኞች እንዲሁም የድርጅቱ አባላት በመገኘት ዝግጅቱን በድምቀት ማክበራቸው ታውቋል፡፡

# እስክንድር ነጋ ለዓለም አቀፍ ሽልማት ተመረጠ

ጋዜጠኛና የፖለቲካ ተንታኙ እስክንድር ነጋ አሜሪካን አገር ከሚገኘው የፔን ኢንተርናሽናል ድርጅት 2012 ዓለም አቀፍ ተሸላሚ ሆኖ መመረጡን የዜና አውታሮች እየዘገቡት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የግል ጋዜጣ መሥራች የሆነው እስክንድር ነጋ እስከ ምርጫ 97 ድረስ ከዓለም አቀፍ ተሸላሚዋ ባለቤቱ ሰርካለም ፋሲል ጋር ሚኒሊክ፣ አስኳልና ሳተነው የተሰኙ ጋዜጦች እንደነበሯቸው ይነገራል፡፡

እስክንድር ነጋ በኢትዮጵያ ነፃ ሚዲያ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ያለው ሲሆን "ኢትዮጲስ" የተሰኘውን የመጀመሪያውን ጋዜጣ ባለቤት ሲሆን በዚሁ ጋዜጣ ምክንያት ዛሬ በህይወት ከሌላው ጋዜጠኛ ተፈራ አስማረ ጋር በተደጋጋሚ ለእስራት ተደርጓል፡፡ ኢትዮጲስ ጋዜጣ ከተዘጋ በኋላ ባለቤቱ ፍቃድ አውጣታ ባወጣቸው ጋዜጣ ላይ በጋዜጠኝነት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ አንድ ዓመት ከአስራ አንድ ወር ታስሮ በነፃ ተለቋል፡፡ እስክንድር እስከ ምርጫ 97 ድረስ ሰባት ጊዜ የታሰረ ሲሆን ሰባቱንም በነፃ መለቀቁን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ይገልፃሉ፡፡ እስክንድር እስከ ዛሬ ድረስ በነጻ ሚዲያው ላይ ላደረገው አስተዋጽኦ የ "2012 pen Barbra Gold smith freedom to Wright A ward" ተሸላሚ አድርጎ መርጦታል፡፡

ጋዜጠኛና ፖለቲካ ተንታኝ እስክንድር ነጋ ከመስከረም 3 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በ "ሽብርተኝነት" ተጠርጥሮ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ይገኛል፡፡ እስክንድር ሜይ 1 ቀን 2012 አሜሪካን አገር ኒዎርክ ላይ በሚደረገው ዓመታዊ የፔን ጋላ ላይ እስክንድር ወይም ተወካዩ ሽልማቱን ይቀበላል፡፡

# ኢህአዴግን በዘር ማጥፋት ወንጀል ለመክሰስ እየተዘጋጀ መሆኑን መኢአድ አስታወቀ

የኢህአዴግ ባለሥልጣናት በአስቸኳይ ካድርጊታቸው ካልታቀቡ በዘር ማጥፋት ወንጀል በዓለም አቀፍ ፍ/ቤት ለመክሰስ እየተዘጋጀ መሆኑን መኢአድ አስታወቀ፡፡ የመኢአድ አመራሮች ይህንን ያስታወቁት ባለፈው ሐሙስ በጽ/ቤታቸው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ነው፡፡ ፓርቲውን ወክለው መግለጫ የሰጡት የፓርቲው ተቀዳሚ ም/ፕሬዝዳንት አቶ ወንድምአገኘ ደነቀው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዋ ወ/ሪት መሶበወርቅ ቅጣውና የህዝብ ግንኙነት ኮሚቴ ም/ኃላፊ አቶ ጌታቸው አበበ ናቸው፡፡ አመራሮቹ እንዳሉት "እየተፈፀመ ያለው ጥቃት በአንድ ዘር ላይ ያነጣጠረ፣ ከሀብት ንብረት ማፈናቀልና ከመኖሪያ ቀዬ ማሳደድ እንዲቆም እየጠየቅን ይህ ሊሆን ካልቻለ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት በዓለም አቀፍ ፍ/ቤት በዘር ማጥፋት ወንጀል ለመክሰስ ከዓለም አቀፍ የሕግ ባለሞያዎች ጋር እየመከሩ መሆናቸውን" አስታወቋል፡፡

መኢአድ መጋቢት 4 ቀን 2004 ዓ.ም በወጣዉ መግለጫ እንደገለፀዉ "የኢህአዴግ ባለሥልጣናት የህዝብን ጉዳይ ወደ ኃላ በመተው እውነታውን ደብቆ ኢህአዴግ በሚታወቅበት በተራ ዶክመንተሪ ፊልም ፕሮፓጋንዳ ዝግጅት ላይ መጠመዳቸው በእጅጉ አሳዝኖናል" በሚል ርዕስ ባለ አራት ገጽ መግለጫ አውጥቷል፡፡ መግለጫው በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ( መኢአድ )በደቡብ ክልል በቤንቺ ማጂ ዞን በጉራፋርዳ ወረዳ ውስጥ በነዋሪዎች ላይ በመንግስት አካላት እየተፈጸመ ያለውን በአንድ ዘር ላይ ያነጣጠረ ከሀብት ንብረት ማፈናቀልና ከመኖሪያ ቀዬ ማሰደድ እንዲቆም ለሚመለከተው ሁሉ ጥሪ ማድረጉ ይታወቃል፡፡

የፌደራል መንግስትን ጨምሮ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በሙሉ ከድርጊታቸው እንዲታቀቡና ለችግሩ መፍትሄ እንዲሰጡ በተለያዩ መግለጫዎችና ደብዳቤዎች በተደጋጋሚም ጠይቋል፡፡ በክልሉ አሁንም ሰዎች ይሰደዳሉ ፤ይፈናቀላሉ ፤ ከመኖሪያ ቀያቸውና ከእርሻ ቦታቸው እንዲነሱ ይገደዳሉ፤ ይደበደባሉ፤ ይታሰራሉ በጉማሬ ጎማ ይገረፋሉ ፤ በሀሰት ክስ ይከሰሳሉ፤ በቅርቡም እየሩሳሌም በሚባለው አካባቢ በወረዳው የፖሊስ አዛዥ በሳጅን ምስክር ድብደባ በጭብቅላቱ ላይ በደረሰ ከባድ ጉዳት ምክንያት እራሱን በመሳቱ ከመኪና ላይ ወድቆ ህይወቱ ያለፈው የአቶ አባብለው ማሞ አሟሟትም የዚሁ ማስረጃ ነው፡፡ ሌሎች ሁለት ወጣቶችም በጦር ተወግተው በታፋቸውና በሽንጣቸው ላይ በደረሰ ጉዳት ለከፍተኛ ስቃይ ተደርገዋል፡፡

አሁንም የህዝቡ ንብረት በካድሬዎች ይዘረፋል፤ ስድስት ወፍጮ ቤቶች ተነቃቅለው ከአገልግሎት ውጭ ሆነዋል እቃዎቹም ተዘርፈዋል፡፡ 23 ቤቶች ተቃጥለዋል ይላል፡፡ መግለጫው በገጽ ሁለት ላይ ሲዘረዝር ከአካባቢው ላይ ህዝቡ በመሰደዱ ምክንያት ማሪያም ሰፈር የሚገኘውን የማሪያም ቤተክርስቲያን ጽላት(ታቦት) ወደ ወረዳው ቤተክህነት ሚካኤል ቤተክርስቲያን ተወስዷል፡፡ ህጻናትና ሴቶች ለከፋ እንግልትና ስቃይ ፤እንዲሁም ለህክምና እጦትና ለምግብ እጥረት ተጋልጠዋል፡፡ ሆኖም ግን መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ለመፍትሄ ከመንቀሳቀስ ይልቅ ለርካሽ የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል ችግሩ እንዳልተፈጸመ ለማድረግና ለማስተባበል እንዲሁም ሁኔታውን ፈጽሞ ለማዳፈን ከፍተኛ ዘመቻ ላይ መሆኑ ታውቋል፡፡

መጋቢት 02/2004 ዓ.ም. የደቡብ ክልል ፕሬዝደንት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ በጉራፋርዳ ወረዳ ውስጥ « የተፈናቀለ ሰው የለም ፤ ሰዎችን ለመመለስም የተያዘ ዕቅድ የለም » በማለት በሚዲያ የተናገሩት ርካሽ ፕሮፓጋንዳ አሳዛኝና አሳፋሪ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ፕሬዝዳንቱ ፀሀይ የሞቀውን እውነታ ለመሸፈን ሲሉ ምንም አይነት ከቀዬው የተፈናቀለም ሆነ ከክልሉ እንዲወጣ የተደረገ ሰው እንደሌለ በማስመሰል ፤በዜጎች ላይ የተፈጸመውን ኢ-ሰብአዊና ኢ-ዲሞክራሲያዊ እንዲሁም የዜጎችን ክብር ያዋረደ ድርጊት መካዳቸው እውነትን የመግደል አባዜ የተጠናወታቸው የኢህአዴግ ባለስልጣናት ዛሬም ከሃያ ዓመት በኃላ ለለውጥ፤ ለግልጸኝነትና ለተጠያቂነት ያልተዘጋጁ መሆናቸውን አመላካች ነው፡፡

የክልሉ ፕሬዝዳንት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ በሚያስተዳድሩት ክልል ውስጥ በዜጎች ላይ ለተፈጸመው ጥቃት የበላይ መመሪያ ሰጭ እንደ መሆናቸው ከማንም በላይ ጉዳዩ በቀጥታ እንደሚመለከታቸው የማይታበል ሀቅ ነው፡፡ አዲስ አበባን ጨምሮ ወደ ደብረ ብርሀንና ሌሎች አካባቢዎች የተሰደደው ህዝብ ቁጥር ከሁለት ሺህ (2000) በላይ በሆነበትና ፤አሁንም ድረስ ከክልሉ እየታሰሩና እየተደበደቡ እንዲወጡ እየተደረገ ባለበት ሁኔታ ምንም እንዳልተፈጸመ ለመሸፋፈን መሞከር እራስን ማታለል ካልሆነ በቀር ከኢትዮጵያ ህዝብ የተሰወረ አይደለም፡፡

እነዚህ ከሰሜኑ የአማራ ክልል አካባቢ በተለያየ ጊዜ እና የስራ ሁኔታ ምክንያት ወደ ደቡብ ክልል ቤንቺ ማጂ ዞን እየወረዱ ረጅም ዓመት ያስቆጠሩ፤ በህጋዊ መንገድ ከመንግስት መሬት ተረክበው ሀብት ንብረት ያፈሩ፤ ቤተሰብ የመሰረቱ ፤ግብር ከፋይ ዜጎች ሆነው ሳለ የክልሉ ባለስልጣናት ቁጥራቸውን ወደ ሰላሳ አሳንሶ «ደን ሲያወድሙና ሲያቃጥሉ የነበሩ ህገወጦች ናቸው » ማለቱ በእጅጉ አሳዝኖናል፡፡ እነዚህ ዜጎች ግን መንግስት እንደሚለው ሳይሆን ህጋዊ ሆነው ይኖሩ የነበሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድና ግብር የከፈሉበት ማስረጃ በእጃቸው ይገኛል፡፡ ከዛም ባለፈ በ1996 ዓ.ም. ወረዳቸውን በልማት ከዞኑ በአንደኝነት ያሸለሙ አምራች ዜጎች ናቸው፡፡ መንገድ የሰሩ፤ ትምህርት ቤት እና ቀበሌዎችን የገነቡ፤ ቤተክርስቲያናትን ያነጹ እና ጥሩ ማህበራዊ መስተጋብርን የፈጠሩ ዜጎች ናቸው፡፡» በማለት አቋሙን ገልፃዕል፡፡

በማያያዝም መግለጫው ሲብራራ በቅርቡ ጉዳዩን ለማጣራት ከአዲስ አበባ ወደ ቤንቺ ማጂ ዞን ጉራፋርዳ ወረዳ የተንቀሳቀሰ አጣሪ ቡድን መኖሩ ይታወቃል፡፡ይህ አጣሪ ቡድን የኢህአዴግ ብአዴን አመራሮች ሲሆኑ ከደህዴን ደግሞ የደቡብ ክልል ቤንቺ ማጂ ዞን እና የወረዳ ኃላፊዎች እንደተካተቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ህዝቡን ሲያስሩና ሲደበድቡ ፤ ሀብት ንብረቱን

ወደ 14 የዞሯል

## ዜና

## የእነአንዱዓለም አራጌ . . .

ከገፅ 1 የዞረ

እንዳላቸው፤ አቶ ሙባርክ ከአቶ መለስ ለአገራቸው ህዝብ የተሻሉ ነበሩ:: አምባገነኖች የአገሪቱን ሀብትና ንብረት ከተቆጣጠሩ በኋላ የመገናኛ ብዙሃንን አፍነው ከፍተኛ የሆነ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጥሰት እየፈጸሙ ናቸው:: ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ ኢንተርኔት ተጠቃሚው 2 ፐርሰንት ብቻ ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ የከፋ ሥርዓት እየተገነባ ነው:: ኢትዮጵያ ውስጥ የከፋ ሥርዓት እየተገነባ ነው አገራችን የሁላችንም ናት::" በማለት ንግግር ሲያደርጉ ተደምጠዋል::

ጋዜጠኛ የፖለቲካ ተንታኝ እስክንድር ነጋ በበኩላቸው "ኢትዮጵያ በአፍሪካ ትልቋ አምባገነን አገዛዝ የሰፈነባት አገር ሆናለች::" በማለት ሲናገሩ የስብሰባው ታዳሚዎች ደግሞ "ነፃነት ናፍቆናል፤ ከእንግዲህ ግራና ቀኝ እየዞርኩ ማውራት አልፈልግም:: ፊት ላፊቴ እያየሁ ማውራት እፈልጋለሁ:: 2004 ርቆብኛል::" የሚሉ አስተያየቶች ሲቀርቡ ተደምጧል:: የ5ኛ ተከሳሽና የ7ኛ ተከሳሽ የመደረክ ላይ ክርክር የሚያሳይ ተጨማሪ ቪዲዮ እንዲታይ በጠበቆች በኩል ተጠይቆ የነበረ ሲሆን በዐቃቢ ህግ በኩል እንደይቀርብ ተቃውሞ ቀርቦበታል:: ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ በተጨማሪ ሰንድነት እንዲቀርብ ብይን በመስጠቱ ቪዲዮ ማስረጃው እንዲታይ ታዞ ነበር:: ሆኖም ግን ሲዲው ተዘጋጅቶ ባለማቅረቡ ሊታይ አልቻለም:: ማስረጃ የማቅረቡ ሂደት ተናቋል:: በመቀጠልም ፍ/ቤቱ የተመለከተው ዐቃቢ ህግ በፍትህ ጋዜጣ ላይና በነጋድራስ ጋዜጣ ላይ ያቀረበውን አቤቱታ ነው:: ጋዜጦቹ በዘገባቸው በፍ/ቤት ያልተገለፀ ዘገባ ዘግበዋል:: ዐቃቢ ሕግና ፍ/ቤቱ በገለልኝነት እየሠሩ እንደልሆነ በሚመስል መልኩ ዘግበዋል:: ስለዚህ የጋዜጦቹ ዋና አዘጋጆች ቀርበው ለችሎት መልስ ይስጡልኝ" በማለት አቤቱታ አቀርቦ ነበር:: ፍ/ቤቱ ሚያዝያ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ቀርበው እንዲያስረዱ አዟል:: እነ አንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ ላይ የግራ ቀኙን የመፋረጃ ሐሳብ ለመቀበል ለግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ/ም በ3 ሰዓት ተቀጥሮ የዕለቱ ችሎት ተጠናቋል::

## የኢህአዴግ . . .

ከገፅ 9 የዞረ

ለአማራም ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም ስለመቋቋሙ የቀረበ ማረጋገጫ ማግኘት አይቻልም:: ምክንያቱም የአማራ ህዝብ በኢህአዴግ በደል ሲፈፀምበት ተባባሪ ነበር እንጂ ከጥቃት ተከላካይ ሊሆን ለአንዴም ቢሆን አልታየም:: ይሁን እንጂ የህዝቡ ዝምታ ለዚህ አካሄድ መንገድ መከፈቱ የሚዘነጋ አይደለም::

የነ አቶ መለስ የሥልጣን መቆያ የኃይል ሚዛን በመጨረሻ ከብአዴን ይልቅ ወደ ደኢህዴን አድልቷል:: ይህም ካለፈው የአዲስ አበባ ምርጫ ጀምሮ በ2002 ዓ.ም በተካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫና "የስልጣን ሽግሽግ" ወይም "መተካካት" ተረጋግጧል::

ደኢህዴን

ደኢህዴግ ህወሓት ከመሰረታቸው የመጨረሻው አባል ድርጅት ሲሆን ይህም የደቡብ ክልል ህዝብን ይወክላል በሚል እሳቤ የተቋቋመ ነው:: ከዚህ በፊት በተለያየ ጊዜ እንደተገለፀው ደኢህዴግ (የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ግንባር) የተመሰረተው በህወሓት ከፍተኛ አመራር በሆኑት በአቶ አባይ ፀሐዬ አማካኝነት በዶ/ር ካሱ ኢላላ አስፈፃሚነት ነው:: ሲመሰረትም ዘግይቶ ህወሓት፣ ብአዴን እና ደራ ላይ የተመሰረተው ኦህዴድ (የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት) ከትጥቅ ትግሉ በኋላ በሰላሙ ጊዜ ነው:: በዚህ የታቀፉት የደኢህዴግ /ኢህአዴግ አባላትና አመራሮች የታዘዙትን ወለም ዘለም ሳይሉ ከመፈፀም ውጭ የራሳቸው ነፃነት የላቸውም፤ ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም::

በሂደት ደኢህዴግ ወደ ደኢህዴን ከተሸጋገረ በኋላም ለህወሓት ያለው ታማኝነት ከሌሎች ይልቅ ተጠናክሮ ቀጥሏል:: ለዚህም ይመስላል ከ2002 ዓ.ም ምርጫ በኋላ በስምም ቢሆን የሀገሪቱ ከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ ከብአዴን፣ ህወሓት፣ እና ኦህዴድ አባላት ተነጥቆ የአቶ መለስ ሚዛን ወደ ደኢህዴን ያደላው::

በአሁን ሰዓት አቶ መለስ እንደፈለጉት ከሚያሾሩት ደኢህዴን የተያዘው የሀገሪቱ የሥልጣን ደረጃን በጥቂቱ እንመልከት:: ለምሳሌ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ የመከላከያ ሚኒስቴር፣ የከተማ ልማት ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የውሃ ሀብት ሚኒስቴር፣ በሚኒስትርነት ማዕረግ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ አማካሪ (በማህበራዊ ዘርፍ)፣ የሀገሪቱ ፕሬዘደንት ልዩ አማካሪ፣ በተለያዩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የሚኒስቴር ዴኤታ እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ከፍተኛ ባለሥልጣንነትን በከፍተኛ ደረጃ ደኢህዴን እየመራው ይገኛል:: ይሄ የሚያሳየው ደኢህዴን ለአቶ መለስ አገዛዝና አስተሳሰብ ማራመጃ ምን ያህል ተዓማኒነት እንዳለው ነው::

ለዚህም ነው የደኢህዴን አመራሮች አሁን ባሉት የህወሓት፣ የብአዴን እና ኦህዴድ ላይ ያለውን የበላይነት እያሳየ ያለው:: ይህም አዲሱ የ "ስልጣን መተካካትን" ተከትሎ የመጣ ነው:: ደኢህዴን ምንም እንኳ ከአቶ መለስ ቀጥሎ የበላይነቱን እያሳየ ቢመጣም የደቡብ ክልል ህዝብን ከመከራና ከሰቆቃ አልታደገም፣ በክልሉ ያለውን የብልሹ አሰራር እና ሙስናን መቋቋም አቅቶት አመራሮች እርስበርስ ሲወነጃጀሉ ይስተዋላል:: የደቡብ ክልል ወጣቶችም በሀገሪቱም ሆነ በክልሉ ተምረውና ሰርተው መኖር ሲሳናቸው ተመራቂ ተማሪዎችን ጨምሮ ወደ ደቡብ አፍሪካ ስደት በሚል ታንዛኒያና ሞዛምቢክ ጫካ ውስጥ እና እስር ቤቶች ከመማቀቅና ከመሞት አልታደጋቸውም::

ይሁን እንጂ የደኢህዴን አመራሮች ከአቶ መለስ ቀጥሎ በኢህአዴግ ሌሎች ድርጅቶችና አመራሮች ላይ ያለው የበላይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ በመምጣት መዘዙ ለሀገሪቱ ነዋሪ ህዝብ ሆኗል:: በዚህም ምክንያት የደኢህዴን አመራሮች የሀገሪቱን ህገ መንግስት አንቀጽ 32(1)ን በመሻር የበላይነታቸውን ህዝቡ ላይ ተፈፃሚ አድርገዋል::

ለዚህም ማሳያ በደቡብ ክልል ዳውሮ ዞን ውስጥ ባለፈው መምህር የኔሰው ገብሬ ባለው የፍትህ እና መልካም አስተዳደር እጦት በተደጋጋሚ ጥያቄ እንዳነሳና እንደታሰረ መዘገቡ ይታወሳል:: በመጨረሻም መምህር የኔሰው ራሱን አቃጥሎ መስዋዕት ሲከፍል የደኢህዴን የዞኑ አመራር መምህር የኔሰውን "እሱ ኦሮሞ ነው፤ ምን አግብቶት ነው ስለዳውሮ አስተዳደር ጥያቄ የሚያነሳው?" ማለታቸውን የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ዘግበውታል:: ይሄ የሚያሳየው ኢትዮጵያዊነትን መካድ ብቻ ሳይሆን ህገ መንግስትን በመጣስ ደኢህዴን በኦህዴድ ላይ ያለውን የበላይነት ያሳየበት ነው:: ለዚህ የሚሆን ምላሽ ግን የኦሮሞ ህዝብን ወክያለሁ የሚለው ኦህዴድ የሰጠው መልስ አልነበረም:: ይልቁንም የኢህአዴግ ባለሥልጣናት (ኦህዴንን ጨምሮ) ሟቹን "የአእምሮ ህመምተኛ ነው" በማለት የወጣቱን መስዋዕትነት ከንቱ ለማድረግ ሞክረዋል፤ ባይሳካላቸውም::

ሌላው እና ትልቁ የደኢህዴን በብአዴን ላይ ያለው የበላይነት የተረጋገጠው በቅርቡ በቤንች ማጂ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ዜጎችን በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ የድፍረት ደብዳቤ ትዕዛዝ "ከሰሜን የመጡ የአማራ ተወላጆች ከአካባቢው ለቀው እንዲወጡ!" የሚል መመሪያ በፊርማና ማኅተም አስደግፈው ተግባራዊ አድርገዋል:: ይሄ አሁንም እንደሚቀጥል ተገልፃል:: ስለሆነም በማኅበረሰቡም ላይ ከፍተኛ ስጋት ፈጥሯል:: በሚፈናቀሉት ዜጎች ዙሪያ ከደኢህዴን /ኢህአዴግ አመራሮች ውጭ የአካባቢው ማኅበረሰብ (ነዋሪ) እጅ እንደሌለበትና የተፈናቀሉትንም ዜጎች በእምባ መሸኘታቸው ተገልፃል:: እዚህ ላይ የብአዴን አመራሮች ምንም መልስ ያለመስጠታቸውና የተፈናቃዮችን ሰቆቃና ስቃይ አብሮ ከማየት ውጭ የፈየደው ነገር የለም:: ብአዴንም የነ አቶ መለስ ጉዳይ አስፈፃሚ ከመሆን ያለፈ የአማራን ህዝብ ጥቅምም ሆነ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቅ እንዳልሆነም በተግባር አረጋግጧል::

ከቤንች ማጂ የተፈናቀሉ ዜጎች እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሀገራቸው አንዷት ኢትዮጵያ ሆኖ ሳለ በእነ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ (የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳደር) "ወደ ሀገራችሁ ሂዱ!" መባሉ ደግሞ ሌላው የዜግነት ክብርን የደፈረ ተግባር ነው:: እዚህ ላይ አቶ ሽፈራውም ሆኑ ሌሎች የደኢህዴን አመራሮች የአቶ መለስ ጉዳይ አስፈፃሚ እንጂ የህዝብ እንደራሴ ስላልሆኑ ከላይ የተሰጣቸውን መመሪያ በድፍረት ተግብረውታል:: ላይ ላዩን የብአዴን የበታችነት እና የደኢህዴን የበላይነት የተረጋገጠበት ቢሆንም ውስጡ እና እውነታው ግን የኢህአዴግ መፍረክረክና በህዝቡ እና አባላቱ እምነት በማጣቱ የተወሰደ ርምጃ ነው::

በዚህ አጋጣሚ የኢህአዴግ ፍጻሜ መቃረቡንና በውስጡ ያለውን መፍረክረክ ለመደበቅ የህዝብን አቅጣጫ ማስቀየሻ የተለያዩ አጀንዳዎች ሲቀረጹና ሲተገበሩ ከርመዋል:: በተወሰነ መልኩ የሥልጣን ዕድሜን ከማራዘም ባለፈ ፍቱን መፍትሄ ሊሆን ባለመቻሉ ከርዕዮት ዓለም (አይዲዮሎጂ)፣ የጐሳ፣ የኃይማኖት ልዩነትን በመፍጠርና በማጋጨት እስከዚህ ተደርሷል፣ ግን አልተሳኩም::

በአሁኑ ሰዓት እየተተገበረ ያለው አዲሱ የአቶ መለስ የስልጣን ማራዘሚያ ስልት ሙስሊሙን ከሙስሊም፣ ኦርቶዶክሱን ከኦርቶዶክስ፣ አንድ ብሔር ውስጥ እርስ በርስ፣ ተቃዋሚ ፓርቲ ውስጥ እርስ በርስ እና ራሱ ኢህአዴግ ውስጥ ህወሓትን ከኢህዴግ፣ ብአዴንን ከደኢህዴን የማጋጨት ስትራቴጂ በስፋት ተጀምሯል:: በዚህም ምክንያት ለኢትዮጵያ ህዝብና ለኢህአዴግ አመራሮች ከባድ የቤት ሥራ በመስጠት የትኩረት አቅጣጫ በማስቀየር አዲሱ የስልጣን ማራዘሚያ ስልት ሂደት እውን ሆኗል:: ይህም በገሃድ የሚያሳው የነ አቶ መለስ አገዛዝ ግብዓተ መሬት መቅረቡን የሚያረጋግጥ ቢሆንም ሀገር እንመራለን ያሉ ተቃዋሚ የሆኑትን ሳይሆን በህዝብ አመኔታ ተጥሎባቸዋል የሚባሉትም አካሄዳቸው የተለመደውን አንድ አቅጣጫ ከመከተል የዘለለ ስልት ሲጠቀሙ አይስተዋልም:: ከተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ይልቅ የኢህአዴግን መፍረክረክና ፍፃሜ የተረዱት የኢህአዴግ አባላት ናቸው:: እነሱም ቢሆኑ መልቀቂያ እያስገቡ ከድርጅቱ ካምፕ ከመውጣት ባለፈ ለህዝቡም ሆነ ለራሳቸው የፈየዱት ነገር የለም::

ተቃዋሚዎች

በኢትዮጵያ ያሉ ተቃዋሚ (ተፎካካሪ) የፖለቲካ ድርጅቶች የኢህአዴግን መፍረክረክ ከመረዳት ይልቅ እሱ የሚፈጥራባቸውን ተፅዕኖ አጉልተው ሲደሰኩሩ ይደመጣል:: ነገር ግን የራሳቸውን ችግር ያለማየትና የሚከተሉት የትግል ስልት ከጊዜው እና ከትውልዱ ጋር አብሮ መሄድ አልቻለም:: ይሄ ድክመታቸውም ከነ አቶ መለስ የስልጣን ዘመን እኩል የሚሰላ ችግር ይዘው እየተጓዙ ይገኛሉ:: ተቃዋሚዎች መጫወት በሚገባቸው ሰዓት ባለመጫወታቸው ከጊዜው ጋር አብረው ባለመዘመናቸውና የፖለቲካ ትርፍ ማግኘት በሚገባቸው ሰዓት ባለመስራታቸው በተፈጠረ ድክመት ኢህአዴግ ቢፍረከረክም እስከ አሁን ሥልጣን ይዞ ሀገር እየመራ ይገኛል:: በአጠቃላይ ኢህአዴግ በአሁን ሰዓት ሥልጣን ላይ ያለው በሰራቸው በጐ ሥራዎችና ባለው ጥንካሬ ሳይሆን በተቃዋሚዎች ድክመት ነው ማለት ይቻላል:: ለነ አቶ መለስ የረጅም የሥልጣን ዘመን አገዛዝ ተቃዋሚዎች ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከታቸው ሊዘነጋ አይገባም:: አሁንም ቢሆን አንድ የማይካድ ነገር አለ:: ኢህአዴግ ፍፃሜው ተቃርቧል፤ ተቃዋሚዎች ግን ተኝተዋል፣ የህዝቡም ሰቆቃ ቀጥሏል፤ ልብ ያለው ልብ ሊል ይገባል::

## ወጣቱ በሱዳን . . .

ከገፅ 1 የዞረ

የህክምና ማዕከል ጋር የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሐኪሞች ቦርድ ሪፈር ወደ ውጭ ሀገር ሄጄ የቀዶጥገና እንዲደረግ በሰጠኝ ማስረጃ መሠረት ሰርጀሪውን ለማድረግ ውል አደረኩኝ:: ቪዛም ኢትዮጵያ በሚገኘው የሱዳን ኤምባሲ በኩል ተልኮልኝ ወሰድኩኝ:: ሆስፒታሉ ቪዛውን ሲልክልኝ እንዳነጋገረኝ ካርቱም ኤርፖርት ስትደርስ አሳውቀንና እንቀበልሐለን፤ ባለኝ መሠረት አሳውቄ ጉዞ አደረኩኝ:: ካርቱም ስደርስ የሚቀበለኝ ሰው አጣሁኝ:: ለሦስት ሰዓት ጠብቄ የሚቀበለኝ ሳጣ 25 ኪ.ሜ በታክሲ ተጓጉዤ ሆስፒታሉን አገኘሁት:: በማለት ደረሰብኝ ያለውን ችግር ያስረዳል::

ወጣቱ በመቀጠልም "ካረፍኩበት ገስት ሀውስ ቀዶ ጥገና ለማድረግ /ኦአር/ ተጠርቼ ከሄድኩኝ በኋላ እንድተኛ ተደረገ:: ካቲተር (የሽንት መሽኛ ቱቦ) ተደረገልኝ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ካቲተሩ የሽንት መሽኛ ዘግቶብኝ ሽንት መሽናት ስለአቃተኝ ከፍተኛ ስቃይ ገጠመኝ:: ይቆጣጠረኝ የነበረ አንድ የሱዳን ካፍቴሪያ ሠራተኛ ስለነበረ እርዳኝ ብለው እንቢ አለኝ:: ካቲተሩን ልበጥሰው ስል ሰዓት እያየ ተው ብሎ አስፈራራኝ:: በአጋጣሚ ፈረንጆች ስራ አዘዙት:: ካጠገቤ መሄዱን ሳይ ህይወቴን ለማዳን ካቲተሩን (የሽንት መሽኛ ቱቦ) በጠስኩት:: ብዙ ደም ፈሶኝ እዚያው በተኛሁበት ሽንቴን በመሽናቴ ልተነፍስ ቻልኩኝ:: እዚያው ባለሁበት እረፍት አድርጌ ጋደም አልኩኝ:: ያ አጠገቤ ቆሞ ሲጠባበቀኝ የነበረው የካፍቴሪያ ሠራተኛ ከተላከበት ተመልሶ ሲመጣ ጋደም ብዬአለሁ:: በግራ በኩል አፌን በፕላስተር አሽጐ ወደ ግራውንድ ሬሳ ክፍል ይዞኝ በመሄድ አንድ ማሽን ላይ እኔ ያለሁበትን አልጋ ሲያስጠጋው ማሽኑ ህይወት መኖሩን ድምጽ ሰጠው:: ህይወቴን መኖሩን ወደ አፌ ሲጠጋ ከፍተኛ ትንፋሽ አገኘ:: ወደ ካቲተሩ (የሽንት መሽኛ ቱቦ) ሲመለከት መበጠሱንና አንሶላው በደም መበከሉን ተመለከተ:: ወዲያውኑ በመደናገጥ ሀራም! ሀራም! አላህ አኩበር! አላህ አኩበር! በማለት ወደ ነበርኩበት ክፍል መልሶኝ ጠፋ:: ህይወቴም በዚህ አጋጣሚ ተረፈ" በማለት ህይወቱ የተረፈበትን ሁኔታ ያስረዳል::

ማርቆስ ከተማ በማያያዝ ሲገልጽ "በመቀጠል ቀዶ ጥገና ወዲያውኑ ተደረገልኝ:: ሦስት ቀን ሙሉ ማደንዘዣውን መቋቋም ስለአልቻልኩኝ ራሴን ሳላውቅ ቀረሁኝ:: ከሦስት ቀን በኋላ ራሴን አወኩኝ:: በህይወት እንዳለውም ተረጋገጠ:: ከዚያም በተጨማሪ ቀዶ ጥገና ከጨረስኩኝ በኋላ ነርሶቹ በየአንድ ሰዓቱ ልዩነት የደሜ ዓይነት ኦ ፖዘቲቭ ስለሆነ ደም ያለ አግባብ ይወስዱብኝ እንደነበር መገንዘብ ችያለሁ:: እንቅልፍ ሸለብ ባደረገኝ ቁጥር ነርሶች በተደጋጋሚ በር እየከፈቱ ያዩኝ ነበር:: ለምንድነው? ስላቸው መልስ አይሰጡኝም ነበር:: ዶክተሮቹ ምን ዓይነት ቀዶ ጥገና እንደሚያደርጉ ገልፀው አላስፈረሙኝም:: ተመሳሳይ ፊርማ አለ ቢሉ እንኳን በአሻራ ማረጋገጥ ይቻላል:: ቀዶ ጥገናው በአግባቡ ባለመደረጉ በጤንነቴ ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮብኛል:: ከቀዶ ጥገናው በኋላ ባደረጉት ምርመራ የልቤ ስፋት ጤነኛ በአለመሆኑ በባለሞያዎች አረጋግጫለሁ:: ወደ አገሬም የተመለስኩት እጅግ በከፍተኛ ችግርና ስቃይ ነው:: በአሁኑ ጊዜ ጤንነቴ ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጧል:: ጉዳዩን ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ደርሼ ያገኘሁት መፍትሄ የለም:: በኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል በሆስፒታሉ ላይ ክስ ለመክፈት ጠይቄ በግልህ ክሰስ ተብዬ አለሁ:: ጠ/ሚኒስትሩ ጽ/ቤት አመልክቼ ጉዳዩ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አመልክት ከማለት ውጪ ወቅታዊ መፍትሄ አላገኘሁም:: እኔ ለመክሰስ አቅም የለኝም:: ስለዚህ እባካችሁን ሊረዳኝ ለሚችሉ ሁሉ ጥሪዬን አቅርቡልኝ" በማለት ጥሪያቸውን አቅርበዋል::

# መድረክ የመጋቢት 22ቱን ስብሰባ ለምን ሰረዘው?

በለጠ ጎሹ

መድረክ በአዲሱ የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ላይ ከአዲስ አበባ ሕዝብ ጋር ቅደሜ መጋቢት 22 ቀን 2004 በሙገር ስሚንቶ መሰብሰቢያ አዳራሽ (ጐተራ አካካቢ) ውሰጥ ውይይት ለማድረግ ማስታወቂያ አውጥቶ ለአዲስ አበባና አካባቢዋ ነዋሪዎች ጥሪ አስተላልፎ ነበር፡፡ አስፈላጊዎቹን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቷል፡፡ ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ፈቃድ አግኝቷል፡፡ አዳራሹን ለመከራየት የሚያስችለውን ባለአራት ገፅ ውል ተፈራርሞ የተጠየቀውን ሁለት ሺ ብር ከፍሎ ደረሰኝ ተቀብሏል፡፡

አንድ የሙገር ስሚንቶ የመምሪያ ኃላፊ በድንገት ተነስተው ‹‹ስብሰባውን ማካሄድ አይቻልም!›› ብለው ከለከሉ፡፡ መድረክ የከፈለውን ገንዘብ መልሶ እንዲወስድ አሳሰቡ፡፡ ምንድን ነው ነገሩ?! እንዴት አንድ ሰው ከመሬት ተነስቶ ያለ አንዳች በቂ ምክንያት ውል ያፈርሳል? ሕጋዊ የሆነ ስብሰባን እንዴት ያስተጓጉላል? እኚህ ሰው ስብሰባው እንዳይደረግ የከለከሉት በራሳቸው ሥልጣን ነው ወይስ የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ (ዋና ሥራ አስኪያጅ) አዟቸው ነው? እሳቸውንስ ማን አዘዛቸው? የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 30፤ንኡስ አንቀጽ 1 እንደሚከተለው ይደነግጋል፤

“ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሠላም የመሰብሰብ፣ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና፣አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎች፣ሰላማዊ ሠልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሠላማዊ ሠልፍ ሠላምን፣ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብ የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡” ይላል፡፡

መድረክ አዘጋጅቶት የነበረው የቤት ውስጥ ሠላማዊ ሕዝባዊ ስብሰባ ስለሆነ፣ከቤት ውጭ የሚካሄዱትን ሕዝባዊ ስብሰባዎችና ሠላማዊ ሠልፎች ሥርዓት ለማስያዝ የተደነገገው አይመለከተውም፡፡ ስለዚህ ስብሰባው መቶ በመቶ ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌውን የሚያሟላ ነበር፡፡ ታዲያ፣ለምን ተሰረዘ? በእኔ እምነት ስብሰባው እንዲሰረዝ ትዕዛዝ የወረደው ከቱባ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ነው፡፡ የኢህአዴግ የሥልጣን ዘመን የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ የደረሰ ይመስለኛል፡፡ ሥርዓቱ ላለመሞት እየተፈራገጠ ነው፡፡ ሙስና እና የዋጋ ንረት አበስብሰውታል፡፡ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ የኃይማኖት ነፃነቱን ለማስከበር እያካሄደ ያለው መጠነ ሰፊ ሕዝባዊ እነቀስቃሴ ወጥሮ ይዞታል፡፡ የመምህራኑ ሠላማዊ የሥራ ማቆም አድማ ሕዝባዊ ማዕበል ያስነሳል ብሎ እንቅልፍ ነስቶታል፡፡ ኢህአዴግ ተጨባጭ ሐቁን ተቀብሎ የእርምት እርምጃዎች እንደመውሰድ ሁሉ ‹‹እኔ ባልኩት መንገድ ብቻ መቀጠል አለበት›› ብሎ፣የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም የማይፈፅመው ወንጀል የለም፡፡ ጥንታዊ ገዳሞችን እያፈረሰ የሸንኮራ ተክል እያቋቋመባቸው ነው፤ብሔረሰቦችን እንደፈለገ ከቀያቸው እያፈናቀላቸው ነው፡፡ ንፁሐን ዜጐችን በሐሰት ውንጀላ እያካሄደና እያሰቃየ ነው፡፡ በአጭሩ፣በአሁኑ ጊዜ ወያኔ/ኢህአዴግ የማይፈፅመው ወንጀል፣ኃጢዓት እና ነውር የለም!

ግን እኔን የገረመኝ ኢህአዴግ ስብሰባውን መሰረዙ አይደለም፡፡ እንዴት የብዙ ዓመታት የፖለቲካ ልምድ ያላቸው የመድረክ አመራር አባላት ሕጋዊ ስብሰባቸው በግብታዊ ትዕዛዝ ሲሰርዝባቸው አሜን ብለው ይቀበላሉ? መድረክ (ዶ/ር ኃይሉ አርአያ) ስብሰባው መሰረዙን መጋቢት 21፣2004 በወጣው ፍትሕ ጋዜጣ ላይ አስታውቀዋል፡፡ ለምን ይህ ማስታወቂያ ወጣ? ሕዝቡ በቀጠሮው ቀንና ሰዓት ሙገር ስሚንቶ አዳራሽ ዙሪያ እንዲሰባሰብ ለምን አልተደረገም? መድረኮች ያኔ ስብሰባው መሰረዙን ለታዳሚው ሕዝብ ሊነግሩት ይችሉ ነበር፡፡ ይህ የሰላማዊ ትግል አንዱ ዘዴ ነው እኮ! ሕዝቡ ይሰበሰባል፤ ፎቶና ቪዲዮ ይነሳል፤ከዚያ በፍኖተ-ነፃነት ጋዜጣ ላይ የሕዝቡን ፎቶ አውጥቶ፣ “መድረክ ያዘጋጀው ሕዝባዊ ስብሰባ መሰረዙ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን አሳዝኗል” ተብሎ ዜና ይሰራበት ነበር! በዚህ በኩል ዶ/ር ኃይሉ አመራሩን አማክረው ትክክለኛ ውሳኔ አስተላለፈዋል ብዬ አላምንም፡፡ በዚህ አጋጣሚ በመግለጫቸው የተበሳጩ የአመራር አባላት ገጥመውኛል፡፡ የፍኖተ-ነፃነት ትንታግ አምደኛ ግርማ ሞገስ ስለ ሠላማዊ ትግል ስልቶች ብዙ ቁምነገሮችን አስጨብጦን ነበር፤ ግን እስካሁን አንዳቸውንም በሚገባ ተግባራዊ ማድረግ የቻልን አልመሰለኝም፡፡

አዳራሹን የተከለከለው ሕዝብ ምንም ሳይሠራ ወደ ቤቱ እንዳይመለስ ማድረግም ይቻል ነበር፡፡ ስብሰባውን ከፋፍሎ በአንድነት ጽ/ቤት በመድረክ ጽ/ቤት እና በሌሎች የፓርቲ ጽ/ቤቶች ውስጥ ማካሄድ ይቻል ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ስብሰባ ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆን መግለጫ የሚሰጥና ውይይቱን የሚመራ ሰው በመመደብ አመርቂ የሆነ የሀሣብ ልውውጥ ማድረግ ይቻል ነበር፡፡ ስብሰባው የተሰረዘው ታዳሚው ሕዝብ እንዳይጉላላ ታስቦ ከሆነ ስህተት ነው፡፡ ሕዝቡ ለነፃነቱ ከዚህ የበለጠ መስዋዕትነት ለመክፈል ተዘጋጅቷል፡፡ ስብሰባው ቢካሄድ ኖሮ፣የአዲስ አበባ ሕዝብ መምህራኑ ለመብታቸው የሚያደርጉትን ሠላማዊ ትግል በተመለከተ፣የድጋፍ መግለጫ ያወጣ ነበር! ከዚህ በመነሳት መድረክ ራሱ እንደ ፓርቲ ተመሳሳይ የድጋፍ መግለጫ ያስተላልፍ ነበር! ምን ያደርጋል? ነገሩ ሁሉ በነበረ ቀረ እንጂ! በዚህ ረገድ መድረክ ልክ እንደቀድሞው (business as usual) የሚያዋጣው አለመሆኑን ይወቅ፡፡

በበኩሌ፣ ኢህአዴግን ስለ ሊዝ አዋጁ ብቻ ሳይሆን፣ስለ መምህራኑ ጥያቄ ጭምር ለመሞገት አስቤ ነበር፡፡ የሊዝ አዋጁ ሕገ መንግሥቱን እንደሚፃረርና አንቀፅና ቁጥር እየጠቀስኩ ለመከራከር ተዘጋጅቼ ነበር፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት የመጀመሪያ ዲግሪ ላለው ጀማሪ መምህር የሚከፍለው 1300 ብር ደመወዝ (የተጣራ)፣የመግዛት ኃይል በኃ/ሥላሴ ጊዜ ከነበረው 65 ብር እንኳን እንደማይስተካከል ለማሳየት ዕቅድ ነበረኝ፡፡ የአዲስ አበባ ሕዝብና የመምህራኑ የኢኮኖሚ ጥቅም መብት የማስከበር ጥያቄዎች ተመሳሳይ መሆናቸውን ለማስረዳት ሞክሬ፣ሕዝቡ የተቀናጀ ሠላማዊ ትግል ማካሄድ እንዳለበት ለመጠቆምም አስቤ ነበር፤ግን ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት መድረክ የበሰለና ስልታዊ አመራር ሊሰጠን አልቻለም! ይህን ስል መድረክን ለመንቀፍ ወይም ከመድረክ የተሻለ አማራጭ አለን ለማለት አለመሆኑን ማስገንዘብ እወዳለሁ! እውነት ለመናገር፣በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመድረክ ሌላ የሠላማዊ ትግል አማራጭ ያለው አይመስለኝም!

ኢህአዴግ ጠመንጃ በወደረ ቁጥር፣አቶ መለስ እጅና እግር እቆርጣለሁ ባሉ ቁጥር፣ሸብርተኞች ናችሁ እያሉ በዛቱ ቁጥር መድረክ ሸብርክ የሚል ከሆነ ጠንካራ ሰላማዊ ትግል መምራትና ማካሄድ የሚቻል አይመስለኝም! አንዱዓለም አራጌ፣ናትናኤል መኮንን፣ርዕዮት ዓለሙ፣በቀለ ገርባ እና ሌሎቹ የዴሞክራሲ ታጋዮች በሐሰት ውንጀላ ወህኒ ቤት እየማቀቁ ያሉት እኮ ለራሳቸው ነፃነት ብቻ አይደለም፤ ይልቁኑ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብን ከኢህአዴግ የባርነት እና የዝርፊያ ስርዓት ለማላቀቅ ነው!

# የኦሮሞ ነገር. . .

ከገፅ 2 የዞረ

ቶሎሳ ጉደታ ከግምቢ ጀምሮ እስከ ኦሮሚያ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሀላፊነት የሙስና ሀሜት አልተለያቸውም፡፡ በቅርቡ ወደ 17 ሚሊዮን ብር የሚገመት ሲጠፋ ሰውየውን የተሻለ ሙስና ወደ ሚያሰራው የኦሮሚያ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ኃላፊነት መዘዋወሩ አስገርሟል፡፡ በቅርቡ በቡራዩ ከተማ ኩማ ደመቅሳ የመሩት የህዝባዊ ስብሰባ ተደርጓል፡፡ የከተማዋ ከንቲባ አቶ ቸርነትን ጨምሮ ከ20 የሚበልጡ የከተማዋ አመራሮችም መታሰራቸው ተውቋል፡፡ ነገር ግን ህዝቡ ባደረገው ጥቆማ እንዲሁም ተጠርጥረው የታሰሩ ሰዎች አብዛኛውን ሙስና የሰሩት በአቶ ዘለዓለም ጀማነህ፣ ደባ ደበሌ፣ አባዱላ ገመዳና ቶሎሳ ደገፉ ትዕዛዝና መመሣጠር መሆኑን አምነው እነሱ በሌሉበት ቃላቸውን እንደማይሰጡ መናገራቸው ታውቋል፡፡

የብዙዎች አይን ውስጥ የገቡት አቶ ቶሎሳ ደገፉ የኦሮሚያ ዲዛይን ኢንተርፕራይዝ የቦርድ ሰብሳቢ፣ የኦሮሚያ ቀይ መስቀል የቦርድ ሰብሳቢ፣ የኦሮሚያ ምርት ገበያ የቦርድ ሰብሳቢ፣ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ድርጅት የቦርድ አባል፣ የኦሮሚያ ቤተሰብ መምሪያ የቦርድ አባል እንዲሁም የኦሮሚያ የገጠር መንገድ የቦርድ አባል መሆናቸዉ ተረጋግጧል፡፡ የኦሮሚያ የውሃ ስራዎች ድርጅት የቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ሺፈራው ጃርሶ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ የኦሮሚያ የውሃ ስራዎች ድርጅት የውሃ ማውጫያ መሣሪያዎችን (ማሺነሪዎችን) የተከራየው ከቦርዱ ሰብሳቢ አቶ ሽፈራው ጃርሶ መሆኑን በፅ/ቤቱ የስራ አመራር የሆኑ ስማቸዉ እንዲጠቀስ ያልፈለጉ ሰው ለፍኖተ ነጻነት ተናግረዋል፡፡ አቶ ሽፈራው “ድሪለር” ለሚባሉት የጥልቅ ጉድጓድ ቆፋሪ ማሺን በሰዓት ከ3800 ብር በላይ የተፈራረሙ ሲሆን ማሽኖቹ ከድርጅቱ ቢሮ ወጥተው እንደማያውቁ እኚህ ግለሰብ ይናገራሉ፡፡

የኦህዴድ ጠቅላላ ጉባኤ አዳነች አቤቤ የተባሉ አመራር በየትኛውም ሀላፊነት እንዳይመደቡ የወሰነ ቢሆንም “ከመቼው የኦሮሚያ ልማት ማህበር ኃላፊ እንደሆኑ ገርሞኛል” ሲሉ የሚናገሩት እኚህ ሰው “ይህን በገዛ ፈቃዳቸዉ ያደረጉት አባዱላ ናቸዉ” በማለት መልስ ይሰጣሉ፡፡ ሰውየው ኃሳባቸውን ሲያጠናክሩ “አቶ አባዱላ የኦልማ ቦርድ ሰብሳቢ ናቸዉ” ሲሉ ያረጋግጣሉ፡፡

“ቀጥተኛ ተያያዥነቱ ቢያጠራጥርም የኩማ ቤተሰብም በእርዳታ መልክ ት/ቤቶችን እያስፋፉ ነው” የሚሉት እኒህ ሰው ‹‹በጎሬ፣ መቱ፣ ያዮና በደሌ ያላቸውን እንኳ እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል” ይላሉ፡፡ ከላይ ባየነው መሠረት አንዳቸውም ለህግ ተላልፈው አልተሰጡም፡፡ ፖለቲካዊ ጫና ያልበዛበት መንግስት ቢሆን አባዱላ ቤቱን ለኦህዴድ ከሰጡ በህግ ፊት አይጠየቁም ማለት አልነበረም፡፡ ይህ ለህወሓት ካርድ ነው” ይላሉ ተንታኞች፡፡ አንዳንድ ዉስጠ አዋቂዎች በአዳማ የሚገኘዉ የአቶ ጁነዲን አማች ህንፃም የአረጋዊዉ ነዉ ብሎ መገመት እንኳ አይቻልም ይላሉ፡፡ በዚህ የሙስና ሪከርድ ዉስጥ ያሉ አመራሮች ከእንግዲህ ግዑዝ ፖለቲከኞች በመሆናቸዉ ፍፁም የህወሓት መሳሪያዎች ናቸዉ ብለው ይከራከራሉ፡፡

<u>የፖለቲካ ሙስና</u>

ጀዋር መሐመድ “Meles Zenawi and OPDD Relations Enter New Phase” በተባለ ጥናቱ አባዱላ ድህረ ምርጫ 97 የአቶ መለስ ዜናዊን በተለያዩ ቀውሶች መጠመድ እንዲሁም የማይጠረጠር ታማኝነታቸውን በመጠቀም ኦህዴድን በተማሩ ሰዎች በማጠናከር ከህወሃት ሞግዚትነት ለማውጣት ሞክረዋል የሚል ትንተና ያቀርባሉ፡፡ ይህ አሰራር ያመጣላቸው ታዋቂነትና ተወዳጅነት ለአቶ መለስ የሚዋጥ ስላልነበር የተዘጉ የሙስና ጉዳዮች እየተነሱ ሰዉየዉን ማሸማቀቅ መጀመራያቸዉን ይከራከራሉ፡፡ ለቀድሞ ፕሬዚደንት ቅርብ የነበሩ ስማቸው ይፋ እንዲሆን ያልፈለጉ ተናጋሪ በጀዋር ትንተና አይስማሙም፡፡ “ሰውዬው ከማስጨፈር የዘለለ ምን ሰራ?” ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ በርሳቸው ትንተና አቶ አባዱላ ኦነግንና ሌሎች የተለየ ሀሳብ ያላቸውን በብር ለማዳከም /ለመደለል ከመሞከር የዘለለ “በነፃ የርዕዮት አለም ትንተና ያመጡትን ሰው አላስታውስም” ሲሉ ይነገራሉ፡፡ “አብዛኞዎቹ ምሁራንም በዚህ ወቅት በብዛት ወደ ከፍተኛ ትህምርት ቤት ነበር ያቀኑት” የሚሉት እኚህ ሰው ከፋም ለማም ሳይሉ ይታዘዙ እንደነበር ያወሳሉ፡፡ “የአባዱላን ድክመት የምታየው የሞተውን ኦነግ ነፍስ ሲዘሩበት ነዉ” በማለት ሌላ አቅጣጫ የሚያስይዙት ተነጋሪው ቢሾፍቱ ያሉት ኮንዶሚኒየሞች ከሞያሌ መጠን ለሚሉ /የኦነግን ስም ለሚያነሱ ብቻ እንደ መደለያ ይቀርቡ እንደነበር ይተርካሉ፡፡ ከኦነግ በማፈንገጥ መጣን ላሉት ዲያስፖራዎች ሁሉ ሰበታ ከተማ መሬት እየተገመሠ ቢሰጣቸውም እየሸጡ እንደ ሄዱ ይነገራል፡፡ ለአንዳንድ ተለጣፊ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችም መኪናና ከፍተኛ ገንዘብ እንደ መደቡ ይነገራል፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ስብሰባ ሲኖር ከፍተኛ ኃላፊዎችን ጨምሮ ለመገኘት ፈቃደኛ እንደማይሆኑ ነው፡፡ የአባላት መዋጮ የሚከፍሉ አብዛኛዎቹ አባላት “ገንዘቤን ከከፈልኩ ኦህዴድ ከኔ ምን ይፈልጋል” እስከማለት ደርሰዋል፡፡

<u>የኦህዴድ የገቢ ምንጭ</u>

ህወሓት በኢንደውመንት ድርጅቶቹ ብዙ ቢሊዮን ብር ያንቀሳቅሳል፡፡ ኦህዴድም በዚህ በኩል የራሱን ያክል ለማድረግ ቢሞክርም እነ ቢፍቱ (ጫት ላኪ)ና እነ ዲንሾ፣ ከህወሓቶቹ ጉና፣ ትራንስና መስፍን ጋር ፍፁም እንደማይወዳደሩ ይታወቃል፡፡ የትራንስ መኪኖች ወደ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ጋምቤላና ጂቡቲ ሲመላለሱ ሎንቺኖቹ የት እንደገቡ የማያዉቀዉ ኦህዴድ እንዲሁ ይማስናል፡፡ “የህወሓት ካምፓኒዎች ሲሚንቶ፣ መዲሃኒት፣ ከባድ መኪኖችና ብረታብረት ሲያመርቱ ያየው ኦህዴድ መርካቶ ውስጥ አንዲት ጠባብ ፎቶ ቤት ከፍቶ ንግድ ጀምሯል፡፡ መቼም ማፈሪያ ነው” ሲሉ በንዴት የሚገልፁት ስማቸውን ለመስጠት ያልፈቀዱ የክልሉ ተወላጅ ናቸው፡፡

ኦህዴድ 1.6 ሚሊዮን አባላት እንዳሉት ይፋ አድርጓል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 300,000ዎቹ የመንግሥት ሰራተኞች ሲሆኑ በየወሩ 5% ደሞዛቸው ለድርጅት አበል ይቆረጥባቸዋል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ አርሶ አደር ያለምንም ፈቃድ በየወሩ አባወራው ሁለት ብር የሚከፍል ሲሆን ሚስቱን ጨምሮ እቤት ውስጥ ባሉት የሰዎች ብዛት መጠን በነፍስ ወከፍ ተጨማሪ አንድ አንድ ብር ይጣልበታል፡፡ 8 ሰው የሚያስተዳድር አባወራ በወር 9 ብር ለኦህዴድ መክፈል አለበት ማለት ነው፡፡ እንግዲህ አባዱላ ይህንን ብር ነበር የሃሳባ ልዩነት ያላቸዉን ሁሉ ለማፈኛ ያለ ሀሳብ ሲያፈሱ የነበረዉ፡፡

<u>እነ አርሰናል እና ኢስላም መንግሥት</u>

የኦህዴድ መፈክር “የወንዜ ልጅ የሚበጅ” የሚል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በኦህዴድ አመራር ሰሞነኛ ቡድኖች ይበረክታሉ፡፡ አንድ ሰሞን የባሌ ልጆች፣ የወለጋ ልጆች ሌላ ሰሞን ዓይነት፡፡ በዚህ በኩል ጁነዲ ሳዶና አባዱላ ገመዳ የሚመሩት ቡድን “አርሰናል” የሚባል ሲሆን በአርሲ የበላይነት የሚያምን ነው፡፡ ከዚህ ሰፋ ካለ ደግሞ “BA” የሚባል ምህፃረ ቃል የተሰጠዉና ባሌና አርሲ ተወላጆችን የሚሰበሰብ አመራር ያለበት ቡድን ነው፡፡ ከዚህ ውጭም ሀይማኖትን መሠረት ያረጉ መቧደኖች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም መሠረት የመጨረሻ ግባቸውን የኢስላም መንግስት ያደረጉ አመራሮች እንዳሉ ይነገራል፡፡ ጅማ አካባቢ በተነሳው የሃይማኖት ግጭት ከአንድ የኦህዴድ ከፍተኛ አመራር አማች ቤት አንድ አይሱዙ ሙሉ ገጀራ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ ሰሞኑን እንኳ በኢሉባቦር አካባቢ ተመሳሳይ አይነት እንቅስቃሴ የተስተዋለ ሲሆን ትዕዛዙን ያገኙት በዚህ ጉዳይ በተደጋጋሚ ከሚታሙት የድርጅቱ አመራር መሆኑ ተደርሶበታል፡፡

<u>አለማየሁ በጎዶሎ ሲጫወት</u>

የወቅቱ የኦሮሚያ ፕሬዚዴንት በሙስና እንደማይታሙ ይነገራል፡፡ ካላቸዉ እዉቀትና ክህሎት የበለጠም ለዚህ ቦታ ያበቃቸዉ በሙስና ላይ የሚያራምዱት አቋም እንደሆነ በሰፊዉ ይወራል፡፡ ነገር ግን ይህንን የሚያዉቀዉ የአቶ መለስ መንግስት ወደ ክልሉ ስልጣን እንዲመጡ ቢያግዛቸዉም የራሳቸዉን ስራ አስፈፃሚ እንዲመሰርቱ አላገዛቸዉም፡፡ በዚህም መሰረት ቡድናቸዉ 4 ለ 9 እንደሚመራ ዉስጠ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ የአቶ አለማየሁ አቶምሳ ፕሬዚዴንትነት ዛሬም ድረስ በአቶ አባዱላና አቶ ዘላለም ጀማነህ ጥላ ስር መሆኑ ይነገራል፡፡ ከኃይል አሰላለፍ አንጻር በአፈ ጉባኤ አባዱላ ገመዳ ዙርያ ጁነዲን ሳዶ፣ ወርቅነህ ገበየሁ፣ አብዱላዚዝ መሃመድ፣አለማየሁ እጅጉ፣ ዘላለም ጀማነህ፣ ለማ መገርሳ፣ ሶፊያን አህመድና ድርባ ኩማ እንዳሉ ይነገራል፡፡ በአቶ አለማየሁ አቶምሳ ዉሳኔዎች ላይም አፍራሽ ሚና እንዳላቸዉ ይነገራል፡፡ በተቃራኒዉ ሙሰኞችን በመዋጋት ጠላት አብዝተዋል የሚባሉት ፕሬዚደቱ አቶ አለማየሁ አቶምሳ አለማየሁ ተገኑን፣ ኩማ ደመቅሳን፣ አስቴር ማሞንና ሙክታር ከድርን ብቻ በመያዝ በጎዶሎ እንደሚጫወቱ ታዉቋል፡፡ ለነገሩ አቶ ሙክታር ከድር የፕሬዚዴንትነቱን ቦታ ስለሚፈልጉ የተደራጀዉን የአባ ዱላ ቡድንን ለመቃወም እንጅ ለአለማየሁ አስተዳደር ወግነዉ እንዳልሆነ በሰፊዉ ይነገራል፡፡ ኦሮሞያ ከገዳ እስካ ኦህዴድ ገዳዳ፡፡

ዜና

# ኢትዮጵያ ታላቁን ዓለማቀፍ ሊቅ አጣች

ብስራት ወ/ሚካኤል

በዓለም ላይ አሉ ከሚባሉ የሥነ ጥበብ በተለይም የሥነ ሥዕል ሊቃውንት መካከል ኢትዮጵያዊው እጅግ የተከበሩ አርቲስት ሜትር የዓለም ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ አረፉ፡፡ አርቲስቱ በካዲስኮ ጠቅላላ ሆስፒታል ህክምና ሲረዱ ቆይተው ማክሰኞ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም በ80 ዓመታቸው አርፈዋል፡፡

አርቲስት አፈወርቅ ከአባታቸው ከአቶ ተክሌ ማሞ እና ከእናታቸው ወ/ሮ ፈለቀች የማታወርቅ በ1924 ዓ.ም በአንኮበር ከተማ እንደተወለዱ ተገልጻዕል፡፡ በትውልድ አካባቢያቸውም መንፈሳዊ ትምህርት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያንከተማሩ በኋላ አዲስ አበባ በመምጣት የቀድሞው ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ (በአሁኑ የኮተቤ መምህራ ኮሌጅ) ት/ቤት ገብተው መማራቸው ተጠቁሟል፡፡

ጣሊያን ከኢትዮጵያ ከተባረረች በኋላ ንጉሱ በወቅቱ ኢትዮጵያውያን ቀለም ቀመስ ወጣቶች የውጭ ዘመናዊ የትምህርት ዕድል ቀስመው እንዲመጡ ከላኳቸው ተማሪዎች አንዱ ናቸው፡፡ እሳቸውም የዕድሉ ተጠቃሚ በመሆን በለንደን እንግሊዝ የመጀመሪያው አፍሪካዊ ተማሪ በመሆን በሥነ ጥበብ ተመርቀው ከተለያዩ ሽልማቶች ጋር ወደ እናት ሀገራቸው ተመልሰዋል፡፡

አርቲስቱ እጅግ በርካታ ድንቃድንቅ የስዕል ጥበቦች ለዓለም አበርክተዋል፡፡ ከሚታወቁባቸው በርካታ ሥራዎች መካከልም "እናት ኢትዮጵያ፣ የሰሜን ተራሮች፣ መስቀል አበባ እና በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ ውስጥ የሚገኘው የአፍሪካ ነፃነትና ብሩህ ተስፋ" የሚሉ ሥዕሎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በሥራዎቻቸውም በዓለም የመጨረሻውን ከፍተኛ ማዕረግ ያገኙ አፍሪካዊ የጥበብ ሰው ሲሆኑ በዚህም ምክንያት "እጅግ የተከበሩ አርቲስት ሜትር የዓለም ሎሬት" የሚል መጠሪያን አግኝተዋል፡፡ ሥራዎቻቸውን በተለያየ የዓለም ክፍል በማቅረብ ኢትዮጵያንና ቀሪዎቹን የአፍሪካ ሀገሮች ማስተዋወቃቸው አይዘነጋም፡፡ በሥራዎቻቸውም በርካታ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን አግኝተዋል፡፡

በድንቅ ሥራዎቻቸው የተደመሙ የተለያዩ ሀገሮችም የክብር ዜግነት ቢሰጧቸውም "እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ ኢትዮጵያዊነት መታደልና ፀጋ ስለሆነ በሌላ የሚቀየርና የሚተው አይደለም" በማለት ምላሽ ይሰጡ እንደነበር ታሪካቸው ያስረዳል፡፡ የክብር ዜግነት የሰጧቸውም ሀገሮች አሜሪካ፣ ታላቋ ብሪታኒያ፣ ፈረንሳይ፣ ራሺያ ፌደሬሽን፣ ግብፅ፣ ጋና፣ ሴኔጋል እና ቫቲካን ይገኙበታል፡፡

አርቲስት አፈወርቅን ለየት ከሚያደርጓቸው አንዱ ጦር ኃይሎች አካባቢ በሚገኘው በሰፊ ግቢያቸው በተንጣለለው አልፋ ህንፃ ውስጥ የራሳቸውን የጥበብ ሥራ የሚሰሩበት ዘመናዊ ስቱዲዮ መስራታቸው ነው፡፡

በዓለማችን ላይ ካሉ 200 ታላላቅ ሰዎች መካከል ምስላቸውና የህይወት ታሪካቸው ተፅፎና በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተጠቅልሎ ጨረቃ ላይ እንዲያርፍ ተደርጓል፡፡

አርቲስቱ ህይወታቸው ከማለፉ በፊት ቤታቸው ሥራዎቻቸውና ስቱዲዮ ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሆን ቃል ገብተዋል በሚል አስከሬናቸው ለቀብር ሥነ ሥርዓት ሚያዝያ 6 ቀን 2004 ዓ.ም ቀትር ላይ ከቤት እንደወጣ የኢፌዲሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቅርስ ጥበቃና ክትትል ክፍል ቤታቸውን አሽጐታል፡፡

ቀብራቸው በመንበረ ፀባዕት ቅድስት ሥላሴ ቤ/ክርስቲያን በመንግስት የክብር የቀብር አፈፃፀም የተደረገላቸው ሲሆን አስከሬናቸው ከመኖሪያ ቤታቸው እስከ መስቀል አደባባይ በፌደራል ፖሊስ ማርሽ ባንድ የሐዘን ጣዕመ ዜማ ታጅቦ በመጨረሻምቅድስት ሥላሴ ደርሷል፡፡

በተለይ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት በገጠማቸው ችግር ምክንያት በሥፍራው መገኘት ባይችሉም የእሳቸውን ቃል ልጃቸው ዶ/ር አሉላ ፓንክረስት በመስቀል አደባባይ ተገኝተው አንብበዋል፡፡ ፐ/ር ፓንክረስት በሀዘን መግለጫው እንደጠቆሙት ለ64 ዓመታት ያህል ከእንግሊዝ ለንደን እስከ አዲስ አበባ ድረስ የቅርብ ጓደኛቸው እንደሆኑና ጥልቅ ሀዘን እንደተሰማቸው ገልፀዋል፡፡

በሥርዓተ ቀብራቸውም አቡነ ጳውሎስን ጨምሮ የተለያዩ ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት አበው ፀሎተ ፍትሀት የፈፀሙ ሲሆን በሥፍራውም የኢፌዲሪ ፕሬዘዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተወካዮች፤ የህዝብ ተወካዮች፤ ምክር ቤት ዋና አፈጉባኤ አባ ዱላ ገመዳ እና የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ አሚን አብዱልቃድር፣ ሚኒስትሮችና የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ተገኝተው ነበር፡፡

ከዓለም አቀፍ ዲፕማቶችም የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽንና የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ተወካዮችን ጨምሮ የግብፅ፣ የሞሮኮ፣ የናይጄሪያ፣ የአልጄሪያ፣ የላይቤሪያ፣ የቱኒዚያ እና የቦትስዋና ከአፍሪካ፤ የጣሊያን፣ የፖርቹጋል፣ የቼክ ሪፐብሊክ፣ የፈረንሳይ፣ የቫቲካን፣ የቤልጂየም እና የኔዘርላንድ ከአውሮፓ፤ የራሺያና የህንድ ከእስያ እንዲሁም የቬንዙዌላ ከላንቲን አሜሪካ አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች ተገኝተዋል፡፡

ሌላው ከተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) በአርቲስቱ መሞት ጥልቅ ሀዘን እንደተሰማው በመግለፅ፣ የጥበብ ሥራዎቻቸውም ለትውልድ እንዲተላለፉ መንግስት አስፈላጊውን ጥበቃ እንዲያደርግ በመጠቆም ለኤፌዲሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መግለጫውን የያዘ ደብዳቤ አስገብቷል፡፡ የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ዶ/ር ኃይሉ አርአያም በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገኝተዋል፡፡

በመጨረሻም የአርቲስቱ ቤተሰቦች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶች፣ ጓደኞቻቸውና አድናቂዎቻቸው በተገኙበት በቅድስት ሥላሴ ቤ/ክርስቲያን ቅዳሜ ሚያዝ 6 ቀን 2004 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ የክብር የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው ተፈፅሟል፡፡

# አቶ ይባስ አስፋው በአቶ ናትናኤል መኮንን ላይ የሞከሩት ድብደባ በእስረኞች ትብብር ከሸፈ

በግድያ ወንጀል 25 ዓመት እስራት ተፈርዶባቸው ቃሊቲ ማረሚያ ቤት የሚገኙት አቶ ይባስ አስፋው ቃሊቲ እስር ቤት የሚገኙትን የአንድነት ፓርቲ ብሔራዊ ም/ቤት አባል አቶ ናትናኤል መኮንን ለመደብደብ ያደረጉት ሙከራ በክፍሉ ውስጥ በሚገኙ እስረኞች ትብብር መክሸፉን የዜና ምንጮቻችን ገለጹ፡፡ የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት "በቅርቡ ከሌላ ክፍል ተዛውረው ወደ እነ ናትናኤል ክፍል የመጡት አቶ ይባስ አስፋው አቶ ናትናኤል ጐን እንደተኙ ከተደረጉበት ጊዜ ጀምሮ የተለያየ ምክንያት እየፈለጉ የትንኮሳ ሥራ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡" ይላሉ፡፡

ምንጮች እንደሚሉት አቶ ናትናኤል በሚተኙበት አካባቢ የምግብ ፍርፋሪ መጣል፣ አኪታ መትፋት፣ሲወጡና ሲገቡ ያልተገባ ፀያፍ ተግባር እየፈፀሙ ዝም ቢሏቸውም ሰሞኑን በቀጥታ አቶ ናትናኤልን ለመደብደብ ሲሞክሩ በክፍሉ ውስጥ ያሉ እስረኞች "እስቲ ጫፉን ትነካዋለህ' በማለት በጋራ በመነሳታቸው የድብደባው እቅድ ከሽፏል፡፡" ይላሉ፡፡ በመቀጠልም " አቶ ናትናኤል ወደ ለጥበቃ ሠራተኞች ሄደው በማመልከታቸው 'ሰውዬውን ከዚህ ክፍል ባታስወጡት እዚህ ክፍል ውስጥ ችግር 'ይፈጠራል' በማለት እስረኞች በጋራ ባሰሙት ጩኸት ይባስ አስፋውን ከዚያ ክፍል አውጥተው ወደ ሌላ ክፍል እንዲዘዋወሩ ተደርጓል፡፡" ብለዋል፡፡

አቶ ይባስ አስፋው ከዚህ ቀደም አቶ አንዱዓለም አራጌ ላይ "የግድያ ሙከራ አድርጐብኛል፡፡" በማለት ለፍ/ቤት ያመለከቱ ሲሆን "ዶክመንቴንም ነጥቆ ለማን እንደሰጠብኝ አላውቅም፡፡ ዶክመንቴ እንዲመለስልኝ ይደረግልኝ፡፡ በደረሰብኝ ጉዳት ማረሚያ ቤቱ በቂ የህክምና ድጋፍ እንዳገኝ አልረዳኝም ጉዳቱ የደረሰብኝ በማረሚያ ቤቱ የእስረኛ አያያዝ ችግር ነው፡፡ የተፈረደበት እስረኛና በቀጠሮ ላይ ያለ እስረኛ አብሮ አይታሰርም፡፡" ብሎ ያመለከቱ ሲሆን ፍ/ቤቱ ማረሚያ ቤቱን አስጠርቶ "አነጋገሮ ጉዳዩ በእስረኞች መካከል የተፈጠረ ጉዳይ ነው፡፡ እስረኛው ህክምና ማግኘት አለበት፡፡" በማለት ብይን ሰጥቶበታል፡፡ አቶ ይባስ አስፋው ከኤች አይ ቪ ቫይረስ ጋር የሚኖር ነው ተብሏል፡፡

# በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የሙዚቃ አልበም በገበያ ላይ ዋለ

## - ቴዲ አፍሮ የእጮኛውን ማንነትም ይፋ አድርጓል

ብስራት ወ/ሚካኤል

ለሰባት ዓመታት ያህል በመዘግየት በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የድምፃዊ ቴዎሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) የሙዚቃ አልበም ቅዳሜ ሚያዝያ 6 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በገበያ ላይ ዋለ፡፡

የአልበሙ መጠሪያ በዳግማዊ አፄ ምኒሊክ፣እቴጌ ጣይቱ ብጡል፣ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ፣ራስ አሉላ አባ ነጋና ሌሎች ለአንድነት፣ለነፃነትና ለሉዓላዊነት መስዋዕት ለከፈሉ ለክቡር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰና ለሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን መታሰቢያ "ጥቁር ሰው" የተሰኘውን ለህዝብ ጆሮ በቅቷል፡፡

በአዲካ ኮሚኒኬሽን ኤንድ ኢቨንትስ እና በቤሌማ ኢንተርቴይመንት አሳታሚነት ለሕዝብ የበቃው አልበም በውስጡ 11 ዘፈኖችን አካቷል፡፡ በሥራው ላይም "ቁጥር ሰው" የሚለው ክፍል የኦሮምኛው ግጥም ላይ ድምፃዊ ታደለ ገመቹ፣ "ፀባየ ሰናይ" የሚለው ግጥም ላይ ደራሲ ይልማ ገ/አብ እና "ፊዮሪና" የሚለው ዜማ ላይ ቴዎድሮስ መኮንን (ቴዲ ማክ) ከቴዲ አፍሮ ጋር በጋራ ከሰሩት ውጭ ቀሪዎቹ ሁሉም ግጥምና ዜማዎች በአርቲስት ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) መስራታቸው ታውቋል፡፡

የሙዚቃ ቅንብሩንም ሙዚቀኛው ሚካኤል ኃይሉ 8ቱን ሲያቀናብር፣አቡጊዳ ባንድ 2ቱን ከአበጋዝ ክብረወርቅ ሽዎታ ጋር ያቀናበሩት ሲሆን የአልበሙ መጠሪያ "ጥቁር ሰው" የማለውን ዘፈን ደግሞ አበጋዝ ክብረወርቅ ሽዎታ እንዳቀናበረው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለአልበሙ ሥራ ቴዲ አፍሮ ምን ያህል እንደተከፈለውም ሆነ እንደተስማማ ከአርቲስቱም ሆነ ከአሳታሚዎቹ ከግምት ባለፈ እስካሁን የተገለፀ ነገር የለም፡፡

ባለፈው ቅዳሜ የዋለው የቴዎድሮስ ካሳሁን የሙዚቃ አልበም በዋጋ ንረት እና በተፈጠረው የኑሮ ውድነት የቀዘቀዘውን የትንሳኤ በዓል ሰብሮ በመግባት በአዲስ አበባ አንድ ሲዲ ከ30-45 ብር መሸጡን ለመታዘብ ችለናል፡፡

አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ለመጀመሪያ ጊዜ እሁድ ዕለት በሥራዎቹ ዙሪያ በሸገር ኤፍ ኤም 102.1 ከጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ ጋር ባደረገው ቆይታ የእጮኛውን ማንነት ይፋ አድርጓል፡፡ እጮኛውም አርቲስትና ሞዴል አምለሰት ሞጩ እንደሆነች አርቲስቱ ገልጿል፡፡

# ኢህአዴግን በዘር ማጥፋት . .

ከገፅ 9 የዞረ

ሐሳብ አይጋጭም ወይ? የተባረሩት ደን ያቃጠሉ ናቸው ተብሎአል እንዴት ነው? ይፈናቀላሉ የሚባሉት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው?" የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተው አመራሩ በጋራ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የመኢአድ አመራሮች በጋራ በሰጡት መልስ "የአቶ ሽፈራው ሽጉጤ መግለጫውን በሰጡበት ዕለትም በዛሬውም ዕለት ድብደባው እስሩ ማፈናቀሉ እየተደረገ ነው፡፡ እሳቸው በሚናገሩበት ሰዓት አንዲት እናት ሊጥ እያቦካች ሳለ የአካባቢው ሚሊሻዎችና ፖሊሶች ደርሰው ከቤቱ እየደበደቡ ያወጡ ነበር፡፡ ሴትየው የእጇን ሊጥ እንድትታጠብ ብትለምናቸው እንቢ ብለው በጭካኔ እየደበደቡ ከነሊጧ ፖሊስ ጣቢያ አሰርዋታል፡፡ አንድ ሴት በወለደች በሁለት ሰዓት ልዩነት ከነደሟ አንጠልጥለው አውጥተው ሜዳ ላይ ጥለዋት ቤተሰቦ ተሸክሞ እንዲሸሽ ተገዷል፡፡ ተፈናቃዮች በክብር ሄዱ የሚሉት የሚገርም ነው፡፡ አዲስ አበባ አዋሬ ሄዳችሁ ማየት ትችላላችሁ፡፡ በቂ እርዳታ አጥተው መፀዳጃ ቸግራቸው ታያላችሁ፡፡ እስከ አሁን ሁለት ሺ ሰው ተፈናቅሏል፡፡ ለማፈናቀል እቅድ የያዙት 22ሺ አባወራ ነው፡፡ በሰው ቁጥር ሲሰላ 78ሺ ህዝብ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡ ደን ያቃጠለ በህግ ይጠየቃል እንጂ አይፈናቀልም፡፡ እነሱን ፖሊስ ጣቢያ አስረው ደኑን እያቃጠሉ ዶክመንተሪ ፊልም እያዘጋጁ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ የኢህአዴግ የተለመደ ባህርይ ነው" ሲሉ መልሰዋል፡፡

የደቡብና የአማራ ክልል ፕሬዝዳንቶች በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ያደረግነው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካም፡፡

## እርማት

በፍኖተ-ነፃነት ጋዜጣ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም 2ኛ ዓመት ቅፅ 2 ቁጥር 37 ላይ ‹‹የአንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን ላይ ክስ መሠረተ›› በሚለው ርዕስ ሥር "- - - በፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍ/ቤት 9ኛ የፍትሐ-ብሔር ችሎት ክስ መሠረተ፡፡" የሚለው "በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ 9ኛ ምድብ የፍትሐ-ብሔር ችሎት ክስ መሠረተ፡፡" በሚል እንዲነበብ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

# መምህራንና የቤተ መንግስት ግማሽ ቀን ውሎ

መ/ር ቀለሙ ሁነኛው
kelemhun@yahoo.com

የካቲት 22/2001 ዓ.ም የማለዳው ቅዝቃዜ 4 ኪሎን በመጠነኛው ቆፈን አጅቧታል፡፡ ከአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫዎች ተጓጉዘው የመጡ ሦስት ሺህ የሚጠጉ መምህራን ለቅዝቃዜው ሳይበገሩ የቤተመንግሥቱ አጥር መግቢያ በር እስኪከፈት እንደ ችቦ ተሰድረዋል፡፡ ከደቡብ ከትግራይ፣ ከኦሮሚያ፣ ከአማራ፣ ከቤንሻንጉል ክልሎች የተወከሉ መምህራን አንገታቸውን እያሰገጉ የቤተመንግስቱን ግቢ ለማየት ይታትራሉ፡፡ ሁሉም ክብር ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊን በአካል ለማየት የጓጉ ይመስላሉ፡፡

በሩ ተከፈተ፡፡ ፍተሻው በጥንቃቄ እየተከናወነ ከሁለት ሰዓት ቆይታ በኋላ የጠቅላይ ሚ/ሩ ጽ/ቤት መሰብሰቢያ አዳራሽ ካፍ እስከ ገደፉ ጢም አለ፡፡ ከማለዳው ሦስት ሰዓት አቶ መለስ ዜናዊ ከመድረኩ በስተቀኝ ባለው በር ከላይ ቡኒ መሣይ ኮት ከታች ጠቆር ያለ ሱሪ በሰማያዊ ሸሚዝ ለብሰው በአጀብ ወደ አዳራሹ ሲገቡ ሁሉም መምህራን ከመቀመጫቸው ተነስተው በጭብጨባ ተቀበሏቸው፡፡ ቿ! ቿ! ቿ! ቿ! ለአንድ መሪ የሚገባውን ክብር በመስጠት፤ ከአቶ መለስ ጐን የተቀመጡት የኢመማ ፕሬዝዳንት አቶ ዮሐንስ ባንቲ ንግግር ካደረጉ በኋላ ስብሰባው ተጀመረ፡፡ የሲቪክ ማህበራት ተወካዮችን ከመላ አገሪቱ እየሰበሰቡ ማነጋገር የአንድ ወቅት የኢህአዴግ የፖለቲካ ስልት ሆኖ በመቀየሱ ነበር ከወጣቶች፣ ከሴቶች፣ ከነጋዴዎች ወዘተ ቀጥሎ ለመምህራኑ እድሉ የተሰጠው፡፡ ይህ አዲስ የብልጣብልጥነት ስልት ብቅ ያለው ከ97 ዓ.ም ወዲህ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ስብሰባ አቢይ ትኩረት የመምህራንን ችግር ለጠቅላይ ሚ/ሩ ማሳወቅ ነበር፡፡ ከየክልሉ የመጡ ተወካዮች አስቀድመው የተዘጋጁ ውስን ጥያቄዎች ግን አንዳችም ሚዛን የማይደፉ ቢሆንም እንዲያቀርቡ በተመረጡ መምህራን አማካኝነት ቀርበው ተደመጡ፡፡

በዚህ መሀከል ባለ ½ ሊትር ሃይላንድ ውሃ በአስተናጋጆች መታደል ሲጀመር መምህራን ግር ተሰኙ፡፡ ገና በማለዳው ምን የሚሉት ውሃ ነው? ከለሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ጀምሮ ቁርስ ሳይበላ ወደ 4 ኪሎ ለተመመ ታዳሚ ውሃ ጀባ የተባለው፤ አይ የምኒሊክ ቤተመንግስት! ፍሪዳው ተጥሎ ጮማ እንደ ጎመን እንዳልተቆረጠበት፣ ጠጅ እንደ ውሃ እንዳልተጠጣበት ለመምህሩ ግብዣ ውሃ ቀረበለት፡፡ ደግሞ ለመምህር! ውሃ መች አነሰው? ያውም በፋብሪካ የታሸገ ሃይላንድ ውሃ፤

ርግጥ ነው መምህሩ የእውቀት ዘር ሊበትን በመላ አገሪቱ ተበትኗል፡፡ ያተላ ውሃ በልብሱ እያጠለለ፣ በጪስ እየተጨናበሰ ጎመን ሲቀቅል፣ ቂጣ ሲጋግር፣ ለሚኖር መምህር የቤተመንግስትን በር መርገጥ በራሱ መንግስተ ሰማያት እንደመግባት ይቆጠራል፡፡

ወደ ዋናው ሀሳቤ ልመለስ፡፡ በወቅቱ የቀረቡት ጥያቄዎች ሚዛን የማይደፉ የመምህሩን ችግር ያላንፀባረቁ እንደነበር ዛሬ ግሃድ ሆኗል፡፡ ይህ በመሆኑም ይመስለኛል የመምህራን የደመወዝ ጭማሪ ችግር አስታዋሽ አጥቶ ሲንከባለል ቆይቶ ዛሬ ግዙፍ ችግር ሆኖ ብቅ ያለው፡፡ በርግጥ በወቅቱ ከመምህራኑ ከቀረቡት የመብት ጥያቄዎች መሀከል የደመወዝ ጭማሪና የስኬል ማስተካከያ ጉዳይ ተጠይቋል፡፡ ጠቅላይ ሚ/ሩም ከመምህራኑ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል፡፡፡፡ በንግግራቸው መሀከል የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር በባለሞያ አስጠንቶ ለእሳቸው ያቀረበውን የደመወዝ እርከን ጥናት እንዳዩትና ግብአት እንዲሆን ለሲቪል ሰርቪስ መ/ቤት እንደመሩት ተናግረው ነበር፡፡

የዚህ ፅሁፍ መነሻም የጠቅላይ ሚ/ሩ ምላሽና የሰሞኑ ለመምህራን የእርከን ማሻሻያ ተደረገ ተብሎ በብዙሃን መገናኛ አታሞ የተደለቀለት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ከሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤት የጠረጴዛ ኪስ ውስጥ ተወርውሮ አቧራ ሲጠጣ ከረመ፡፡ የቀረበው ጥናት አሁን ካሁን ይተገበራል ተብሎ ሲጠበቅ ዓመታት አለፉ፡፡ የጉዳዩ መዘግየትና በአገሪቱ የተከሰተው የኑሮ ውድነት እጅግ አሰቃቂ ደረጃ ላይ በመድረሱ የማህበሩ ጠንካራ መሪዎች ድሬደዋ ላይ ጥቅምት 5 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰባስበው ጠንከር ያለ ሀሳብ ያዘለ የአቋም መግለጫ አስተላለፉ፡፡ የውሳኔውን ግልባጭ እያንዳንዱ መምህር እንዲያውቀው በየት/ቤቶቹ ተለጥፎ ተነበበ፡፡ መምህራን አወቁት፡፡ የማህበሩንም ውሳኔ ደገፉት፡፡ ከጐኑም ሊቆሙ ወሰኑ፡፡

የጉዳዩ መጠንከር ያሳሰበው ኢህአዴግ ጥያቄውን ለማፈን ቢሯሯጥም አልተሳካለትም፡፡ ሳይወድ በግድ የካቲት 12/2004 ዓ.ም ማህበሩ በአቋም መግለጫው መሠረት የጠራው አስቸኳይ ስብሰባ ላይ የሚመለከታቸው ሚኒስትሮች ተገኝተው በቅርብ ቀን የመምህራን ጥያቄ ምላሽ እንደሚያገኝ ተናገሩ፡፡ መምህራንም በጉጉት እንዲጠባበቁ ተነገረ፡፡

መጋቢት 3/2004 ዓ.ም ምሽት ግን መምህሩና ሞያው ላይ ብርቱ ውርደት ወረደ፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ሚ/ር እና የትምህርት ሚኒስቴር ሚ/ር ዴኤታዎች በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለው ማህበሩ ያቀረበው የእርከን ማሻሻያ ጥያቄ ለዲፕሎማ 61.00 ብር ለመጀመሪያ ዲግሪ 73.00 ብር በመጨመር ተመልሷል ተባለ፡፡ ለዚያውም ይህ ጭማሪ የመምህሩን ህይወት የሚለውጥ፣ የሞያውን የቀድሞ ክብር መልሶ የሚያጎናፅፍ፣ የመምህራንን ፍልሰት የሚገታ በሚል ነጋሪት ተጎሰመ በአቶ ፉአድ ኢብራሂም አስገራሚ ንግግር የደረጃ እድገቱም ከ6ደረጃ ወደ ሰባት ደረጃ ተሸጋግሯል ተባለ፡፡ ማህበሩ ያቀረበው ግን እንደሌሎች ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች 9 ደረጃ እንዲሆን ነው፡፡

መግለጫው በብርቱ ያስቆጣቸው መምህራን እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው ተነሱ፡፡ "መንግስት ክብራችንን ነካው፣ የውርደት ማቅ አለበሰን፣ ሞያውን አዘቀጠው" ሲሉ ቀፎው እንደተነካ ንብ በየት/ቤቱ ተተረማመሱ፡፡ ሁሉም እየተሰባሰቡ የአቋም መግለጫ በማውጣት የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ ሲጀምሩ የኢህአዴግ ሹመኞች ከቢሯቸው ወንበር ተነስተው ወደ ት/ቤቶች ከነፉ፡፡ በውይይት ለማሳመን ካልሆነም ለማስፈራራት፡፡ ግን ማንን ያስፈራራል? ፍርሃት ራሱ ይፍራ እንጂ! "ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም" እንዲሉ ነውና፡፡

ይድረስ ለአቶ መለስ ዜናዊ

ርስዎ የደርግን አስከፊ ሥርዓት ለመታገል በቁርጠኝነት በረሀ ሲወርዱ በየዱር በየገደሉ መምህራንን አግኝተው አያውቁም ነበር? መምህር ከወታደር ቀጥሎ በየጉራንጉሩ የዘመተ የዕውቀት አርበኛ እንደሆነ ለእርስዎ አይነገርዎትም፡፡ የካቲት 22/2001 ዓ.ም በቤተመንግስት የአገሪቱን መምህራን ወክለው የተገኙትን መምህራን ሲያወያዩ የደመወዛቸውን ጉዳይ ከግምት ማስገባትዎን፣ ሌሎች የመኖሪያ ቤትና መሰል ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ መንግስትዋ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚንቀሳቀስ የገቡት ቃል በ61 ብር እና በ73 ብር ወይም በአንድ የእርከን ጭማሪ ተጠናቀቀ፡፡ የእርስዎ የበታች ሹማምንት በተለይም መምህሩን በበላይነት የሚመራው ትምህርት ሚኒስቴር ሞያውን አራከሰው፡፡ ከአራት ኪሎው ጠማማ ፎቅ ጠማማ መግለጫ ተሰጠ፡፡

ክቡር ጠ/ሚ/ር እንደሚያውቁት የእግር ወለምታ በቅቤ ይታሻል የአፍ ወለምታ ግን በምን ሊታሽ ይችላል? የመምህራን ሞራል እንዳይጠግን ሆኖ ተሰብሯል፤ ክቡርነትዎ ጥንት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በየጠቅላይ ግዛቱ በነበሩበት ት/ቤትም በእሳቸው የመጎብኘት እድል ሳይገጥሞት አይቀርም፡፡ ግርማዊነታቸው ጉብኝት ሲያደርጉ ለተማሪዎች ማበረታቻ ይሰጡ ነበር፡፡ መምህራንንም ዳበስ ዳበስ እያደረጉ ያሞግሱ ነበር፡፡ ርስዎ ግን አይደለም መጎብኘት በአገሪቱ ውስጥ መምህራን ስለመኖራቸው እንኳን የዘነጉ ይመስለኛል፡፡ "ጽድቁ በቀረና በወጉ በኮነነኝ" እንዲሉ የርስዎ ጉብኝት ቢቀር እንኳን ድምፃቸውን እንዴት አይሰሙም? የመምህራኑ ጥያቄ መኪና ይሰጠን፣ ቪላ ቤቶች ይገንቡልን፣ መዝናኛ ሥፍራዎች ይዘጋጁልን የሚል አይደለም፡፡ "ተራብን፣ የወር ደመወዛችን ከቤት ኪራይ ክፍያ ማለፍ አልቻልንም፤ ታረዝን፣ ጫማችን ተንሻፍፎ፣ ሸሚዛችን ነትቦ፣ ሱሪያችን ተጥፎ ተማሪ ፊት ቆሞ ለማስተማር ተሳቀቅን. . . ይሄ እኮ ነው የመምህሩ ብሶት፡፡

ክቡር ጠ/ሚ/ር መምህራን ይህንን ብሶታቸውን ለመናገር (በተለይም በአዲስ አበባ) ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ የእርስዎ የበታች ሹማምንት በቃላት ውርጅብኝ ያስፈራሯቸዋል፡፡ "ዋ! ትተነፍስና! ዋ! ቃል ትናገርና! እምቢ ካልክ በአንዲት ገፅ ደብዳቤ ከሥራህ ትሰናበታለህ! ባንተ ምትክ ሌላ መምህር ይቀጠራል . . ." ይላሉ፡፡ ክቡርነትዎ ርስዎ የወጣትነት ወዘናዎን ለደደቢት በረሃ የገበሩት ለዚህ አይነት ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ነበር? አያሌ የኢትዮጵያ ልጆች በተለይም የትግራይ ወጣቶች አኩሪ የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉት ኢትዮጵያውያን ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲያንሸራሽሩ እንጂ እንዲታፈኑ አይደለም፡፡ በደርግ የታፈነው አይበቃም ወይ?

ክቡርነትዎ በየደረጃው ያስቀመጧቸው የድል አጥቢያ አርበኛ ሹማምንት በመምህሩ ህይወት ላይ ሲያፌዙበት እየሰሙ ማለፍ የለብዎትም፡፡ ግራ ቀኙን ይጠራጠሩ እንጂ! የድርጅቱን አላማና ራዕይ የሚያራምዱ መስለው ለሹመት የበቁ የቀበሮ ባህታዊ ያን ሊኖሩ ይችላሉ እኮ! ለዜጎች መልካም አስተዳደር እየነፈጉና በቢሮክራሲ ትብታባቸው እያማረሩ በመንግስትም የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቃቸዋል፡፡ ሹማምንቶችም በሕገ መንግስቱ ላይ የሰፈሩትን ሠላማዊ ትግል የማድረግ ዴሞክራሲያዊ መብትን ለመምህሩ ለመንፈግ በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ እየተንቀሳቀሱ ስለሆነ ሁኔታዎችን በትኩረት ሊከታተሉ ይገባል፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚ/ር መምህራን ከአገሪቱ አቅም በላይ የሆነን የእርከን ማሻሻያ አልጠየቁም፤ የአገሪቱ ጓዳ ካፈራው እንደ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በእኩል አይን ታይተው እንዲነቆነጠርላቸው ነው የጠየቁት፡፡ ሞያው ሰውን የሚያህል ፍጡር ሰው የሚያደርግ መሆኑ እየታመነ የመንግስት እጅ ለመምህሩ ሲሆን ለምን ያጥራል? ከሁሉም የሚያሳዝነው ድርጊት በመምህራን ደመወዝ ላይ ለተጨመረችው አንድ እርከን (ብር 61.00 እና 73.00) በብዙሃን መገናኛ የተሰጠው መግለጫ ነው፡፡ በሚዲያ መለፈፍ ለምን ተፈለገ? ለምን በሚ/ር መስሪያ ቤቱ የውስጥ አሰራር በደብዳቤ አልተገለፀም? ይሄ ነው መምህራንን አስቆጥቶ ሥራ ለማቆም ያነሳሳቸው፡፡

በእርግጥ ባለፉት ሳምንታት መምህራን በየትምህርት ቤቶቻቸው የወሰዷቸው ርምጃዎች እንደ ወንጀል ተቆጥረው በየደረጃው ባሉ ሹማምንት ሊታፈኑ ይችላሉ፡፡ በአንዳንድ ት/ቤቶችም መምህራን ከሥራ መባረራቸውን የሚያስረዳ ደብዳቤ ደርሷቸዋል ይህ ርምጃም የባሰ ቁጣን የሚቀሰቅስና የሚያባብስ እንጂ የዘለቄታ መፍትሄ አይሆንም፡፡ ለሌሎችም ማስፈራሪያና ዛቻ በተለያዩ አቅጣጫዎች እየደረሳቸው ይገኛል፡፡ ክቡርነትዎ ለተፈጠረው ችግር እየተወሰደ ያለው እርምጃ አንዳችም መፍትሄ አያመጣም፡፡ ዛሬ ባለንበት 21ኛው ክ/ዘመን ችግሮች መፈታት ያለባቸው በሰለጠነ መንገድ ነው፡፡ መንግስትም ስህተቶቹን አምኖ መምህራንን ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባል፡፡ ለመምህራን ጥያቄና ብሶት ጆሮ ዳባ በማለት በሚረባውም በማይረባውም ነገር ሰዎችን መወንጀል ተገቢ አይደለም፡፡ በሕገ መንግስቱ ላይ የተደነገጉት የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተጣሱ ቁጥር በገዢው ፓርቲ ላይ ጥላቻን ያሳድራል፡፡ መንግስትዎም ተአማኒነትን ያጣል፡፡ ከሁሉም በላይ የመምህራን አለመስማት በአገሪቱ የትምህርት ጥራት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ በቀላሉ ሊታይ አይገባም፡፡ ለዚህም ነው ሩሲያዊው ኮሚኒስት መሪ ቭላድሚር ኤሊች ኤልያኖቭ ሌኒን "በትምህርት ቤት ውስጥ በጣም ተፈላጊው ሰው መምህሩ ነው፡፡" ሲል የተናገረው፡፡ የሳምንት ሰው ይበለን፡፡

# ኢህአዴግን በዘር. . .

ከገፅ 10 የዞረ

ሲያዘርፉና ሲያፈናቅሉ የነበሩና አሁንም ድረስ ቀንደኞቹ የችግሩ ፈጣሪ አድራጊዎች የዞን፤ የወረዳና የቀበሌ ባለስልጣናት፤ እንዲሁም ሰው ደብድበው በመግደላቸው ምክንያት በግድያ ወንጀል መጠየቅ የሚገባቸው ግለሰቦች ከአዲስ አበባ ከሄደው ቡድን ጋር የችግሩ አጣሪ ቡድብ አባላት ሆነዉ እንዲሰሩ መደረጉ የመንግስትን ለመፍትሄ ዝግጁ አለመሆን አመላካች ነው፡፡ ሲል ከሷል፡፡

መግለጫው ሰለአጣሪ ቡድኑም የማጣራት ሂደት ሲዘረዝር፡-

የጥቃት ሰለባ የሆነውን ህዝብ ማነጋገር ሲገባው እስከ አሁን ድረስ አላናገረም ፤ሊያናግሯቸው ፈቃደኛ አልሆነም፡፡

በተቃራኒው የዞንና የወረዳ ኃላፊዎች እንደሚመቻቸው አድርገው ያዘጋጁቸውን ግለሰቦች እንደ አርሶ አደር አድርጎ በማቅረብ በአካባቢው ላይ ምንም አይነት ችግር እንዳልተፈጠረና ሰላም እንደሆነ፤ ማንም ላይ በፖሊስና በታጣቂዎች ድብደባም ሆነ ሌላ ጥቃት እንዳልተፈጸመ በመግለጽ ፤ ከአካባቢውም አንድም የተፈናቀለ አርሶ አደር እንደሌለ ፤እንዲሁም ደግሞ አካባቢውን ለቃችሁ ውጡ የሚል ኃይልም እንዳልመጣባቸው እንዲናገሩ ተደርጓል፡፡ አጣሪዎቹም ህዝቡን የማይወክሉትን፤ ነገር ግን ህዝቡን ወክለው ምስክርነት እንዲሰጡ የተደረጉትን እነዚህን የኢህአዴግ ታማኞች በቪዲዮ ሲቀርጹ ውለዋል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች የወረዳው የገጠር ልማት ሰራተኞችና የቀበሌ ካቢኔ አባላት መሆናቸው በግልጽ እየታወቀ የተሳሳተ መረጃ እዲሰጡ መደረጉ ኢህአዴግ እየሰራ ላለው ፀሀይ የሞቀውን ጉዳይ ለመካድና ለማፈንና እንዲሁም ለውሸት ዶክመንተሪ ፊልም ፕሮፓጋንዳው ግብአት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ መንግስት እውነት ችግሩን ለመፍታት ቢፈልግ ኖሮ የጥቃቱ ሰለባ የሆነው ህዝብ በሜዳ ተበትኖ ባለበትና አዲስ አበባን ጨምሮ ፤ከወለጋ እስከ ደብረ ብርሀን በፈሰሰበት ሁኔታ ተጎጂውን ህዝብ ባገለለ መልኩ ማጣራቱን ለማስኬድ ባልፈለገ ነበር፡፡ ቤንቺ ማጂ ድረስ መሄድ ሳያስፈልገዉ አዋሬ ያሉትን ተፈናቃዮች ማየቱ ብቻ በቂ ነዉ፡፡ የኢህአዴግን ባህሪ ለሚያውቅ ሁሉ ጉዳዩ ወዴት እያመራ እንደሆነ መገመት አይከብደውም፡፡

በክልሉ ያለው የችግሩ ገፈት ቀማሽ ህዝብ ግን ከተደበቀበት እየወጣ « እነዚህ ሰዎች የኢህአዴግ ሰዎች ናቸው ፤ የሚሰጡት ማስረጃም ህዝቡን የሚወክል አይደለም እኛ ችግር ደርሶብናል አዳምጡን ለማጣራት ከፈለጋችሁ ተጎጂው ህዝብ አካባቢ ውረዱና አናግሩን፣ የመንግስት ካድሬዎች ያቃጠሉትንም ቤት፤ ያወደሙትን ንብረት ተመልከቱ ፤ የህዝቡንም ማሳ እዩ ፤ በሜዳ የቀረውንም ከብት ተመልከቱ ፤ሰው አልባ የሆኑ መኖሪያ ቤቶችንም እዩ » ቢልም የሚሰማው አጥቷል፡፡ እንዳውም አጣሪው ቡድን ይገኝበታል ወደተባለበት ቦታ የተንቀሳቀሰውን ህዝብ የዩና የቁጥሩ መጨመር ያሰጋቸው የአካባቢው ካድሬዎች ህዝቡ በታጣቂና በፖሊስ ኃይል እንዲበተን አድርገዋል፡፡

አጣሪ ቡድኑ የተጎዳውንና የተሰደደውን ህዝብ የመኖሪያ አካባቢ በመተውና ሌላ አካባቢ ላይ በመሄድ በመኖሪያ ቤቱ የሚገኘንና ያልተፈናቀለን ህዝብ ሲቀርጽ ውሏል፡፡ምንም አይነት ችግር እንዳልተፈጠረም በሚዲያ አስነግረዋል፡፡ይህም ለተራ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ሲባል የህዝብን ጩኸት የማፈን ድርጊትም ፈጽመዋል ፡፡

አጣሪ ቡድኑ ደን ሲቃጠልና ፤ የደረቀ ዛፍ እየፈለገ ሲቀርጽ ሰንብቷል፡፡ይህም የአካባቢው ባለስልጣናት ህዝቡን ከሚያስፈራሩበትና በብዙዎች ላይ ክስም ከመሰረቱበት አንዱ ተግባር ነው ፡፡« ዛፍ አድርቃችኃል ፤ ደን አቃጥላችኃል » ብለን እንከሳችኃለን የሚለው ዛቻቸው እውነት ሆኖ በርካታ ዜጎች በዚህ ክስ ተከሰው ፍርድ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ኢህአዴግም ለሌላ ዙር የውሸት ዶክመንታሪ ፊልም (ድራማ) እየተዘጋጀበት ይገኛል፡፡ ብሎአል፡፡

መግለጫው በመጨረሻው ሲያጠቃልል የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ( መኢአድ ) «ይህን አይነቱን የአጣሪ ቡድኑን ድርጊት በህዝብ ላይ የተፈጸመ አስከፊ ግፍና በደልን ለመሸፋፈን የሚደረግ ርካሽ ተግባር በመሆኑ አጥብቆ ያወግዛል ፡፡ የሚመለከተውና ያገባኛል የሚል አካል ሁሉ ድርጊቱን እንዲያወግዝም ጥሪ ያስተላልፋል፡፡

መንግስት ለችግሩ መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ሁኔታውን ለመሸፋፈንና ለማዳፈን የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አቁሞ በአስቸኳይ ለነዚህ ዜጎች መፍትሄ እንዲሰጥ አሁንም በድጋሜ ጥሪ እናደርጋለን፡፡

ሰው የገደሉ፤ በአካል ላይ ጥቃት የፈጸሙ፤ በተለያየ ህገወጥ ተግባር ላይ በመሰማራት በህዝቡ ላይ ወንጀል የፈጸሙ የመንግስት ባለስላጣናት በህግ እንዲጠየቁ መኢአድ ይጠይቃል፡፡» ሲል ይደመድማል፡፡

በመጨረሻም አመራሮቹ ከጋዜጠኞች ጥያቄ ቀርበላቸዋል፡፡ "የደቡብ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት ሰሞኑን የተፈናቀሉ የሉም፡፡ ወደ ክልላቸው መሄድ የፈለጉ 800 ሰዎች በክብር ተሸኝተዋል ብለዋል፡፡ ይህ

# በዜጎቻችን ላይ እየደረሰ ያለ የማፈናቀል በደልን በማስመሰል ፕሮፓጋንዳ መደበቅ አይቻልም

## ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) የተሰጠ መግለጫ

የኢህአዴግ የከፋፍለህ ግዛው የጎሳ ፖለቲካ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በሀገራችን፣በተደጋጋሚ፣ከፍተኛ በደሎችን አስከትሏል፡፡ በበደኖ፣በአርባጉጉ፣በወለጋ፣ በጋምቤላ፣ በሲዳማ፣ በተለይ በጌዴኦና በጉጂ ዞን የተፈጸሙ ግጭቶችና የአስከተሉት እልቂት የቅርብ ጊዜ አስከፊ ትዝታዎች ናቸው

አሁን ደግሞ በሀገራችን የደቡቡ ክልል፣በተለይ በቤንች ማጂ ዞን፣ጉራፋርዳ ወረዳ በአማራ ብሔር ተወላጆች ወገኖቻችን ላይ ከፍተኛ በደል እየተፈጸመ ይገኛል፡፡ በደሉ እየተፈጸመ ያለው በክልሉ መስተዳድር ውስጥ ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ባሉ ባለሥልጣናት የተቀናጀ አሠራር ነው፡፡

ከአማራ ክልል የመጡና በጉራፋርዳ ወረዳ እስከ 30ዓመታት ድረስ የኖሩ ዜጎች እየተደበደቡ፣እየታሰሩና ከቀያቸው እየተፈናቀሉ ለስቃይ እየተዳረጉ ነው፡፡ የክልሉ ባለሥልጣናት ግን በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው በደል እንዳይታወቅና እውነቱ እንዳይወጣ ከፍተኛ ርብርብ እያደረጉ ናቸው፡፡ በዚህ ጥረታቸውም እርስ በርሳቸው የሚጋጩ አቋሞችን እየገለጹ ናቸው፡፡ የክልሉ አስተዳዳሪ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም በመንግሥት ሚዲያ በአደረጉት ጉዳዩን የመሸፋፈን ጥረት በአንድ በኩል “የተፈናቀለ ሰው የለም” ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ “33 ሰዎች ሕጋዊ ባለመሆናቸው ከነቤተሰቦቻቸው ወደ መጡበት እንዲመለሱ ተደርጓል” ይላሉ፡፡

ከጉራፋርዳ የተፈናቀሉ ሰዎች ከላይ የተጠቀሱት 33 ሰዎች ብቻ አይደሉም፡፡ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ በ11/10/2001 ለቤንች ማጂ ዞን ጽ/ቤት በጻፉት ደብዳቤ ከነሐሴ 30 ቀን 1999 በኋላ ወደ ዞኑ የገቡ የሌላ ክልል ዜጎች ሁሉ ወደ መጡበት እንዲመለሱ እንዲደረግ ማዘዛቸው ይታወቃል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ መሠረትም 800 የአማራ ብሔር ተወላጆች ወደመጡበት እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡

ወደ አማራ ክልል እንዲመለሱ የተደረጉ ዜጎች በምን ሁኔታ እንዲመለሱ እንደተደረገ መገመት አያዳግትም፡፡ እነዚህ ዜጎች መጀመሪያውኑ ወደ ደቡቡ የሀገራቸው ክፍል የሄዱት ከፍቷቸው ነው፡፡ ባይከፋቸው ኖሮማ የተወለዱበትን፣እትብታቸው የተቀበረበትን፣ያደጉበትን፣ዘመድ ወዳጅ ያፈሩበትን ቀየ ለቀው ባልሄዱ ነበር፡፡ ስለዚህ እነዚያ 800 ሰዎች ወደ መጡበት እንዲመለሱ የተደረጉት ወደውና ተስማምተው ሳይሆን ተገደው መሆን አለበት፡፡

በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ደብዳቤ ላይ እንደተገለጸው ደሕዴን እነዚያን 800 ሰዎች ባሕርዳር ድረስ ወስዶ ለብአዴን ያስረከበው በራሱ ወጪና በራሱ ትራንስፖርት ነው፡፡ የአማራ ሕዝብ ተወካይ ነኝ የሚለው ብአዴንም ለምን ብሎ አልጠየቀም፡፡ የክልሉ ዜጎች በማናቸውም የሀገሪቱ ክፍሎች የመኖር ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው እንዲከበር ከጎናቸው አልቆመም፡፡ በዚህ የሕግ ጥሰትም ከደሕዴን ጋር ተባባሪ ሆንዋል፡፡

ደሕዴን ቀደም ሲል 800 ዜጎችን ከክልሉ እንዲወጡ በአደረገበት የተለመደ አካሄዱ ሁለተኛውን የማፈናቀል ዙር ጀምሯል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ዙር የተፈናቀሉት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ እንደሚሉት 33 ብቻ አይደሉም፡፡ ከጉራፋርዳ ወረዳ ተፈናቅለው፣አዲስ አበባ መጥተው በመኢአድ ጽ/ቤት ጊዜያዊ መጠለያ ተሰጥቷቸው የተስተናገዱና በስም፣በፆታ፣በዕድሜ፣በወረዳ አድራሻና በመጡበት ቀን ጨምሮ የተመዘገቡ ዜጎች እንኳን ቢያንስ 157 (አንድ መቶ ሃምሳ ሰባት) ናቸው፡፡ ከእነዚህ ተፈናቃዮች መካከል ብዙዎች የደረሰባቸውን በደል በተመለከተ ሰሚ ይኖራል በሚል ተስፋ አቤት ለማለት ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ሄደው ነገር ግን ሰሚ አጥተውና ሜዳ ላይ ፈስሰው ሕፃናት፣እናቶችና አባቶች በፖሊስ ተከበው በፀሐይ ሲንቃቁ፣በመጨረሻም ከሕዝብ እይታ ለማራቅ ከቦታው በሎንቺና ሲወሰዱ የአንድነት ከፍተኛ አመራር አባላት በዓይናቸው አይተዋል፡፡ ተፈናቃዮቹን እንዳያነጋግሩም በፖሊስ ተከልክለዋል፡፡

የአቶ ሽፈራው ሽጉጤ የሰኔ 11 ቀን 2001 ደብዳቤ ሰፈራን በተመለከተ ቀደም ሲል በኢህአዴግ አራቱ ድርጅቶች መካከል የተደረሰ አንድ የጋራ ስምምነት መኖሩን ሲጠቁም፣ “በአገራችን በአሁኑ ጊዜ ሰፈራን በሚመለከት ያለው አሠራር ከክልል ክልል የሚፈፀም ሳይሆን በክልሎች በውስጣቸው ብቻ እንዲፈፀም የጋራ ሃገራዊ ስምምነት ተደርጓል” ይላላ፡፡ በዚህ ስምምነት መሠረት ሰፈራ ከክልል ውጭ ሊካሄድ አይችልም ማለት ነው፡፡ ይህ ስምምነት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 32 የተደነገገውን በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የመዘዋወር፣ኑሮን የመመሥረትና ንብረት የማፍራት መብትን ስለሚፃረር ሕገወጥ ነው፡፡

የደቡብ ክልል አስተዳደር በወሰደው ዜጎችን በኃይል የማፈናቀል ተግባር የሰው ህይወት ጠፍቷል፤ዜጎች በጦር ተወግተዋል፤በድብደባ ቆስለዋል፤ ታስረዋል፡፡ ለዓመታት ደክመው ያፈሩትን ንብረት አጥተዋል፡፡ በመፈናቀላቸው ለረሃብ፣ለጥማት፣ለእንግልት ተዳርገዋል፡፡ ሕፃናት ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ተገደዋል፡፡ በአጠቃላይ የበርካታ ዜጎች ህይወት ምስቅልቅሉ ወጥቷል፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከላይ በተጠቀሰው ወረዳ በአንድ የማርያም ቤተክርስቲያን ዙሪያ ይኖሩ የነበሩ የአማራ ብሔር ተወላጆች በመፈናቀላቸውና ቤተክርስቲያኑ ያለአገልጋይ በመቅረቱ የቤተክርስቲያኑ ታቦት (ጽላት) በአቅራቢያው ወደሚገኘው የሚካኤል ቤተክርስቲያን ተወስዶ በደባልነት እንዲያርፍ ተደርጓል፡፡

ከማፈናቀሉ ተግባር ጋር በተያያዘ የወቅቱ ትልቅ ጥያቄ የደቡብ ክልል አስተዳደር ቀደም ሲልም ሆነ አሁን በተለይ የአማራ ብሔር ተወላጆችን ለበርካታ ዓመታት ከኖሩበት እያፈናቀለና ወደመጡበት እየመለሰ ያለው ለምንድን ነው? “ለአማራው ሕዝብ መብትና ጥቅም የቆመኩ ነኝ” የሚለው ብአዴንስ የክልሉ ዜጎች መፈናቀልን የደገፈ በሚመስል መልኩ በዝምታ መቀበሉስ ምን ይባላል? የሚለው ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከደቡብ ክልል አስተዳደር የሚሰጠው መልስ የተምታታ ነው፡፡ በአንድ በኩል የተፈናቀለ ሰው የለም ሲል በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል 800 ሰዎች አሁን ደግሞ 33 ሰዎች ሕጋዊ ባለመሆናቸው ወደ መጡበት እንዲመለሱ ተደርጓል ይላል፡፡ ዜጎቹ ሕገወጥ ከሆኑ እንደማንኛውም የአካባቢው ተወላጅ ዜጋ በሕግ ተዳኝተው በአሉበት ፍርዳቸውን ያገኛሉ እንጂ ከሚኖሩበት ተፈናቅለው እንዲባረሩና ምንም ያላጠፉ ሌሎች የቤተሰቡ አባላትም ጭምር እንዲሰቃዩ አይደረግም፡፡ ይህን ማድረግ ኢ-ሕጋዊና ኢ-ሰብአዊ ነው፡፡ ስለዚህ ከማፈናቀሉና ከማባረሩ በስተጀርባ ያለው ምክንያት ሕጋዊ አለመሆን ሳይሆን ሌላ መሆን አለበት፡፡

ለማፈናቀሉ አንድ ዋና ምክንያት ፍንጭ የምናገኘው ተፈናቃዮች ከልብና በቁጭት ከሚናገሩት ነው፡፡ ከተፈናቃዮች አንዷ ወ/ሮ ለፍኖተ-ነፃነት ጋዜጣ ሪፖርተር በምሬት የሰጡትን ቃል እንመልከት፡፡ “ከሰሜን ሸዋ ሄደን እዚያ መኖር ከጀመርን ከ20 ዓመት በላይ ነው፡፡ አራት ልጆች አሉኝ፡፡ ከእኔና ከባለቤቴ ጋር ስድስት ቤተሰብ ነን፡፡ በሁለት ጊዜ ምርጫ መሬት የሰጣችሁን ኢህአዴግን መምረጥ ሲገባችሁ ተቃዋሚዎችን መርጣችኋል፡፡ ከእንግዲህ አታስፈልጉም፤አካባቢውን ለቃችሁ ሂዱ አሉን፡፡ ወዴት እንሂድ ብለን ስንጠይቃቸው አናውቅም፤ውጡ ብለው ደበደቡን፡፡ ባለቤቴ በደረሰበት ድብደባ ዛሬ መቆም አይችልም፡፡ አዲስ አበባ የደረሰው በስቃይ ነው፡፡ አሁንም ተኝቷል፡፡ ልጆቼን የማበላው የለኝም፡፡ ቤተክርስቲያን ለማደር ብንሄድ አባረሩን፡፡ ለጊዜው መኢአድ እዚህ እረፉ ብሎን እዚህ አርፈናል፡፡ ልጆቻችን ትምህርት አቋርጠዋል፡፡ ግራ ገብቶን ተቀምጠናል፡፡ ለማን አቤት ማለት እንዳለብን ጠፍቶናል፡፡ ማንም ሊያዳምጠን አይፈልግም” ሲሉ በማልቀስ ተናግረዋል፡፡

ከወ/ሮዋ መሪር ንግግር የምንረዳው የማፈናቀሉና የማባረሩ አንዱ ምክንያት ብቀላ ነው፡፡ መሬት የሰጣችውን ኢህአዴግን በመምረጥ ፈንታ ተቃዋሚዎችን በመምረጣቸው የመጣ ቅጣት ነው፡፡ ሌላው ምክንያት ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ በተለይ በጉራፋርዳ ወረዳ ውስጥ ለሚገኙና ከ22,000 በላይ ለሆኑ፣በአጠቃላይ ደግሞ በደቡብ ክልል ለሚኖሩ ሰፋሪዎች በመጪዎቹ ምርጫዎች ተቃዋሚዎችን እንዳይመርጡ የተላለፈ ከባድ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአማራው ሕዝብ ተወካይ ነኝ የሚለው ብአዴን ዝምታና ተባባሪነትም ግልጽ ሆኖ ይወጣል፡፡

የአማራ ብሔር አባላት በሆኑ ወገኖቻችን ላይ እየተወሰደ ያለው ርምጃና እያደረሰ ያለው ስቃይ መቆም አለበት፡፡ የዜጎች ሕገመንግሥታዊ መብቶች መከበር አለባቸው፡፡ መፈናቀሉ ያስከተለው የአካልና የህሊና ቁስል ተፈናቃዮችን ወደነበሩበት በመመለስ እንዲሽር መደረግ አለበት፡፡ ዜጎች የፈለጉትን በነፃነት እንዳይመርጡ ለማድረግ የሚወስደው የበቀል ርምጃና፣የሚተላለፈው የማስጠንቀቂያና የማስፈራሪያ ዘመቻ መቆም አለበት፡፡ የጎሳ ፖለቲካ መቆም አለበት፡፡ ለዜጎች መፈናቀልና መሰቃየት ምክንያት የሆኑ መመሪያዎችን የሰጡ ባለሥልጣናት በሕግ መጠየቅ አለባቸው፡፡ ዜጎቻችን በየ ዓረቡ አገር የሚደርስባቸውን ሰቆቃ እያየን ስንቆጭ በአገር ውስጥም ከአረቡ አገር ሰቆቃ ያላነሰ በደል በዜጎች ላይ ሲደርስ ማየት ልብ የሚሰብር ነው፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድ) እየተካሄደ ያለው የማፈናቀል ዘመቻ እንዲቆምና መረጋጋት ተፈጥሮ ዜጎች በመተሳሰብና በሠላም አብረው መኖር የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር አጥብቆ ይጠይቃል፡፡ በዚህ አጋጣሚ በደቡቡ የሃገራችን ክፍል የተከሰተው ችግር እንዲቆምና ለወደፊትም እንዳይደገም ለማድረግ የሚረዳ መረጃ የሚሰበስብ አጥኚ ቡድን ወደ አካባቢው የሚልክና የጥናቱንም ውጤት እንደ አስፈላጊነቱና እንደ አመቺነቱ ለሕዝብ የሚያሳውቅ መሆኑን ይገልጻል

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ
(አንድነት)
ሚያዝያ 6 ቀን 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# በርሜሉ ቀዳዳ ከሆነ . . .

ከገፅ 9 የዞረ

በርሜሉ እንዳይሞላ ያደርጋል፡፡ ያንተ ቃሊቲ መገኘት የበርሜላችንን ውሃ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ወዳጄ ሀይለ መስቀል ወዴትም እንዲሄድ አልፈልግም፡፡ ሙልነህ አያሌውን መከታተል እፈልጋለሁ፡፡ በኢህአዴግ አሰራር አንድ ቀን ሁላችንም ወንጀለኞች መሆናችን አይቀሬ በመሆኑ ሁላችንንም ማሰር ከማይችልበት ደረጃ ላይ መደረሱ የማይቀር ነገር ነው፡፡ ከዛሬ በፊት ያለ መድረሱ ራሱ በኛው ስህተት ነው፤ በርሜሉ እንዳሞላ እየሾለክን፡፡

በመጨረሻም

በትጥቅ ትግል ወቅት ህወሃት /ኢህአዴግ ለተማረኩ ወታደሮች ሦስት አማራጮችን ያቀርብ ነበር፡፡

አንደኛዉ በነፃ መሬት ሰርቶ መኖር፡፡ ነፃ መሬት ኢህአዴግ ከደርግ ያስለቀቃቸውና የራሱን አስተዳደር የመሠረተባቸው አከባቢዎች ናቸው፡፡

ሁለተኛዉ የኢህአዴግ አላማ ተቀብሎ መዋጋት ነበር፤ እነ ኩማ፣ እነአባዱላ፣ እነ ባጫ ደበሌ በዚህ መልኩ የተገኙ ናቸዉ፡፡

ሶስተኛዉ በነፃ መሬት በኩል ወደ ውጭ መሰደድነበር

አብዛኛዎቹ ምርኮዎች ሦስተኛውን መንገድ መርጠዋል፤ አሁን ያሉት ምርጫዎችም ደግሞ

1. ግዑዝ ሆኖ (ነፃ ሆኖ) ትንሽ ትንሽ ሰርቶ መኖር
2. ኢህአዴግ ሆኖ ቦርጭ ማዉጣት
3. መሰደድ፤ የሀሳብ ልዩነትማ ካለዎት መሰደድ፣ መሰደድ፣ መሰደድ...መሰደድ፣ መሰደድ፣...

## የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህር የሆኑት ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ "ወጣትነት የሀገር ፍቅር" በሚል ርዕስ የውይይት መነሻ ሐሳብ ያቀርባሉ። በውይይቱ ላይ ማንኛውም ሰው ተገኝቶ እንዲከታተል ተጋብዟል።

ቀን እሁድ 14/08/2004 ዓ.ም
ሰዓት ከጥዋቱ 3:00 ጀምሮ

ቦታ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ጽ/ቤት ቀበና ኦሮሚያ ደን ልማት ቢሮ ወደ ውስጥ 250 ሜትር ገባ ብሎ፡፡

የአንድነት ፓርቲ ወጣቶች ኮሚቴ

# የቀድሞ ፓርላማ አባላት የተከላካይ ምስክሮች ቃል ሳይሰማ ቀረ

በፌደራል አቃቤ ህግ ክስ የተመሰረተባቸው 69 ሰዎች መከላከያ ምስክሮቻቸውን ለማሰማት ለትናንት ሰኞ ሚያዝያ 8 ቀን 2004 ዓ.ም በፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት ተቀጥረው ነበር፡፡

አቃቤ ህግ ሚያዝያ 19 ቀን 2004 ዓ.ም በተሻለ በከሺ የክስ መዝገብ ላይ ከቀድሞው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ) አባል የነበሩት የኦህኮ አባላት የተከበሩ አቶ ጉቱ ሙሊሳ እና አቶ አስፋው አንጋሶ ይገኙበታል፡፡

ተከሳሾችም አቶ ተሻለ በከሺን ጨምሮ አቶ ትርፋሣ መገርሳ፣አለማየሁ ጋሮምሣ፣ መምህርት ሙላቷ አብዲሳ፣ልጅዓለም ታደሰ፣ሐሰን መሐመድ፣አዱኛ ለሜሳ፣ሚልኬሳ ዋቅጅራ፣ሳምሶን አለሙ፣ገመቹ አሚሾና ሌሎች 59 ሰዎች ከኦነግ ጋር በተያያዘ በሚል በሽብር ተግባር ተጠርጥረው ክስ ተመስርቶባቸው እንዲከላከሉ ብይን መስጠቱ ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከሳሾች የመከላከያ ምስክሮቻቸውን እንዲያሰሙ ለትናንት የተቀጠረ ቢሆንም ሳይሰማ ቀርቷል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የተጠቆመው በተከሳሾች ብዛት እና የ3ኛ ወንጀል ችሎት በመጥበቡ ለዛሬ ማክሰኞ ሚያዝያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋት ጀምሮ የተከላካይ ምስክሮችን ቃል ለመሰማት ፍ/ቤቱ በሰጠው ቀጠሮ መሠረት ይሰማል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ተከሳሾችም ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተጠርጥረው የተያዙ ሲሆን በአብዛኛው ከኦሮሚያ ክልል በተለይም በክስ መዝገባቸው ላይ የሰፈረው የመኖሪያ አድራሻቸው ላይ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ከአዲስ አበባና ከሶማሌ ክልል የተያዙ ሲኖሩ በክሱ መዝገብ ላይ ተጠርጣሪዎቹ በሙሉ ከኦነግ ጋር በተያያዘ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ ክስ ላይ በነ አቶ በቀለ ገርባ የክስ መዝገብ ላይ ተከሰው እንዲከላከሉ የተበየነባቸው ወጣቶችም ይገኙበታል፡፡

## ርዕዮት ዓለሙ . . .

ከገፅ 1 የዞረ

አብረዋት ተከሰው የተፈረደባቸው ሦስት ተከሳሾች ይቅርታ የጠየቁ ሲሆን ርዕዮት "ያጠፋሁት ጥፋት ስለሌለ ይቅርታ አልጠይቅም፤እስከ መጨረሻው እከራከራለሁ፡፡" በመጨረሻ ላይ የሚወስኑብኝን ውሳኔ ለመቀበል ወስኛለሁ፡፡ በማለት ይግባኝ መጠየቋ ይታወቃል፡፡

## "ሞረሽ" የተባለ የ "አማራ. . .

ከገፅ 1 የዞረ

አማራ ናችሁ ይሉናል፤አማራ ነን ስንል የለም ኢትዮጵያዊ ነን በሉ ይሉናል" ሲሉ ተናግረዋል፡፡ አምባሳደሩ በሰጡት መግለጫ "እስከነጭራሹ ኢትዮጵያ የሚባል አገር የለም የሚሉ አሉ" ያሉ ሲሆን ድርጅቱንም ከዚሁ አንፃር ማቋቋማቸውን አውስተዋል፡፡

የድርጅቱን አላማ በአራት ዋና ዋና ሀሳቦች የተቀመጡ ሲሆን በአማራው ላይ የሚደርሰውን ግፍ ማስቆም፣የኢትዮጵያን አንድነት ማክበር፣ዴሞክራሲን ማስፈን፣ባህልና ኃይማኖቷን ማስጠበቅ መሆኑ ተብራርቷል፡፡ አምባሳደር እምሩ ዘለቀ ንቅናቄውን በማስመዝገብ ላይ መሆናቸውን ገልፀው ደምብና ፕሮግራሙም በቅርቡ እንደሚደርስ በመግለፅ ሁሉም ሰው መሳተፍ እንዳለበት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## ማጣፊያው ላልተበጀለት . . .

ከገፅ 5 የዞረ

አልተሰተዋለም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ትንንሽ አዳዲስ ሀገራት ተፈጥረዋል፡፡ ወደፊትም ላለመፈጠራቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል አይመስለንም፡፡ ስለሆነም በፍትህ መነፈግ ብቻ ደካማ እና አቅመ ቢስ ሀገራት ከመፈጠራቸው በፊት በሀገራቸው ጥላ ስር (Under the umbrella of the mother states) ሆነው ፍትህ እና ዴሞክራሲ እንዲጐናፀፉ አሜሪካ መርዳት ይገባታል ባይ ነኝ፡፡ ጨካኞች እና አምባገነኖችን አቅፎ ደግፎ ጠላቴ የሚሉትን (አሸባሪዎችን) መቅጣት አዳጋች ይመስለኛል፡፡

ባራክ አባማ በቅርቡ የጋናን የዴሞክራሲ አካሄድ ከማንቆለጳጰስ አልፈው ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራት አርአያ እንደሆነ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ ይህ መልካም ይመስለኛል፡፡ ሆኖም ግን የሀገርዎን ብሔራዊ ጥቅም በማስላት ብቻ የአፍሪካው ቀንድ አምባገነን መንግስታት ወዳጅ ሆነዋል፡፡ እባክዎን ቢያንስ ቢያንስ የዴሞክራሲ አጋር ለመሆን ካልቻላችሁ የአምባገነኖች መከታ በመሆን አታስቀጥቅጡን፡፡ የኮንግረስ ዶናልድ ፔይን መንፈስም እንዳይወቅሳችሁ አስቡበት፡፡ በቅርቡ ቤልጄዬም ብራስልስ ላቀኑት የኬንያው ፕሬዝዳንት ራይላ ኦዲንጋ (Raila Edinga) የህብረቱ ፕሬዚዳንት ሀርማን ቫን ሮምፒ (Herman Vain Rompuy) እንደነገሯቸው ከሆነ የባህር ላይ ወንበዴዎችን ለማጥፋትና በሱማሊያ የሠፈረውን አሚሶን (Amison) ለማጠናከር 100 ሚሊዮን ዩሮ (100 million) ለመስጠት ቃል ተገብቷል፡፡ ይሄም ቢሆን ፍሬ ከርስኪ ይመስለኛል፡፡ በተለይ ለአፍሪካ ቀንድ ሀገራት፡፡ እዚህ ህዝቦች የዴሞክራሲ ያለህ እያሉ የሚያነቡበት አካባቢ ነው፡፡ በእርግጥ ነው አውሮፓውያኑ አትላንታ የሚል ስያሜ የሰጡት የባህር ሀይል ዘመቻን ሊያጠናክርላቸው ይችላል፡፡ በመለጠቅ ግን የኬኒያውን ፕሬዚዳንት ያናገሩት ሀርማን አንድ ቁም ነገር አንስተዋል፡፡ ይኸውም በመጪው (በቅርብ) ጊዜ የሚካሄደውን የኬንያ የምርጫ ሥርዓት በከፍተኛ ደረጃ ለመርዳት እና ያለፈው ጊዜ አሳፋሪ ስህተት እንዳይፈጠር እንደሚሰሩ ቃል ገብተዋል፡፡ ይሄ መልካም ይመስለኛል፡፡

### እንደ መደምደሚያ

በአምባገነኖች የምትመራው ኢራን የእግር ውስጥ እሳት እየሆነች መምጣቷን አለም ከተገነዘበው ውሎ አድሯል፡፡ ስለሆነም እናንተ ጠላት (ወዳጅ) ያላችሁት አንደኛው የአፍሪካው ቀንድ ሀገር የኑክሊየር ባለቤት ለመሆን ከተቃረበችው ሀገር ጋር ተባባሪ ከሆነ ጥቅማችሁን ሁሉ ሊያስቀረው ይችላል፡፡ ያለው አማራጭ ሁለት ነው፡፡ አንደኛው የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት አስከባሪዎችን መንግስታት በአካባቢው እንዲኖሩ መርዳት፡፡ ሁለተኛው ደግሞ አሸባሪዎችን ብቻ እንፋለማለን የሚሏችሁን አምባገነኖችን አቅፎና ደግፎ መያዝ፡፡ በእኔ በኩል ሁለተኛው አማራጭ የሚሰራ አይመስለኝም፡፡ ምርጫው ግን የናንተው ነው፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
UNITY FOR DEMOCRACY & JUSTICE (UDJ)

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

**የገቢ ማሰባሰቢያ የራት ፕሮጋራም**

አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየታገለ ይገኛል፡፡ ለትግሉ ስኬት የእርስዎ ድጋፍ ወሳኝ ነው፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ የራት ዝግጅት ፕሮጋራም አዘጋጅቷል፡፡ ለመግቢያ ባለ 1,000፣ 500ና 300 ብር መግቢያ ካርዶች ተዘጋጅተዋል፡፡

በራት ፕሮግራሙ ላይ ታዋቂ ግለሰቦች ንግግር ያደርጋሉ፡፡ የእራት ግብዣው ግንቦት 24 ቀን፣ 2004 ዓ.ም. ይደረጋል። የሆቴሉ ስም ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ.ም. በሚወጣው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ላይ ይገለፃል፡፡

በውጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያኖች በሀገር ውስጥ በሚኖሩ ቤተሰቦችና ጓደኞች አማካኝነት ካርዱን መግዛት ትችላላችሁ፡፡

ለተጨማሪ መረጃና ካርድ ለመግዛት በሚከተለው አድራሻ ይጠቀሙ፤
በቢሮ ስለክ ቁጥር 011-840-08-11
በተንቀሳቃሽ ስልክ 091-161-84-34
ኢ-ሜል፡ andientfinance@yahoo.com ወይም andinet@andinet.org

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
የሂሳብ ቁጥር፡ 510
ንብ ባንክ ዑራኤል ቅርንጫፍ

ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለህግ የበላይነት መመስረት፣ ሁላችንም ካርዱን በመግዛት ድርሻችንን እንወጣ!